"ሕርቃል ንጉሥ ነው:: ክርስቲያኖች በአረማውያን እየተሰቃዩ በነበረ ጊዜ የክርስቲያን አለቆችና ሊቃውንት ወደርሱ ሂደው የኛ ጠላቶች የሆኑ ወገኖቻችንን ሁሉ ገደሉብን በብርቱም እያሰቃዩን ነውና እባክህ አንተ እርዳን ብለው ለመኑት:: እርሱ ምን ብሎ መለሰላቸው ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ሰው የገደለ ሰው መላ ዘመኑን ይጹም ብለዋል:: እኔ ሰው የገደልኩ እንደሆን መላ ዘመኔን ለመጾም አልችልም:: ስለዚህ ምን ይመስላችኋል ቢላቸው መቼም የሰው ልጅ ዕድሜ ብዙ አይደለም ቢበዛ መቶ ነው::"

"አንተ እኛን ነጻ ካወጣኸን ጠላቶቻችንን ካጠፋህልን እኛ ተካፍለን ላንተ እንጾምልሃለን ብለው ቃል ገቡለት:: እርሱም በቃላቸው መሠረት ዘምቶ የክርስቲያኖችን ጠላቶች እንዳጠፋቸው በታሪክ ይታወቃል:: እኒያ ክርስቲያኖችም ስለ ሕርቃል 8 ቀን ጾሙለት:: እኛም በሑዳዴ ጾም የመጀመሪያው ሳምንት ዘወረደ ወይም ሕርቃል የምንለው ስለዚህ ነው:: እኛ ኢትዮጵያውያኖች እንደወሰንነው ስለ ቴዎድሮስ በየዓመቱ 8 ቀን እንጾማለን ብለን ወስነናል:: በዚህ ምክንያት ነገሩ ይካሄዳል ብለን አምነናል:: 3 ሲኖዶሱ ይኸን ካልፈቀደ የአጤ ቴዎድሮስን በዓል ለማክበር ለኛ አይከብድም:: ሕዝቡም የዚህ ግንዛቤ ይኖረው ዘንድ በተዋረድ የምንንቀሳቀስበትን መርሐ ግብር ነድፈናል" ሲሉ ጽፈዋል::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የታሪክ ጥቅሶች የሃይማኖት አባቶች ዛሬም ቢሆን አጤ ቴዎድሮስን የሚወዷቸው እንዳሉ ያመለክታል:: እነዚህ የሃይማኖት መምህራን አጤ ቴዎድሮስን የሚወዷቸው ለሃይማኖታቸው ቀናዒ የሆኑ ናቸው:: ሃይማኖታቸው ከፍ እንድትል የሚፈልጉ ከጳጳስ እስከ ካህን የአጤ ቴዎድሮስን መዋቅር ደግፈው ለቤተ ክርስቲያን እድገት የሚጥሩ ናቸው::

የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን መምህራን አሁን አሁን ወንጌልን ፈትፍተው የሚያስተምሩ ልጆች በቅለዋል:: እነዚህ ልጆች ናቸው ዛሬ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ከነጣቂ ተኩላ በመከላከል ላይ ያሉ:: አጤ ቴዎድሮስ ቢኖሩ ኑሮ በቅሎአቸውን እንደሸለሙት ሙሽራ ዲያቆን ይሸልሟቸው ነበር:: በዚሁ ከጠነከሩበት ምድራዊ ሽልማት ቢቀርባቸው ከፍተኛውን ሽልማት የሚሰጣቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይሸልማቸዋል::



# ክፍል ሰባት

## ምዕራፍ 1

### አጤ ቴዎድሮስ "የአሜሪካ ጦርነት አበቃ ወይ?"

የእስራት ዘመኔ በአበሻ አገር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 95 "አጤ ቴዎድሮስ ሳሙኤል፣ጎባትን በየጊዜው እየላኩ የአሜሪካ ጦርነት አበቃ ወይ?" እያሉ ያስጠይቁ ነበር:: ሲሉ ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስ ለምን ስለ አሜሪካ ጉዳይ ሊያውቁ ፈለጉ? ምን ታያቸው? የጥቁሮች መጎሳቆል አስጨንቋቸው ይሆን? ትኩረት ሰጥቶ የተቸበት እስካሁን አላነበብኩም የማርኮስ ጋርቪይ ራእይ ታይቷቸው ይሆን? ዛሬ ያለው የኢትዮጵያ ትውልድ ሊረዳው የሚገባው ነገር ቢኖር ኢትዮጵያ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በቅኝ ግዛት ተይዘው ለነበሩ ሕዝቦች ምሳሌ የነበረች መሆንዋን ነው:: ለዚህም ነው የማርቆስ ጋርቪይ ታሪካዊ ንግግሮቹን የምንጠቅሳቸው::

መልአክ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት ኑሮ እና ክርስትና በአሜሪካ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ127 "እኔ የማምነው አንድ አምላክ በኾነው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ በኢትዮጵያ አምላክ ነው:: ደግሞም እኔ ከማንኛውም ነጭ ጋር እኩል ነኝ ማርቆስ ጋርቪይ" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን ብሎ የሚናገር ትውልድ አሜሪካ ውስጥ የሚፈጠር መስሎአቸው ይሆን አጤ ቴዎድሮስ፣ አዎ በእርሳቸው ጊዜ ኢትዮጵያ ለሌሎች የአፍሪካ አገሮች አስተዋጽኦ ባታደርግም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለአፍሪካ ሕዝብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጓ አይዘነጋም::

ለዛሬው ለእኛው ትውልድ ሳይሆን ለወደፊቱ ኢትዮጵያውያን ትምህርት ይሆናቸው ዘንድ ለማሳሰብ ነው:: አሜሪካ የመጣሁት ሚያዝያ 29 ቀን 1979 ዓም ወይም በጎርጎርዮስ ቀመር በ1987 ሲሆን ምርጫን በተመለከተ ብዙም ቦታ ሰጥቸው አላውቅም ነበር:: ምክንያቱም አገር አለኝ የሚለው ስሜቴ ፈንቅሎ ኢትዮጵያ ጎንደር

ደብረ ታቦር ፋርጣ ግራሪያ ወርቄን ጽዮን ደብር ቁጭ ያደርገኝ ነበር።

አሁን ሁኔታውን ተገንዝቤ ይመስለኛል የአሜሪካን ምርጫ በትግዕሥት መመልከት ስጀምር ወደ ኋላ ከዚያች ካደኩባት የሣር ጎጆ ከአያቴ ጋር ቁጭ ብዬ የባጥ የቆጡን ጠይቄ የሚሰጠኝ መልስ ያረካኝ ጀመር። የኢትዮጵያን ታሪክ በኢትዮጵያውያን የተጻፉትን ደጉንና ክፉውን ደግሜ ደጋግሜ አነበብኩ። ራሴን አንቱ ለማሰኘት ሳይሆን እግዚአብሔር በሚያውቀው ከ1000 በላይ መጻሕፍትን ከ200 በላይ መጽሔቶችንና ብዙ ጦማር ጋዜጦችንና የሥዕል ድምጽ የቪዲዮን ካሴቶችን አጠራቅሜ ሳነብና ስመለከት ይበልጥ ኢትዮጵያ ትዝ ትለኛለች። ስለ ሀገሬ ጥዋት ማታ አስባለሁ።

የእናቴን ልጅ ወንድሜን በመጀመሪያ አሜሪካ ሳመጣው የጠየቀኝ ጥያቄ "የት አለ ዲግሪህ? የታለ ንብረትህ? አንተን የሚሉ ለአገር አሳቢ ያች አገር ለአንተ ምን አደረገችልህ? እኛ የገበሬ ልጆች ስንሆን ወላጆቻችን አርሶ አደሮች ናቸው። በአውቶቢስ ሥራ እየሄድክ ስለ ኢትዮጵያ መጽሐፍ የምትሰበስብ" ብሎ 13 ዓመት የምበልጠው ወንድሜ ላይ ታች ተመልክቶ ተቆጣኝ።

በእኔ ጭንቅላት የሚጉላላው ከአያቴ ከእማሆይ የሹሜ ጋር ቁጭ ብዬ ከወንዱ አያቴ ስማቸውን እንጂ መልካቸውን ያላወኩአቸው ከእርሳቸው ባልንጀራ አባ ፈጠነ ስለ ኢትዮጵያ ስለ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ግተውኛል። ቁጭ ብዬ ሳስብ ያ የነሱ ንግግር ከፊቴ መጥቶ ቁጭ ሲል ጭንቅላቴ ወደ ትውልድ አገሬ እየገባ ስላስቸገረኝ በሕይወቴ ላይ ብዙ ችግር ቢገጥመኝም "ተስፋ"ስላለኝ እጽናናለሁ። ወንድሜም አንድ ቀን ይረዳልኝ ይሆናል።

ልጆቼም ሰው ይሆኑ ይሆናል። እነሱ ባይሆኑ ምናልባት ልጆቻቸው ይሆናሉ። ሌሎች ኢትዮጵያውያን የወለዱአቸው ልጆች አያቶቻቸው ለመጡበት አገር ለኢትዮጵያ ያስቡ ይሆናል። ማን ያውቃል ኢትዮጵያውያን ከወለዱአቸው ልጆች መካከል የአሜሪካ ርእሰ ብሔር የሚሆን ይወለድ ይሆን? ለዚህ ይሆን አጤ ቴዎድሮስ የአሜሪካንን ጦርነት በጥሞና ይከታተሉት የነበረው?



"አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናትም ዛሬም ነገም" የተባለውን መጽሐፍ ለመጻፍ የተለያዩ መጻሕፍትንና ሰነዶችን ስመረምር አለቅሳለሁ። ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ጀኔቫ ላይ ሲናገሩ የተቀረጸውን የምስል ድምጽ ቪዲዮን ክር ስመለከት አለቅሳለሁ። የክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድን ማስታወሻ ሳነብ አለቅሳለሁ። ኮሎኔል ጎሹ ወልዴ ስለ ኢትዮጵያ የተናገሩትን ስመለከትና በተለያዩ መጽሔት ላይ የሰጡትን ሳነብ አለቅሳለሁ። ሌሎች አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ስለ ኢትዮጵያ ሲናገሩ አለቅሳለሁ። ሰቨን ራቨርሰን ስለ ኢትዮጵያና ስለ አጤ ቴዎድሮስ የጻፉትንና የተናገሩትን ሳነብና ስመለከት አለቅሳለሁ።

ሊቀ ጠበብት ፓንክረትስ ስለ ኢትዮጵያ ደጋግመው የጻፏቸውን መጻሕፍት ሳነብ አለቅሳለሁ። በተለይ "አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች" የተባለውን መጽሐፌን ስጽፍ ብዙ አልቅሻለሁ። "ከጋንቤላ እስከ ሁመራ" የተባለውን መጽሐፍ ስጽፍና ስለ ዳር ደንበር ሳስብ ሆዴ ሳገላብጥ አለቅሳለሁ። ደግነቱ ከሥራ ቤት ገብቼ ከጽሕፈት ቤቴ ቁጭ የምል ብቻየን ስለሆነ ሳለቅስና ሳዝን ባለቤቴ አታየኝም።

አንድ ቀን ግን ከሕዝብ ፊት ስሜቴን መቆጣጠር አቅቶኝ ልናገር ተነሥቼ አቋረጥኩት። ያም ቀን ሚያዝያ 2 ቀን 2002 ዓም ክቡር ሊቅ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና መሐንዲስ ግዛቸው ሽፈራው፣ አቶ ገብሩ አስራት ሲያትል መድረክ ስብሰባ ላይ ለጥያቄ እድል አግኝቼ የድምጽ ማጉያውን ከያዝኩት በኋላ ሳላውቀው ስሜቴ ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት፤አልፎ የወሎ ሕዝብ ግማሹ ትግሬ ነህ ተብሎ ሲደበደብ ይታየኝ ጀመር። የወልቃይት ልጆች ጎንደሮች አማሮችን "ባርኖስ" ያሉአቸው ከ1000 ሺህ በላይ አስረው የፈጇቸው ከአቶ ገብሩ ፊት ስቆም ስሜቴን አልተቆጣጠርኩትም። ባርኖስ ማለት በትግርኛ ትል አንበጣ ማለት ነው።

አቶ ገብሩ አስራት አማሮችን ትልና ተባይ ያሉአቸውን ልጠይቅ ስነሣ መናገር ተሳነኝ። ጽፌ ላነበው በጄ የያዝኩትን ጽሑፍ ሳላነበው ተውኩት። በዚህ ቀን ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ወቅቶች የኢትዮጵያውያን የምሁሮችን ሁኔታ ሳስብ አለቅሳለሁ። የሥነ መንግሥት ፖለቲካን ሁኔታ በተመለከተ ሳስብ አለቅሳለሁ። የምንኖረው ከሠለጠነው ዓለም ነው በማለት ምሁሮቻችን ሲያወሩ

እሰማለሁ:: እነሱ እንኳን ሊሠለጥኑ ቀርቶ የሠለጠነው ሕዝብ ምን እንደሚያደርግ የተረዱ አይመስሉም::

ለምሳሌ በ1981 ዓም ጄሲ ጃክሰን ለዲሞክራቱ ርእሰ ብሔር ለመሆን ተፎካካሪ ነበሩ:: እርሳቸው አፍሪካን አሜሪካን ናቸው:: አንድ ቴሌቪዥን ጣቢያ "ጥቁር ለፕሬዝዳንትነት ብቁ ነው?" ብሎ ጠይቆ ነበር:: መልሱ "93 እጅ ጥቁር ለፕሬዝዳንትነት ብቁ አይደለም" የሚል ሲሆን በ2000 ዓም በተደረገው የምረጡኝ ፉክክር "አሁንም "አፍሪካን አሜሪካን ለፕሬዝዳንት ብቁ ነው? የሚል ጥያቄ ሲቀርብ መልሱ "97 እጅ አፍሪካን አሜሪካን ለብሬዝዳንትነት ብቁ ነው" የሚል ነበር:: ሴነተር ኦባማ የምረጡኝ ፍክክር በጎርጎርዮስ አቆጣጠር የካቲት 5 ቀን 2008 ማታ በቴሌቭዥኑ ሳዳምጥ ቆይቼ ከወጣሁ በኋላ አለቀስኩ ይህን ስመለከት ትዝ ያለኝ ነገር ቢኖር ወራቱ በቅንጅት መከፋፈል ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለበትን ሳስብ አለቅሳለሁ::

በተለይ ነሐሴ 22 ቀን 2000 ዓም ደንቨር የመዝጊያ ተፎካካሪው ሴናተር ኦማባ ንግግር ሲያደርጉ አልቅሻለሁ:: እርሳቸው የአባታቸው አገር ኬንያ ነው:: ኬንያ ቀደም የኢትዮጵያ ግዛት ነበር ኬንያ ማለት በኦሮምኛ "የኛ" ማለት ነው:: ደንበሩ ከኢትዮጵያ ጋር የተለየው በ1897 ዓም ወዲህ ነው:: የደንቨሩን የስብሰባ መዝጊያ ስመለከት አሜሪካ አንድ ትልቅ አብዮት የተካሄደ መስሎኛል:: ይህ የአንድነት አብዮት ጠበሉ ወደ ትውልድ አገሬ እንዲደርስ አምላኬን ተማፀንኩ::

የአሜሪካንን ምርጫ ሳይ የቀድሞዎቹ ርእሰ ብሔሮች ለመናገር ሲነሡ ሕዝቡ ጭብጨባው አላቆም ብሎ ተመለከትኩ:: ርእሰ ብሔር ክሊንተን ለመናገር ሲነሡ ሕዝቡ በጭብጨባ ደስታውን ሲገልጽ ሳይ በትውልድ ሀገሬ መሪዎች የደረሰውንና ለወደፊቱም የሚደርሰውን ሳስብ አለቅሳለሁ:: የአሜሪካን ምርጫ በተመለከተ ምን ተደረገ ለሚለው የዓለምን ሕዝብ ቀልብ የሳበ ታሪክ ነው:: በርግጥ አሜሪካ ከ1484 ዓም ወይም 1492 በእስፔን ተወላጅ ክርስተፎር ኮሎምቦስ በተባለ ተጓዥ ተገኘች:: ይህ የባሕር ላይ ተጓዥ አሜሪካን ሲያገኝ ባዶ መሬት አልነበረም ሰው ይኖርበት ነበር::

ነዋሪዎች ሕንዶች ሲሆኑ ዛሬ ድረስ ነቲቭ አሜሪካን ይባላሉ:: እነሱም የተለያዩ በጎሳና በቋንቋ የማይገናኙ ናቸው:: በእነሱ የተጻፈ



መጽሐፍ ሳነብ የጎሳቸው ብዛት ከ350 በላይ መሆናቸውን ይገልጻል:: ነገር ግን ሀገሪቱን የሚያስተዳድረው ከዛሬ 4 መቶ ዓመት በፊት ከአውሮፓ የመጣው ትውልድ ነው:: አውሮፓውያን መሬት ጠቦአቸው ወደ ደቡብና ሰሜን አሜሪካ መጥተው ከተወላጆች ጋር ለተወሰነ ጊዜ ተቀላቅለው ከኖሩ በኋላ ተወላጆችን አድክመው ሥልጣኑን በጃቸው ካደረጉ በኋላ ብዙ ጦርነቶች ነበሩ::

ይህን ያልተበላ መሬት ካገኙ ጀምሮ በጉልበት የሚያገለግላቸው ባርያ አመጡ:: አንዳንድ ባልንጀሮቼ "ሁሉንም ከኢትዮጵያ ነው ካላልክ አይሆንልህም" ይሉኛል:: ነገር ግን ታሪክ በመሆኑ መነገር ይኖርበታል እላለሁ:: ታሪክ ጠቅሼ ነው የምናገረው እንጂ ኢትዮጵያን ስለወደድኩ ሁሉን ከኢትዮጵያ የመጣ አስመስዬ መናገር አልሻም:: ቱርኮች ቀይ ባሕርን ተቆጣጥረው ባርያ መግዛት ሲጀምሩ በተለይ በ1525 ዓም አካባቢ አጤ ግራኝ አህመድ አንበልምም ያሉትን ክርስቲያኖች እንደ ባርያ ይሸጡ ነበር:: ሌላው ቀርቶ የአጤ ልብነ ድንግል ልጅ የኋላው አጤ ሚናስ ጦርነት ላይ ተማረኩ:: ባርያ ሁነው ተሸጡ::

አጤ ግራኝ አሕመድ ሙተው የአጤ ልብነ ድንግል ልጅ አጤ ገላውዴዎስ ሥልጣን ሲይዙ የአጤ ግራኝ አህመድ ልጅ ወገራ ላይ ሲማረክ ሁለቱ እቴጌዎች የፈጸሙት ድርድር (ድፕሎማሲ) ውጤት አቤቶ ሚናስን የአጤ ግራኝ አህመድ ባለቤት እቴጌ ድል ወንበራ አስመጥተው ልጃቸውን ከአጤ ልብነ ድንግል ባለቤት ከእቴጌ ሰብለ ወንጌል አስመልሰዋል:: በዚህ ወቅት ብዙ ኢትዮጵያውያንን አጤ ግራኝ አህመድ ባርያ አድርገው ወደ ቱርክ መሸጣቸው አይዘነጋም::

ቱርክ ኢትዮጵያውያን ባሮችን ጭኖ ወደ ሀገሩ ሲመጣ በጊዜው ኃያል የነበረው የስፔን የባሕር ኃይል ቀምቶ ስፔን ወሰዳቸው:: ከዚያም ለ6 ወራት ስፔን አስቀምጦ ወደ አሜሪካ አመጣቸው:: በአፍሪካን አሜሪካን የታሪክ ትንታኔ መሠረት በመጀመሪያ የተገኙት ጥቁሮች 16 ሲሆኑ ቦታው ፍላደልፊያ መሆኑን ሲያብራራ የት አገር እንደመጡ ሰነድ ያጣ መሆኑን ይገልጻል::

በኢትዮጵያውያን የታሪክ ትንታኔ መሠረት እነዚህ በመጀመሪያ የተገኙት ኢትዮጵያውያን ናቸው:: የዛሬው ሰላሴ ቀድሞ ጃማ ይባል ነበር! ጃማ የመጡ በመሆናቸው ከአሜሪካ ወደ ዛሬው ጀማይካ ሄዱ::

ያረፉበትን አገር ስም ላለመርሳት ጃማ የሚለውን እንደያዙ ለብዙ ዘመን ቆዩ። ነገር ግን ከግዜ በኋላ ጃማ የሚባለው ጀማይካ ተባለ። መልካቸው ኢትዮጵያውያንን የሚመስሉ በብዛት አሉ።

ዛሬ በዓለም ላይ ተከብሮ የሚገኘው የትራፊክን መብራት የፈለሰፈው ግሬተር ሞርጋን ነው። እርሳቸው ጥቁር ሲሆን የትራፊክ መብራት ሠርቶ በሥራ ላይ ካዋለው በኋላ ትርጉሙን በኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ ዓይነት ሰይሟል። ይህ ከፈረንሳይ የመጣው ጥቁር ኢትዮጵያዊ ዘር ሊኖረው ይችላል። ከዚህ በፊት ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ዓለም ዙሪያ ታላላቅ ተግባር ይፈጽሙ ነበር። እንግዲህ ከአፍሪካ የመጡት ጥቁሮች በባርነት ቀንበር ተጥሉባቸው ይሰቃዩ እንደነበር አይዘነጋም። ጥቁሮች ጠንክረው በመታገላቸው ርእሰ ብሔር ጆሴፍ ኬኔዲ መምረጥና መመረጥ ይችላሉ ብለው በማጽደቃቸው እነሆ ዛሬ አፍሪካውያን ከአደር አደር እየተደራጁ ናቸው።

ዛሬ ያለው የአሜሪካ ትውልድ ምን ይሠራል እንጂ ቆዳው ምንድነው የሚል ጥያቄ ሳያስገባ በአባታቸው ኬንያ በእናታቸው አሜሪካዊ የሆኑትን ርእሰ ብሔር አቶ ባራክ ሁሴን ኦባማን መረጣቸው። ኬንያ ቀደም ሲል በአክሱምና በላሊበላ ዘመነ መንግሥት ብቻ ሳይሆን በሸዋ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ግዛት ነበረች። የአጤ ግራኝ አህመድ ጦርነት መነሣትና ኋላም ዘመነ መሳፍንቱ መደገም እንኳን ራቅ ያለውን ግዛት ለመያዝ ቀርቶ መሐል ያሉትን አውራጃዎች የሚያስተዳድር መንግሥት ባለመኖሩ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ቅኝ ገዥዎች ከኬንያ ጋር ያለውን መሬት ራሱን የቻለ አገር አድርገው ሲወስዱ ኬንያ ለኢትዮጵያ ጎረቤት አገር ሆነች።

ስለዚህ ርእሰ ብሔር አቶ ኦባማ ቢርቅም ኢትዮጵያዊ ዘር አላቸው። ኢትዮጵያውያን ቀደም በትምህርት ኋላም በስደት ወደ አሜሪካን የገባን ብዙ መቶ ሺህ ነን። ታዲያ ከኢትዮጵያውያን ሆነ ከሌሎች አፍሪካውያን ጋር በመጋባት ብዙ ቅይጥ ልጆች ተወልደዋል። እነዚህ ልጆች የመማር እድል ያገኙ ቁጥራቸው ብዙ መቶ ብቻ ሳንሆን ዛሬስ ብዙ ሺህ ልጆች ተወልደዋል። ማን ያውቃል የእኛ ልጆች ባይሆኑም የልጅ ልጆቻችን የአሜሪካ ርእሰ ብሔር ሁነው ሳይመረጡ አይቀሩም! እኔም ሕልም አለኝ።



አንባብያን ግራ ሳይገባችሁ አይቀርም። ምክንያቱም ከአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ጋር ይህ ምዕራፍ ምን አገናኘው ትሉ ይሆናል። በመሠረቱ ትክክል ነው። አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያውያን አሜሪካን መጥተው መኖራቸውና ዛሬ ትውልድ አገራቸውን ኢትዮጵያን በምጣኔ ሃብት ለማሳደግ የሚያደርጉት ጥረት ታይቷቸው ይሆን? ከዚህ በፊት በተለያዩ መጻሕፍቶቼ አልፎ አልፎ ኢትዮጵያውያን ወደ አሜሪካ እንዴት እንደመጡና እንደተስፋፉ መመዝገቤ ይታወቃል። የሃይማኖት አባቶች አጽም ዛሬ በሰሜን አሜሪካ ዐርፏል በውጭው ዓለም ለኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ያበረከቱት ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ አንዱ ነበሩ።

ግልጽና ቀና የነበሩትን አባት ምሁራን አሳስተዋቸው በሥርዓተ ጳጳስ ደረጃ ፍትሐተ ጸሎት ሳይደረግላቸው እንደ አልባሌ ሰው ተረሱ። የሚገርመው ነገር ከእርሳቸው የቀብር ሥርዓት ላይ ለመገኘት ከመጡት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ወደ ጎዙኑም እንዳይገቡ የተከለከሉ ነበሩ። ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱና ሌሎች ሊቃነ ጳጳሳት እያሉ ሊቀ ጳጳስን ያህል ሰው በተራ ካህናት ፍትሐት ተደረገ። ከዚህ ከአንድ ክፍለ ሀገር ወደ አንድ ክፍለ ሀገር አስከሬኑን ሲያመላልሱት ሰንብቶ ጀማይካ አጽማቸው ለማረፍ በቁ። አሁንም የእርሳቸው አጽም ካለበት ቦታ ላይ በአባ ይስሐቅ ስም ገዳም መገደም አለበት። ይህን ለማድረግ መላው የቤተ ክርስቲያን ምእመን መነሣት ይኖርበታል።

መታየት ያለበት የመጀመሪያው ተግባራቸው እንጂ በምሁራን ምክንያት የተፈጠረውን ልዩነት መቁጠሩ አያስፈልግም። እኔ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅን የምመለከታቸው በመጀመሪያ ያደረጉትን የተቀደሰ ተግባር ነው። ለዚህም ለወደፊቱ ታሪክ የሚጽፉ ሁሉ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ለምን እንደ አልባሌ ሰው ተረስተው ቀሩ? ብሎ ጥያቄ ሲያቀርብ ስህተቱ ከማን እንደሆነ መረዳት ይችላል። በኢትዮጵያ ታሪክ ከልቅሶ አትምጡ ተብሎ ተከልክሎ አይታወቅም። ከልቅሶ ላይ ሰዎች አትምጡ አይባሉም! ለምን መጣችሁም አይባልም። እጅግ የተጣሉ ቢሆኑም ከልቅሶ አይከለከሉም! ወይዘሮ ምንትዋብ አጤ ቴዎድሮስ በራሳቸው ሽጉጥ ሲሞቱ በማየታቸው ይህን ብለዋል።

"አባቴን ቢገድሉ ነበር መናዴዴ፤
ወንድሜን ቢገድሉ ነበር መናዴዴ፤

በራስሁ ቆረጡ ይቅር አለ ሆዴ”

እያሉ ያለቀሱት ጀግና እንደ ሰው ከሞተ በኋላ ማንኛውም ሰው አዘንተኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው:: እርሳቸውማ እንዲያውም አጤ ቴዎድሮስን በመደገፍ የፈረንጁን ጉርቦ አንቀው አብረው ሙተዋል:: ይህን ነው ታሪክ ያስተማረን እንጂ ከልቅሶአችን አትምጡብን ከዚህ በፊት ተብሎ ተጽፎ አላነበብኩም:: ሊቀ ጠበብት ጌታቸው ኃይሌ በዚህ ዙሪያ የጻፉትን ከመጽሐፋቸው ጥቅስ ልውሰድ::

<u>አንዳፍታ ላውጋችሁ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 290 “ሲያሳድዷቸው ኖረው ሲሞቱላቸው ተሽቀዳድመው ሊቀብሯቸው ኒው ዮርክ መጡ አሉ:: ከፍትሐቱ ሥነ ሥርዓት ሲወገዱ ያሳፈረን እሱ ነው እያሉ በኔ በውሳኔው በሌለሁበትና በቦታው ባልነበርኩበት አማረሩ፤ከጳጳስ አፍ የማይወጣ ብልግናም ተናገሩ” ሲሉ ጽፈዋል:: ምናልባት በወቅቱ አብረዋቸው ከነበሩት መካከል ስህተቱ የማን እንደሆነ ግልጥልጥ አድርጎ የሚጽፍ እንዳለ ይወጣ ይሆናል::

ለሊቀ ጠበብት ጌታቸው ኃይሌ ወይም ደግሞ ዛሬ ገለልተኛ ነን ለሚሉት ምሁራን ሳይሆን ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ የሁላችን አባት ናቸው:: ይህ ገለልተኛ ነኝ የሚለው ኃይል የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር የሚያናጋ የሆዳሞች ዋሻ ነው:: ስደተኛውን ሲኖዶስ ደግፉ አልልም:: ምንም እንኳን ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን እያፈረሷት መሆንዋን ባምንም ቅሉ ገለልተኛ ከመሆን የብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ ልጆች ብትሆኑ የተሻለ መሆኑን እመርጣለሁ::

ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ብቻ ሳይሆኑ ብፁዕ አቡነ ዜና ማውቆስ እንዲሁ በምድረ አሜሪካ ዐረፉ:: በእርሳቸው ማረፍ ያላዘነ ኢትዮጵያዊ የለም:: በእርሳቸው ማረፍ ምክንያት ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮን የብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ ሲኖዶስ የሰጡት መግለጫ ቀደም ሲል ከጻፉት መጽሐፍ ጋር ይጋጫል:: በእርግጥ ታሪካችን በኀዘን አንጨክንም:: ይህ መሆኑን ጥሩ አድርጌ አውቃለሁ::

<u>ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ያፈረሱት አባ መርቆሬዎስና ተከታዮቻቸው</u> በቅዱስ ሲኖዶስ ተወግዘው ተለዩ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 44-47 ልዩነት የተፈጠረው በሥልጣን ጉዳይ መሆኑን መጽሐፋቸው



ያስረዳል:: ነገር ግን ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የካቲት 6 ቀን 2002 ዓም በማረፋቸው ለአሜሪካ ሬዲዮን ድምጽ መግለጫ ሰጡ:: ክርስቲያኖች በመጀመሪያ ለአረፈ ሰው ቅድሚያ ማጽናናት ነው ወይስ አሉ ባልታ የሚያስፈልገው? ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ታሪክ ያውም በቤተ ክርስቲያኑ ዘንድ ተሰምቶ አይታወቅም::

በተለይ ቅዱስ ሲኖዶስ ነው ከሚባለው ጽ/ቤት ይህ መግለጫ ሲሰጥ የክርስቲያኖችን ልብ ያቆስላል:: ምክንያቱም የውግዘቱን መግለጫ አስፋፍተው ከላይ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ላይ በግል ብፁዕ አቡነ ዜናማርቆስን አስመልክቶ የተጻፈው ታሪክና ከዚህ ዝቅ ብሎ የምጽፈው መግለጫዎችና በግለሰብ ስም ከቤተ ክርስቲያን የመጣውን ደብዳቤ ለሚያነብ ቤተ ክርስቲያኗን እንዲርቅ ያደርጋል::

<u>ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ</u> በብፁዕ አባ ዜና ማርቆስ ላይ የተላለፈውን ውግዘት ማንሣት በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ፤ “ብፁዕ አባ ዜና ማርቆስ በ1971 ዓም የወለጋ ሀገረ ስብከት ሁነው ተሹመው ቆይተው ከ1984 ዓም ጀምሮ ቤተ ክርስቲያንን፤ሀገራቸውን ትተው የገቡትንም ቃል ኪዳን ዘንግተው ወደ ውጭ ሀገር በመሄድ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ የማይመለከታቸውን ተግባር ሲፈጽሙ ቆይተዋል፤በዚህም ምክንያት ቅዱስ ሲኖዶስ ንስሐ ገብተው በንስሐ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እስኪመለሱ ድረስ በውግዘት አርቋቸው ቆይቶ ነበር::

ይሁንና ይህ በእንዲህ እንዳለ ብፁዕ አባ ዜና ማርቆስ የካቲት 6 ቀን 2002 ዓም ስላረፉ በሲያትል-ሰሜን አሜሪካ አካባቢ የሚኖሩ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው ውግዘቱ ተነሥቶላቸው ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ መጥተው በሥርዓተ ሊቀ ጳጳስ ሥርዓተ ቀብራቸው በሀገራቸው ኢትዮጵያ እንዲፈጸምላቸው ጠይቀዋል:: ስለዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ በጥያቄው መነሻነት የካቲት 8 ቀን 2002 ዓም ባደረገው ጉባኤ ውግዘቱ የሥርዓተ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ማፋለስ ስለነበር ሥርዓተ ጸሎት ተደርጎላቸው ቅዱስ ሲኖዶስ በሚፈቅደው መካነ መቃብር ሥርዓተ ቀብራቸው እንዲፈጸም በማለት ቅዱስ ሲኖዶስ በአንድ ድምጽ ተስማምቶ ወስኗል” ይላል::

“የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው ውግዘቱ ተነሥቶላቸው ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ መጥተው በሥርዓተ ሊቀ ጳጳስ ሥርዓተ ቀብራቸው እንዲፈጸምላቸው ጠይቀዋል ”ይላል። ለመሆኑ የተወገዘ ጳጳስ ከሆነ እንዴት የመንፈስ ቅዱስ ልጆች ሊኖሩት ይችላሉ? ይህ ሰፋ ያለ ትችት የሚያስፈልገው በመሆኑ ባልፈው ይሻላል።”

“ሌላው አስከሬናቸው ወደ ኢትዮጵያ መግባት እንዳለበት የጠየቁ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ያስተማሩአቸውና ከኢትዮጵያ ሲያትል አምጥተው አሠልጥነው ፖርትላንድ የላኳቸው በመንፈስ ግን የብፁዕ ወጣያት አቡነ ጳውሎስ ልጅ የሆኑት ቀሲስ እንዱአለም ይርዳው፤ መሆናቸው ከቤተ ክህነት 12/4 2002 ዓም የተጻፈላቸው ደብዳቤ ያስረዳል።

<u>ለቀሲስ እንዱአለም ይርዳው</u>12/4/199/2002 ዓም “ከዚህም ጋር ውግዘቱ ተነሥቶላቸው አስከሬናቸው ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ ገብቶ ሥርዓተ ጸሎቱ ተፈጽሞላቸው ኢትዮጵያ እንዲቀበሩ በጠየቃችሁት መነሻነት ቅዱስ ሲኖዶስ የካቲት 8 ቀን 2002 ዓም ባደረገው ጉባኤ ውግዘቱ ተነሥቶላቸው ወደእናት ሀገራቸው ኢትዮጵያ መጥተው ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ እየተባሉ ሥርዓተ ጸሎት ተደርጎላቸው ሥርዓተ ቀብራቸው እንዲፈጸም ቅዱስ ሲኖዶስ የወሰነ መሆኑን እናንተ የመንፈስ ልጆቻቸው ተረድታችሁ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት ጉዳዩን በመከታተል ትብብር ታደርጉ ዘንድ ይህን ደብዳቤ ልከንላችኋል” ይላል።

ለአሜሪካ ድምጽ የሰጡትን መግለጫ በአንድ አረፍተ ነገር ከዚህ ደብዳቤ መግቢያ ላይ የጠቀሱ ሲሆኑ ድግግሞሽ በመሆኑ አልገለበጥኩትም። በእርግጥ ከዚህ ደብዳቤ ላይ ትንሽ ልይት የሚያደርገው ቃል “የካቲት 6 ቀን 2002 ዓም ከዚህ ዓለም በሞት የመለየታቸውን የወንድማችንን ዜና ዕረፍት በሰማን ጊዜ እጅግ በጣም አዝነናል፤ኀዘኑም ተሰምቶናል” ይላል።

የብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስን ዕረፍት በተመለከተ የሲያትል ሕዝብ ሁሉም አዘንተኛ ነበር። በተለይ የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ወንዱም፤ሴቱም፤ትልቁም፤ሕፃናቱም፤ሁሉም አዘንተኛ ነበር። ማረፋቸው ከተሰማ ጀምሮ ከተለያዩ ክፍለ ሀገር ሳይሆን ከተለያዩ አህጉራት ኢትዮጵያውያን ወደ ሲያትል ሲመጡ የቅዱስ



ገብርኤል ምእመናን ከአየር ማረፊያው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ማታ ደግሞ በየቤታቸው በመውሰድና እንግዶችን በማስተናገድ የተደረገውን መልካም ተግባር በዚች ምዕራፍ ጠቅሼ አልጨርሰውም እኔ እስከ መጨረሻው ሰዓት ስመለከት ሰንብቻለሁ።

እጅግ በኀዘን የተጎዱ መኖራቸውን አስተውያለሁ። ከቤተ ክርስቲያን መነኮሳት መካከል ከሎስ አንጀለስ ቅድስት ማርያም የመጡት አባ ጽጌድንግል ደግፋው ተጎድተዋል። ሌሎች እንዲሁ! አስከሬናቸውን ለማሳረፍ ከፍተኛውን ተግባር የፈጸሙ ከብዙ በጥቂቱ በእኔ ዓይን አቶ እዝራ ተሾመ፤እንጅነር ግርማ ኃይለ ልዑል ወንጌል ሰባኪው አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡንና የወቅቱ ሊቀ ዲያቆናት ታደሰ የኋላሸት የዛሬው አባ ገብረ ሥላሴ ለአብነት ብጠቅስ ይበቃል።

የብፁዕ አቡነ ዜናን አስከሬን አክብሮት ያገኙ ምናልባት ልዑል መኮንን ኃይለ ሥላሴና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ፤ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ታላቁ ባለቅኔ ጸጋዬ ገብረ መድኅን፤ እንዲሁም ድምጻዊው ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ፤ ሕዝቡ አዝኖ አልቅሶላቸዋል። ከላይ የጠቀስኳቸው ከትውልድ አገራቸው ላይ ነበር። በስደት ዓለም ከሰው አገር ላይ እንደ አቡነ ዜና ማርቆስ አክብሮት ያገኘ ኢትዮጵያዊ እስካሁን ያለ አይመስለኝም።

ለዚህም ታላቅ አክብሮት ያደረጉት ሠርቶ የማሠራት ልምድ ያላቸው ስማቸውን ከላይ የጠቀስኳቸው ምሁራንና የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሲሆኑ ለዚሁ በዓል ማማር ደግሞ የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ዋናዎቹ ናቸው። በእንባ በኀዘን ሰው የሚመለስ ቢሆን ኑሮ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ይመለሱ ነበር። ነገር ግን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ውጭ ከሞት የተነሣ ባለመኖሩ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ በሰው ኃዘንና ልቅሶ ሊመለሱ አልቻሉም። የብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስን ዕረፍት አስመልክቶ ነጸብራቅ መጽሔት ልዩ እትም ሁና ለ40 ቀናቸው መታሰቢያ ወጥታለች።

ዘራዐጻዊት ጌጡ <u>ነጸብራቅ መጽሔት</u> መጋቢት 2002 ዓም ገጽ 13 “የአባታችን አስከሬን በቋሚነት የሚያርፈው በአሜሪካ ሀገር በሒውስተን ቴክሳስ በሚገኝ ብቸኛውና የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳም እንደሚሆን በስደት ሀገር

የሚገኘው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል" ሲሉ ጽፈዋል:: እንዲሁም ሌላው ናፍቆት የተባለው መጽሔት እንዲህ ሲል ዘግቧል::

<u>ናፍቆት መጽሔት</u> የካቲት 2002 ዓም ገጽ 5 "አቡነ ዜና ማርቆስ በስደት ሕይወት ባሳለፏቸው ዓመታት ሁሉ በውጭው ዓለምም በስደት ላይ ያለውን ሕዝብ ሲያጽናኑ፣ በሃይማኖት ሲያንጹና ሲያረጋጉ እንዲሁም በስደታቸው ዘመንም ላከናወኑት ታላቅ ሐዋርያዊ ተልእኮ መነሻና የመንበረ ጵጵስናቸው ጽሕፈት ቤት በማድረግ ያገለግሉበት የነበረውን በሲያትል ዋሽንግተን የመካነ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራልን ሙሉ አገልግሎት የሚሰጥበት ቤተ ክርስቲያን አድርገው በማሳነጽና በማደራጀት ለ17 ዓመታት አገልግለዋል" ሲል ዘግቧል::

<u>አቦል መጽሔት</u> ታኅሣስ-ጥር-የካቲት 2002 ዓም ገጽ 42 "ገዳሙም በብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ሊቀ ጳጳስ እንደሚሰየም ታውቋል" ሲል የአስከሬን ማሳረፉን ሥርዓት አስመልክቶ ሰፊ ዘገባ ዘግቧል:: የብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስን ማረፍ አስመልክቶ ሲያትል ታይም ሁለት ቀን የዘገበ ሲሆን ሌሎችም የኢትዮጵያውያን መጽሔቶች ዘግበዋል::

ከዚህ ላይ ጠንከር ያለ ሥራ ስደተኛው ሲኖዶስ መሥራት እንዳለበት ማስጠንቀቂያ የሰጡም ምእመናን እንዳሉ ግልጽ ነው:: ገዳሙ መመሥረት እንዳለበት የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሲኖዶሱን ማሳሰባቸው ከዚሁ መጽሔት ለመረዳት ችያለሁ:: ይህን ግጥም የገጠሙት ኮሎምቦስ ኦኃዮ የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ምእናን ናቸው::

<u>ነጸብራቅ መጽሔት</u> መጋቢት 2002 ዓም
ገጽ 44 "ቅዱስ መርቆሬዎስ ስደተኛው አባት
ይበርቱ እንግዲህ እርስዎም በጸሎት
ብፁዓን ጳጳሳት ካህናት በሙሉ
በአንድነት ሆናችሁ በርታ በርታ በሉ
ሠርታችሁ አሠሩ አርአያ እንድትሆኑ
እንግዲህ በርቱና ገዳሙንም አቅኑ" ሲሉ ገጥመዋል::

ከላይ እየደጋገምኩ እንደጠቀስኩት አጤ ቴዎድሮስ የአሜሪካን ጦርነት ለማወቅ የፈለጉበት ምክንያት ምናልባት እንዲሁ ብዛት



ያላቸው ኢትዮጵያውያን መጥተው የሚኖሩበት መሆኑ ታይቷቸው ይሆን? በሂውስተን ቴክሳስ እንዲሁ በብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ስም ገዳም ተሰይሞአል:: አጽማቸው ሊያርፍበት በእቅድ ተይዟል:: ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ በብዛት ቤተ ክርስቲያን መሥርተዋል:: ከዚህ በፊት በኢትዮጵያውያን እጅ የገቡ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያናት ብዙ ዘመን ያገለገሉ ሲሆን አንዳንድ አካባቢ መሬት ገዝተው ትላልቅ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ያሳነጹ ጠንካራ ክርስቲያንኖች እንዳሉ አይዘነጋም:: ከነዚህ ሁሉ በታላቅነቱ የታወቀው ቤተ ክርስቲያንግን አትላንታ ነው::

<u>አቦል መጽሔት</u> ታኅሣስ-ጥር-የካቲት 2002 ዓም ገጽ 15 "በነሐሴ 29 ቀን 2009 ዓም በ5.5 ኤከር ላይ በ3.2 ሚሊዮን ዶላር ተገንብቶ ልዑል እግዚአብሔር ፈቅዶ ስለሆነ በቅዱስ ፓትርያርኩ መሪነት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፤ካህናት፤ መምህራን፤ ዲያቆናት መዘምራን እና ብዙ ምእመናን በተገኙበት ቤተ ክርስቲያኑ ተባርኮ ተመረቀ" ሲል መጽሔቱ ጽፏል::

ይህ ታላቅ ርእሰ አድባራት ቤተ ክርስቲያን የተገነባው አትላንታ ጆርጅያ ነው:: ይህ ቤተ ክርስቲያን አሜሪካ ካሉት የኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት በትልቅነቱ ግንባር ቀደም መሆኑ ተነግሮለታል::ዛሬማ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ማኅበራትም ተደራጅተው ሕንጻ እየገዙ ባለቤት ሁነዋል:: ለዚህ ቅድሚያ የሚሰጠው ኢትዮጵያውያን ቁጥራቸው ትንሽ ተግባራቸው ትልቅ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ያሉበት በችካጎ ያሉት ኢትዮጵያውያን ናቸው:: ለዚህ ታላቅ ተግባራቸው ለሌሎች በስም ምሁር ለሆኑት በተግባራቸው ከመሀይም ለማይለዩ ለሌሎች ምሁራን አርአርያ ናቸው::

ከችካጎ ኢትዮጵያውያን ኅብረት በሌሎች ክፍለ ሀገር ያለን ኢትዮጵያውያን ምን ተማርን? ማኅበራት መመሥረታቸው ሽማግሌቹ ተሰብስበው ይውሉበታል:: ሕፃናት በወላጆቻቸው ትውልድ ሀገር ፊደልና ቋንቋ የማንነት ታሪክ ሊማሩበት ይችላሉ:: ሕፃናት እውቀት ሊያገኙበት የሚችሉት ማኅበራት ሲመሠርቱ ነው:: ሥራ ፈልጎ ማስገባትና ሲታመሙና፤ሲደክሙ ረዳት የሌላቸው ብዙ አዛውንቶች ችግር ላይ መሆናቸውን መረዳት አለብን::

ዛሬማ ሩቅ ሳንሄድ ቁጥራቸው ትንሽ ተግባራቸው ትልቅ የሆኑት ኢትዮጵያውያን በችካጎ የተጀመረው በሲያትል መደገሙ በሌሎችም ኢትዮጵያውያን ባሉበት ቦታ ሁሉ ጠበሉ እንዲደርሳቸው በር ከፋች ሁኗል። ከዚህ አገር ለመኖር በማኅበር መደራጀት አስፈላጊ መሆኑን ወይዘሮ ሙሉእመቤት ረታ፤የሲያትል ማኅበር ሊቀ መንበር አስምረውበታል።

ወይዘሮ ሙሉመቤት ረታ <u>አውራምባ ታይም ጋዜጣ</u> 1ኛ ዓመት ቁጥር 3 ጥር 2011 ገጽ“ አንድነታችን በዚህ አገር ፖለቲካ ትልቅ አቅም አለው። ሴናተሩም ሆነ ሌሎች ፖለቲከኞች የኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ሲባል ሁሉም መምጣት ይፈልጋል። ምክንያቱም ለእነሱ ይህ ድምፅ ነው። ስለዚህ ችግሮቻችን ለማቅለል በኮሚኒቲ አንድ ሆነን መንቀሳቀስ አለብን።”

“የቱንም ያህል በፖለቲካ ልንለያይ እንችላለን እንደ ኮሚኒቲ ግን ውጤታማ የሚያደርገን ይህንን ኮሚኒቲ ስናጠናክረው እና ድምፃችን መሰማት ሲችል ነው። ሕዝቡ ለዚህ ሕንጻ መግዣት ቁልፍ ሚና ተጫውቷል። አሁንም ይህንን ሁሉ ስኬት አብቅተን ወደ ኋላ እንዳንመለስ ሕዝቡ ሥራዬ ብሎ ኮሚኒቲውን እንዲንከባከብ አደራ እላለሁ” ሲሉ ተናገሩ።

ይህን የሲያትልን ሕንጻ እንዲገዛ ጥረት ያደረጉት ትንሽ ናቸው። እነዚህ ኢትዮጵያውያን የማይሞት ልጅ በመውለዳቸው በታሪክ ሲታወሱ ይኖራሉ። “ሰው ሰው በመሆኑ ያልፋል። ጥሩ ተግባር ግን ከመቃብር በላይ ይኖራል። ስለዚህ በሌሎች በሉስ አንጀለስና በዋሽንግተን ዲሲና በአትላንታ ከተማ ያሉ ኢትዮጵያውያን ምን ይጠብቃሉ?

## ምዕራፍ 2

### በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን የተሾሙ ሹማምት

አጤ ቴዎድሮስ እንደነገሡ በየደረሱበት ክፍለ ሀገር ባላባቱን ሹመዋል። እንኳን በክፍለ ሀገር ደረጃ ቀርቶ በምክትል ወረዳ በየአካባቢው ታማኝ የሆነዉን ሹመውለታል። በጎጃም ራስ እንግዳ የሁሉም ጠቅላይ ገዥ ሁነው በውስጣቸው ብዙት ያላቸው ባለ



ማዕረጎች ሹመዋል። ትግሬንም ለራስ ባርያው እና ለራስ ኃይለ ማርያም ሲሾሙላቸው ባሕረ ነጋሽን በውስጣቸው አድርገው እንዲቆጣጠሩ አድርገዋል።

የባሕረ ነጋሽ ተወላጆች በራስ ባርያው አቅራቢነት ተሹመዋል። በተለይም የካቶሊክን ካህናትና የፈረንሳይን ወኪሎች ለመያዝና ለመውጋት የተዘጋጁትን የሐማሴን ተወላጆች በራስ ባርያው አቅራቢነት ከአጤ ቴዎድሮስ ፊት ቀርበው ሹመት የጸደቀላቸው ባላባቶች ናቸው። ወሎን ድል ካደረጉ በኋላ ስቆጣን ለደጃዝማች ገብረ መድኅን ማለትም ለአጤ ተክለ ጊዮርጊስ አባት ሌሎችንም አውራጃዎች እንዲሁ ባላባቱን ሹመውበታል። ሸዋን እንደተቆጣጠሩ ለባላባቱ የኃይለ ሥላሴን ልጅ መርድ አዝማች ኃይለ ሚካኤልን በሸዋ ሾሙ።

ታሪክ አለቃ ተክለ ኢየሱስ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 111 “ መርድ አዝማች ኃይለ ሚካኤልን በሸዋ ሾመ። ለአቶ አንዳርጋቸው አበጋዝነትን ሰጥቶ በየአለበት ጸና። የኃይለ ሥላሴ ሥርዓት ይርጋ ብሎ አዋጅ ነገረ” ሲሉ ጽፈዋል።

በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በሃይማኖትም በኩል ቢሆን መሪዎች ነበሩ። በተለይ በክርስቲያኑ መምህር አካለወልድ፤በእስልምናው ሼህ ሁሴን፤በአራቱ ሃይማኖት ካህን ሙሴ የተባሉ መኖራቸውን የሚናገሩ አሉ። በተለይም በግእዝ የተጻፈ መጽሐፍ ያላቸው አቶ አሰግድ ድሌ “የአራት ሃይማኖት ካህን ሙሴ የተባለ የደንቢያ ሰው ተባባሪያቸው ነበር” በማለት እየተረጎሙ አንብበውልኛል።

| | |
|---|---|
| 1ኛ ጳጳሱ አቡነ ሰላማ | 2ኛ ዕጨጌ ወልደ ማርያም |
| 3ኛ መምህር አካለወልድ | 4ኛ ሸህ ሁሴን ጅብሪል። |
| 5ኛ የአራት ካህን ሙሴ | ሌሎችም ምሁራን ነበሩ። |

አጤ ቴዎድሮስ ካህን ቢጠሉም በሄዱበት ሁሉ ጽላትና ሥዕል ካህናትና ዲያቆናት ሳያስዙ አይሄዱም ነበር። አብረው የሚሄዱ ካህናትና ዲያቆናትና ካህናት መካከል።

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ ቄስ አለሙ | 2ኛ ቄስ ካሣ | 3ኛ ቄስ ታፈረ |

4ኛ አለቃ ወልደማርያም 5ኛ ቄስ መኮንን 6ኛ ዲያቆን ርሃኑ
7ኛ ዲያቆን ዘመነ 8ኛ ዲያቆን ውቤ 9ኛ ዲያቆን ላኩ

ስማቸው ያልታወቀ ሌሎችም አለቃዎችና ጠንቃቃ መነኮሳት አብረው ይሄዱ እንደነበር ታውቋል። በቤተ መንግሥቱ በኩል የመኳንንት ልጆች ለአገር ይጠቅማሉ በማለት ከልጃቸው ከደጃዝማች መሸሻ ጋር በአንድነት ያስተማሩአቸው ብዙ ናቸው። ከብዙ በጥቂቱ እነዚህን ለአንባብያን ልግለጽ።

1ኛ ልጃቸው ደጃዝማች መሸሻ ቴዎድሮስ ኋላ እራስ
2ኛ ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜ ጎንደር ወልቃይት
3ኛ ደጃዝማች ጎበዜ ገብረ መድኅን ወሎ ሰቆጣ አገው ኋላ አጤ
4ኛ ደጃዝማች ምኒልክ ሸዋ ኋላ አጤ
5ኛ ባላምባራስ ካሣ ምርጫ ኋላ 4ኛው አጤ ትግሬ
6ኛ ደጃዝማች ዓለሜ ጓሉ ጎጃም
7ኛ ደጃዝማች መንገሻ አትኬም፣ጎጃም ኋላ በአጤ ምኒልክ ዘመን ራስ ቢትወደድ እነዚህን አስተምረዋቸዋል። ከነዚህ መካከል ደጃዝማች ዓለሜ ጓሉ አጤ ቴዎድሮስ ከመሞታቸው በፊት ሙተዋል። ሌሎች ከራስ መሸሻ ቴዎድሮስና ከራስ ቢትወደድ መንገሻ አትኬም በቀር በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ሸፍተዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ካስተማሩአቸው ከፍ ተብሎ ስማቸው ከተጠቀሰው መካከል ከደጃዝማች ዓለሜ ጓሉና ከደጃዝማች ጥሶ ጎበዜ በቀር ሌሎች ሁለቱ ራስ ለመባል በቅተዋል። ደጃዝማች መሸሻ ቴዎድሮስ ራስ ሲባሉ ደጃዝማች መንገሻ አትኬም በአጤ ምኒልክ ዘመን ራስ ቢትወደድ የተባሉት ሌሎች 3ቱ ኢትዮጵያን መርተዋል።

በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን የነበሩት ባለሥልጣኖች ከእርሳቸው ጀምሮ በነገራችን ላይ ብዛት ያላቸው የማዕረግ ስም የነበራቸው ብዙ ኢትዮጵያውያን ስላልተመዘገቡ በደረጃ ማስቀመጥ አልተቻለም። ለምሳሌ ከንጉሠ ነገሥቱ ቀጥሎ ንጉሥ መኖር ነበረበት ነገር ግን አጤ ቴዎድሮስ አልጋ ወራሽና ንጉስ አልፈቀዱም ነበር።

ከእርሳቸው ቀጥሎ እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ዓይነት ሥልጣን የነበራቸው የጎጃሙ ተወላጅ ራስ እንግዳ ነበሩ። እንደጦር ሚኒስተር ደግሞ ፊታውራሪ ገብርዬ ናቸው። በውረድ ተዋረዱ በማዕረጉ



ለማስቀመጥ ስጥር ተቸግሬም ነበር። ለምሳሌ በሀገራችን የማዕረግ አሰያየም እንዲህ ይሰየማል።

1ኛ ንጉሠ ነገሥት 2ኛ ንጉሥ 3ኛ ልዑል ራስ 4ኛ ራስ
5ኛ ቢትወደድ 6ኛ ደጃዝማች 7ኛ ፊታውራሪ
8ኛ ቀኝ አዝማች 9ኛ ግራዝማች 10ኛ ባላምባራ 11ኛ ልጅ ናቸው።

ከዚያም ደግሞ ጸሐፌ ትእዛዝና በጅሮንድ ሊቀ መኳስ ሌላም ሌላ ሲኖር በቤተ ክርስቲያን በኩል ደግሞ እንዲሁ በጣም ብዙ የማዕረግ ስም አለ። ስለዚህ ባጤ ቴዎድሮስ ዘመን የነበሩት ማዕረጎች ከዚህ በታች የምዘረዝራቸው ይሆናሉ።

1ኛ አጤ ቴዎድሮስ 2ኛ ራስ እንግዳ 3ኛ ራስ ኪዳነ ማርያም
4ኛ ራስ ወልደ ማርያም 5ኛ ራስ ጺጋ 6ኛ ራስ ውቤ
7ኛ ራስ ገብሬ 8ኛ ራስ አዳል ለማ 9ኛ ራስ ባርያው
10ኛ ራስ መሸሻ 11ኛ ራስ ባርኮ 12ኛ ራስ አዳሉ መስጦፋ።

1ኛ ቢትወደድ ባሕሪ 2ኛ ቢት ደማሽ 3ኛ ቢትወደድ ቢሰውር 1ኛ
4ኛ ቢትወደድ ዋሴ 5ኛ ቢት ቢሰውር 2ኛ 6ኛ ቢትወደድ ኀይሉ
7ኛ ቢትወደድ ደፋር 8ኛ ቢት ግርማ 9ኛ ቢት ቢሰውር 2ኛ ሌሎችም።

1ኛ ደጃዝማች ገልሞ 2ኛ ደ/ች ዓለሜ ቋሬ 3ኛ ደጃዝማች ባርያው
4ኛ ደጃዝማች አቦዬ 5ኛ ደጃዝማች ሊጋባ 6ኛ ደጃዝማች መሸሻ
7ኛ ደጃዝማች ጎጂ 8ኛ ደጃዝማች ገለታ 9ኛ ደጃዝማች ተሰማ
10ኛ ደጃዝማች ዓለሜ ጎጃሜው
11ኛ ደጃዝማች ይመር አሊ
12ኛ ደጃዝማች እንግዳ
13ኛ ቀኛዝማች ጣዩ በኋላ ደጃዝማች ተብለዋል።

ፊታውራሪ ገብርዬ ሙሉ ስማቸው ገብረ ሕይወት ተብለው ነው የሚጠሩት ነገር ግን አጤ ቴዎድሮስ አቆላምጠው "ገብርዬ" ስለሚሏቸው ሌሎችም የታሪክ ደራስያን ሙሉ ስማቸውን ሳይሆን የቁልምጫ ስማቸውን በመያዝ ዛሬ ድረስ ገብርዬ ተብለው ይጠራሉ። ፊታውራሪ ገብርዬ ወይም ገብረ ሕይወት ጎንደር ጋይንትና ጎጃም አገው ምድር አውራጃ ተወላጅ መሆናቸውን አቶ ገሪማ ታፈረ ጽፈውታል።

1ኛ ፊታውራሪ ገብርዬ
2ኛ ፊታውራሪ ካሣዬ
3ኛ ፊታውራሪ በሀካል
4ኛ ፊታውራሪ ሐሰኔ
5ኛ ፊታውራሪ ተድላ
6ኛ ፊታውራሪ ለምለም በመጨረሻ የተሾሙ

ፊታውራሪ ገብርዬ/ገብረሕወት የጦር መሪ ነበሩ:: እርሳቸው ካጤ ቴዎድሮስ ተለይተው አያውቁም:: ከአጤ ቴዎድሮስ ቀድመው መቅደላ የወደቁ ጀግና ናቸው:: ፊታውራሪ ገብርዬ ከእንግሊዞች ጋር ጦርነት ገጥመው በመጀመሪያ የሞቱ ናቸው::

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 215 "ገብርዬ በአንድ ፈረሰኛ ለምድ ለብሶ በአጫሜ ሾተል በወርቅ የተንቆጠቆጠ ጋሻ በግራ ክንዱ አንግቦ በጠገበ ፈረስተጋብቶ ሁለት አፎቿ ጦር አንዱን ነጥሎ በቀኝ እጁ ይዞ እየሰበቀ ሁለተኛውን በግራ እጁ ከፈረሱ ዛብ ጋር በማጣመር ከጋማው ላይ ጣል አድርጎ አሥራ አምስት በሚሆኑ ፈረሰኞች እየተከበበ ገብሬ የፈሪ ጅራፍ እያለ እየተንደቀደቀ ዘለቀና የዋለበትን የጦር ሜዳና የሠራውን ጀብድ በማስታወስ ፈክሮ ከፈረሱ ወርዶ እጅ ይነሣል፤ገብርዬ ያውልህ እኛን ለመውጋት ከባሕር ማዶ የመጣው የእንግሊዝ ጦር ጦርህን ያዝና ሂደህ ተዋጋ ብለው ያዙታል" ሲሉ ከጻፉ በኋላ ፊታውራሪ ገብረሕይወት ገብርዬ ዘምተው መሞታቸውን ዘግበዋል::

ስለዚህ ፊታውራሪ ገብርዬ የጦር መሪ ወይም ሚኒስትር ነበሩ:: በዳግማዊ አጤ ምኒልክ ዘመን ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የጦር መሪ ወይም ሚኒስትር ነበሩ:: በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ሻለቃ ማዕረግ ተሰጥቷል:: ሌላም ማዕረግ የነበራቸው ወታደራዊ ሞያ ያላቸው ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ አይዘነጋም::

1ኛ ሻለቃ ወልደጋብር 2ኛ ሻለቃ ስለሽ 3ኛ ሻለቃ ሊህ
4ኛ ሻለቃ ልይልህ 5ኛ ሻለቃ ወርቄ 6 ሻለቃ አባ ጋብር

በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ታሪክ የሚጽፉ ሆኑ የቤተ መንግሥቱን ዜና መዋዕል የሚያዘጋጁ ባለሞያዎች ሹመዋል:: እነዚህም ባለሞያዎች



አንዱ የረሳውን አንዱ ጽፎት ዛሬ እንድንመረምረው ሰነድ የተወልን ከዚህ ዝቅ ብሎ ስማቸውን የጠቀስኩት ናቸው::

1ኛ አለቃ ዘነብ
2ኛ አለቃ ወልደማርያም
3ኛ ስማቸው ያልታወቀውና ሌላም ሳይኖሩ አይቀሩም ነበሩ::

በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ሆነ ሕገ መንግሥት ፍትሐ ነገሥት ተርጉመው የሚያስረዱ ምሁራን ነበሩ:: እነዚህ ምሁራን እንደሌሎቹ የቤተ ክርስቲያን ምሁራን ማለትም ካህናትና ደብተራ አልያም ደግሞ መነኮሳት ፀረ ቴዎድሮስ ሁነው እንደተነሡት ሳይሆኑ ለኢትዮጵያ መልካም አመለካከት የነበራቸው ምሁራን ነበሩ::

1ኛ አለቃ እንግዳ 2ኛ አለቃ ገብረየስ
3ኛ አለቃ ፈንታ 4ኛ ቄስ ወልደማርያም
5ኛ ቄስ ማለደ 6 ከመጨረሻው አለቃ ገብረሐና

ከዚህ በታች ታዋቂ የነበሩትን ግለሰቦችና ዝቅተኛ ማዕረግ ያላቸውን በተራ እመዘግባለሁ:: እነዚህ ኢትዮጵያውያን ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ሁነው ለአገራቸው ብዙ የሠሩ ናቸው::

1ኛ በጅርወንድ አዳል የንብረት ሹም
2ኛ ነጋድራስ ገብረ መድኅን የንግድ ኀላፊ
3ኛ ጥሶ ኃይሉ የእንግዳ ሹም
4ኛ ሊቀ መኳስ ብሩ የአምባ ግሸን ሹም
5ኛ አዛዥ እሸቱ አጋፋሪ
6ኛ በጅሮንድ ክንፉ የንጉሡ ንብረት ኃላፊ
7ኛ ባላምባራስ ተሰማ የፈረሰኞች ሹም
8ኛ አዳም ወዳጄ የመቅደላ ሹም
9ኛ ክንቲባ ኃይሉ የጎንደር ክንቲባ
10ኛ ይመር ጎዳና የዋድላ ገዥ
11ኛ ባሻ መርዜን የግሼን ም/ል ሹም
12ኛ መሐመድ ሠራዊት የንጉሡ መልክተኛ
13ኛ ሊጋባ ተክሉ እልፍኝ አስከልካይ
14ኛ ባሻ እንግዳ ምክትል እልፍኝ አስከልካይ

15ኛ አዛዥ ፊንታ ጥይትና ጠበንጃ ተቆጣጣሪ
16 ባሻ ጣህር ቃሲም ረዳት ንብረት ክፍል
17ኛ አሳላፊ ኪዳኑ ለሸዋ ታዛቢነት ተሹመው የነበሩ::
18ኛ ልጅ አማን የቴዎድሮስ ጋሻ ጃግሬ የነበሩ በጦርነቱ የሞቱ
19ኛ ባላምባራስ ወልደ ጻድቅ መራጭ የኩናማ ገዥ የነበሩ::
20ኛ ባሻ እንግዳ መዝገብ ቤት
21ኛ ልጅ አብተው፤ ሌሎችም የነበሩ::

በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ብዙ አስተርጓሚዎች ነበሩ:: በረብኛ፤ እንግሊዘኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋን ጥሩ አድርገው የሚችሉ ምሁራን ነበሩ:: እነዚህ ውድ ኢትዮጵያውያን ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ሁነው አገራቸውን ያገለገሉ ዝናቸው ከፍ ብሎ ያልታወቁ ናቸው:: ከነዚህ መካከል ታዋቂ የሆኑት አቶ ማኅደረቃል ብቻ ናቸው::

1ኛ አቶ ማኅደረ ቃል አስተርጓሚ የትግራይ ልጅ
2ኛ እንግዳወርቅ አስተርጓሚ የትግራይ ልጅ!
3ኛ አቶ ሣሙኤል አስተርጓሚ የትግራይ ልጅ
4ኛ አቶ ወልደገብርኤል አስተርጓሚ የወሎ ልጅ
5ኛ አቶ ሞአሊም ማቴ አስተርጓሚ የወሎ ልጅ
6ኛ አቶ መሐመድ ሰይድ አስተርጓሚና ተላላኪ የወሎ ልጅ
7ኛ ልጅ አብተው አስተርጓሚ የጎጃም ልጅ
8ኛ ደብተራ ደስታ አስተርጓሚ የጎንደር ልጅ ናቸው::

በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን 3 ቋንቋዎች የሚያስተረጉሙ ሲኖሩ ኋላ ደግሞ ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን የጎንደር ልጅ ከሕንድ ተምረው መጥተው ነበር:: እርሳቸው በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን የሠሩት ነገር ግን አልነበረም:: ሌሎች ግን ከላይ እንደተጠቀሰው ብዙ አገልግሎት ለአገራቸው አበርክተዋል::

ታሪክ ለወደፊቱ ሲያስታውሳቸው ይኖራል:: በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ዓለም አጨዋች ማለትም (አዝማሪ) ነበሩአቸው:: በጣም ታዋቂ ከነበሩት መካከል ድምጻዊ አብተው ይባሉ ነበር:: ሌላም ድምጻውያን መሰንቆና ክራር የሚጫወቱ አብረዋቸው ነበሩ::



# ምዕራፍ 3

## አጤው ለእድገት ሲሯሯጡ መኳንንቱ አፈንገጡ!

ስማቸው ያልታወቀው የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት ገጽ 18 "በአጤ ቴዎድሮስ ጊዜ የነበሩ ሽፍቶች በጎጃም ተድላ ጓሉ፤በደንቢያ እስከ ወልቃይት ጋረድ ከንፉ፤በትግሬ አገው ንጉሤ እኒህ ሦስቱ በርትተው ነበር:: በየስፍራቸው ሁነው የጎጃም የተድላ ጓሉ ጥፋት ተድላ ጓሉ ጅበላ ከሚባለው አምባ እየገባ ብዙ ቀን አስቸግሮ ነበር:: ንጉሡ ሲመጡበት ወደ አምባ ይገባል:: ንጉሥ ሲመለሱ አገር ያጠፋል ሁል ጊዜ ንጉሥን ያናድዳቸው ነበር" ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስ ጎንደርን ትግሬንና ወሎንና ሸዋን ጎጃምን አንድ አድርገው ማስተዳደር ሲጀምሩ በጎንደር የሸፈቱት የትልቅ ወንድማቸው ልጅ ደጃዝማች ጋረድ ከንፉ ኃይሉ ነበሩ:: የእንግሊዝን ቆንሲል አቶ ፕላውዴንና ዮሐንስ ቤልን የገደለው የአጤው የወንድም ልጅ ናቸው::

እርሳቸውም የደጃዝማች ጋረድን ወታደር ቀጡአቸው:: የተማረኩትንም ያለምንም ምሕረት ጨርሰዋቸዋል:: ጭካኔው ሊበዛባቸው የቻለው ሁለቱ የውጭ አገር ዜጎች በመገደላቸው ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል አዋጅ ሲታወጅ አብረው የነበሩ በመሆናቸው ጭምር ነው::

ስማቸው ያልታወቀው የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት ገጽ 21 "ጋረድ ከንፉ የአጤ ቴዎድሮስ የወንድም ልጅ ነው:: ጋረድ ከንፉ አጤ ቴዎድሮስን ከድቶ ብርቱ ሽፍታ ሁኖ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: የወንድማቸው ልጅ መሆኑን አልቃሽ ስትገልጽ "ጋረድ እንኳን ሞተ እንኳን ተቀበረ ወንድምህ ነው ብለን እንፈራው ነበረ" ብላለች::

ከደጃዝማች ጋረድ ቀጥሎ አገር ለመሸጥና ለመከፋፈል የተነሡት ደጃዝማች ንጉሤ ናቸው፡ እርሳቸው የፈጸሙትን ክህደት አስመልክቶ ራሱን የቻለ ምዕራፍ አለው:: ታዲያ አጤ ቴዎድሮስ ወደ ትግራይ

እንዳይዘምቱባቸው ስለፈለጉ የሚያስወሩት ወሬ ነበር። ያም ወሬ "አንድ ታላቅ አባት እርስዎ ተከዜን ሲሻገሩ ይሞታሉ ብሎአል ብላችሁ ንገሩአቸው" አስብለዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ወደ ትግራይ ሊሔዱ ሲነሡ ወታደሩ ፈራ። ታዲያ አባ ታጠቅ ሃይማኖት ያላቸው በመሆናቸው ይህን የጠንቋይና የደብተራ ሴራ ሊበጥሱት በማሰብ ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ተጓዙ።

<u>አባ ታጠቅ ካሳ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 104 "እንዲሁ በትግሬ በኩል የነበሩት ጠላቶቻቸው በወሎ፤በሸዋ ቢጎጃም ያሉትን ወንበዴዎች ለማጥቃት በሚራወጡበት ወቅት አላደርሳቸው ስለአለ ወደ ትግሬ ፊታቸውን ሳያዞሩ ብዙ ዓመታት መቆየታቸው ይታወቃል። ከዚህም የተነሣ ጠላቶቻቸው ተከዜን አይሻገሩም የተሻገሩ እንደሆን ይሞታሉ የመንግሥታቸው ፍጻሜ ይሆናል እያሉ ያስወሩ ጀመር።"

"በመካከልም አባ ታጠቅ የትግሬን ሸፍቶች ለመቅጣት የሚጓዙበት ጊዜ ሆነና በሰሜን አድርገው ወደ ትግሬ ሲጓዙ ተከዜ ደረሱና ከወራጁ ውኃ በጎሽ ዋንጫ አስጠልቀው ከጠጡ በኋላ አዝማሪ አብተውን አስጠርተው እንዲህ በል እያሉ ግጥም ይሰጣሉ።"

"የዓባይን ውኃ በቅል ይጠጡታል
የተከዜን ውኃ ለምን ይፈሩታል?
ሲሉ ትግሮች ለገጠሙት መልስ ሲሰጡ ከዚህ የሚከተለውን ያዘምራሉ።
ተከዜን ሲሻገር ይሞታል የሚሉ
መጽሐፉ ታጠበ ያባይ ጠንቋይ ሁሉ
ወርሒን ስንደግመው እንግዲህ ምን ይሉ
ወርሒን ማለትም በትግሬ የሚገኝ አንድ ትልቅ ወንዝ ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

<u>ስማቸው ያልተጠቀሰው የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት</u> ገጽ 27 "ደጃች ንጉሤ ጥቂት በጥቂት ወታደር ሰበሰቡ ደጃች ኃይለ ማርያም የትግሬ ገዥ ነበሩና ከአገው ንጉሤ ጋር በሐውዜን ወገን ሀራሀር በሚባል ስፍራ ገጠሙ እጅግ ብርቱ ጦርነት ተዋግተው በዝያን ጊዜ ደጃች



ኃይለ ማርያም ሞቱ" ይሉና ገጽ 28 "አጤ ቴዎድሮስም እንደ መብረቅ ከሸዋ ሌትና ቀን ገስግሰው በ16 ቀን ሸዋ ናቸው ብለው ሳለ የመይሳው ልጅ ተምቤን ዱብ አሉባቸው።"

"የአገው ጦርም አንድ ጠበንጃ ሳይተኩስ አንድ ጦር ሳይወረውር ሁሉ ተያዙ እኩሉም ጌታውን እየጣለ ወደ አድዋም ወደ አክሱምም ገዳም ገባ ደጃች ንጉሤና ደጃች ተሰማም ያንጊዜው ተያዙና 2እግራቸው 2እጃቸውን ጎምደው አሞራና ጅብ በላቸው"በትግሬ በፊት ደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤል ከሮማ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር በገቡት ውል መሠረት የባሕር በር ሊሰጡ መስማማታቸውን አጤ ቴዎድሮስ ሰምተው በረው ሲደርሱ ደጃዝማቹንና ተባባሪያቸውን ሲደመስሱ ሌላው "ባሳደኩ እጄን ተነከስኩ" እንደተባለው ያሳደጓቸው ደጃዝማች ካሣ ምርጫ ሸፍተው ረበሹ።

ምንም እንኳን የየራሳቸው ምዕራፍ ቢኖራቸውም የደጃዝማች ንጉሤና የደጃዝማች ካሳ ምርጫ አገር ለማፍረስ ከተዘጋጁት ግንባር ቀደም መኳንንቶች መካከል ዋናዎቹ ናቸው። ለዚህ ማስረጃ ከምዕራፉ ስትደርሱ ትመለከቱታላችሁ። አሁን በሌሎች መኳንንቶች ላይ ባለው ባይበዛም አጠር ብሎ መግለጥ ስላለበት ወደ ሌሎች ልመለስ። በጎጃም ደጃዝማች ተድላ ጓሉ፤ የታወቁ ይሁን እንጂ ሌሎች ብዛት ያላቸው መኳንንቶች በአጤ ቴዎድሮስ ላይ መሸፈታቸው አይዘነጋም።

ለምሳሌ ደጃዝማች ብሩ ኃይሉ ለአጤ ቴዎድሮስ አልገብርም በማለታቸው አጤ ቴዎድሮስ ከአዘዞ ማክሰኞ ተነሥተው እረቡ እንጀበራ በመድረስ ደጃዝማች ብሩ ኃይሉን ድል አድርገዋቸዋል። በመጀመሪያ ደጃዝማች ተድላ ጓሉ ወደ አጤ ቴዎድሮስ መግባታቸውና ኋላም ታማኝ የነበሩ መሆናቸው አይዘነጋም። ነገር ግን አብረው ከጎንደር ወደ ወሎ ዘመቻ ከሄዱ በኋላ መክዳታቸው ታውቋል።

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 213 "ደጃዝማች ተድላ ወዳ አጤ ቴዎድሮስ ገብተው የአባታቸውን ግዛት ከአስመረቁ ወዲህ ንጉሡ ለዘመቻ ወደ ሸዋ ሲጓዙ ከወሎ ከድተው ወዳገራቸው ወደ ጎጃም ተመልሰው ሸፈቱ። ለመሸፈት

ካበቃቸው ምክንያት አንዱ ምናልባት የሸዋው ንጉሥ ኃይለ መለኮት ጦራቸው የማይደፈር ስለሆነ ቴዎድሮስ እዚያ ተሸንፈው ወይም ደክመው ሲመለሱ እኔ ከዚያ የጎጃምን ጦር ይዤ የደከመውን ጉልበታቸውን ባዲስ ጉልበት ተቀብዬ አሸንፈዋለሁ የማለት ተስፋ ይሆናል" ሲሉ ጽፈዋል።

ደጃዝማች ተድላ ጓሉ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ መሸፈታቸውና አጤ ቴዎድሮስ እልህ አስጨራሽ ጦርነት እንዲያደርጉ አስገድደዋቸዋል። አጤ ቴዎድሮስም ተከታትለው ተራራ ለተራራ ሲያናውዟቸው ኑረዋል። አጤ ቴዎድሮስ ደጃዝማች ተድላ ጓሉን ለመቅጣት ሲሉ አልባሌ ሰው ሁነው ከሕዝብ መካከል ገብተው ወሬ እስከመሰብሰብ ደርሰው ነበር። በደጃዝማች ተድላ ጓሉ ምክንያት ያለፈላት መነኩሴ ነበረች። ከላይ እንደተባለው አጤ ቴዎድሮስ ከሸዋ ወደ ጎጃም ሲመለሱ ደጃዝማች ተድላ ጋር ጦርነት ከፈቱ።

<u>አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 101 "አጤ ቴዎድሮስ ሸዋን ወግተው ወደ ጎንደር ለመመለስ ዓባይን ሲሻገሩ ተድላ ጓሉ ከመንቆረር ወጥተው ከምሽጋቸው ገቡ ቴዎድሮስም ጅብላንብሬ ተድላ ጓሉን ሳልይዝ አልሄድም ብለው መንቀረር ላይ ሠፈር አደረጉ። የጅብላ ምሽግም ባለመሰበሩ ቴዎድሮስ በአገሩ ላይ ራስ እንግዳን ሹመው ጎንደር ገቡ" ሲሉ ጽፈዋል።

ደጃዝማች ተድላ ጓሉ አጤ ቴዎድሮስ ሲሄዱባቸው አንዴ ተራራ ላይ በሌላ ጊዜ ደግሞ በርሃ እየገቡ ሲያስቸግሩ ኑረው በኅዳር 6 ቀን 1860 ዓም አጤ ቴዎድሮስ ከመሞታቸው በፊት አስቀድመው እርሳቸው ሞቱ። በወሎ ደጃዝማች ዋግሹም ጎበዜና ደጃዝማች አመዴ በሽር፣ ወይዘሮ መስታይትና ወይዘሮ ወርቂት፣ሌሎችም መኳንንቶች ለአጤ ቴዎድሮስ አንገዛም ብለው ብዙ ጊዜ ጦርነት ገጥመዋል።

በተለይም ደጃዝማች አመዴ በሽር፣አጤ ቴዎድሮስን ካሰቃዩአቸው መኳንንቶች መካከል አንዱ ናቸው። ደጃዝማች አመዴ በሽር፣ አጤ ቴዎድሮስ ሲደርሱ በቅጽበት እልም ይላሉ፣አጤ ቴዎድሮስ ሰላም ነው ብለው ሕዝቡን ቀጥተው ሲመለሱ ደጃዝማች አመዴ በሽር ከተደበቁበት ወጥተው ይመጣሉ። በደጃዝማች አመዴ በሽር ምክንያት አጤ ቴዎድሮስ ወሎን ቅጥቅጥ አድርገውታል።



ደጃዝማች አመዴ በሽር ወሎን የተለያዩ አውራጃዎችና ወረዳዎችን ሳይቀር እየዞሩ በአጤ ቴዎድሮስ እንዲመቱ አድርገዋል። አጤ ቴዎድሮስ ደግሞ አስቀድመው ያወጡት አዋጅ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ስለፈለጉ በደረሱበት አውራጃና ወረዳ ውስጥ ፍትሐ ነገሥት ተገልጦ ሕግን የሚያውቁ ሊቆች ወስነው የተማረከው ምርኮኛ ሁሉ እንዲገደል ያደርጋሉ።

<u>አባ ታጠቅ ካሳ የቋራው</u> አንበሳ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 128 "አጤ ቴዎድሮስ በኅዳር ወር አገሩ ሁሉ በሽር አመዴን እየረዳ ስለአስቸገራቸው ከጉራምባ ጀምሮ እስከ ገነቴና እስከ ጨለቃ ወንዝ እስከ ሸዋ ደንበር ያለው አገር ሁሉ እንዲመታ አድርገው ብዙ ሕዝብ አለቀ፤ ብዙ ንብረት ተዘረፈ። በወረራው ሽብር በየመንደሩ ወድቀው ሲንገላቱ የተገኙትን ሕፃናት አሰባስበው ለመኳንንቶቻቸው አሳድጉ እያሉ ሰጥተዋል" ይሉና።

ገጽ 136 "አመዴ በሽር እንደተለመደው ሸሽቶ ሲያመልጥ ደጃዝማች ትኩ ብርሌን ግን ሁለቱ ልጆቻቸው ጦርነት ገጥመዋቸው ሲዋጉ አንዱ ልጃቸው በጦር ወግቶ ማረካቸው። ወዲያውም አባታችንን ወግተን ማርከናቸዋል ሲሉ ለንጉሠ ነገሥቱ የምሥራች ልከውላቸዋል። አጤ ቴዎድሮስም ከወላጅ አባታቸው እኛን ቢወዱ አይደለም ወይ እንደዚህ ያለ ጀብድ መሥራታቸው በማለት ከተደነቁና ከአመሰገኑ በኋላ ግዛቱን ለሁለቱ ወንድማማቾች አካፍለው ሰጥተዋቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል።

ወቅቱ አንድነት የሚፈልግና አንድነትን የማይፈልግበት ዘመን በመሆኑ ከአባታቸው ጋር እስከ መዋጋት ደርሰዋል። አጤ ቴዎድሮስ በእንዲህ ባለው ወቅት የማረኩትን ሕዝብ ቢገድሉ በእውነቱ ተጠያቂው ማን ሊሆን ነው? ይህን የሕዝብ እልቂት እንዲደርስበት ያደረጉት እንደ ደጃዝማች አመዴ በሽር ዓይነት መሳፍንትና መኳንንቶች ናቸው።

ደጃዝማች አመዴ በሽር ባይሸፍቱና ሕዝቡን ከእርሳቸው ጋር ባያሳምጹት ኑሮ ይህ ቅንና ደግ ሕዝብ በአጤ ቴዎድሮስ ስቃይ አይደርስበትም ነበር። እንኳን ቀደም ዛሬም ቢሆን አንዳንድ አፈ ጮሌዎች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ሕዝቡን ማሳመጽ ተግባራቸው

ሆኖአል። እነዚህ በዘመነ መሳፍንት ወቅት የነበሩት መኳንንቶች ደግሞ በሽፍትነት የዳበሩ ነበሩ። ለዚህ ሲሉ ሕዝቡን ቀስቅሰውና አስነሥተው ጦርነት ሲገጥሙ የሚያልቀው ሕዝቡ ነው።

ጦርነት በሚደረግበት አካባቢ ሁሌም ሕዝቡን ይጎዳል። ይህ ጸሐፊ በ1971 ዓም አርማጭሆ 21 ቀን ሙሉ የተመለከተውን ጦርነት አይረሳውም። በዚህ ጦርነት የሁለት ወረዳ ሕዝብ ሲሰደድና ተባሯሪ ጥይት ሲመታው ተመልክቷል። የደርግ ጦር ቤቱን ሲያቃጥለው እህሉ አብሮ ተበልቷል።

ሕዝቡ የቅጠል ጎጆ ሠርቶ በብርድና በዝናብ ከርሟል። ይህን ያደረጉት ድርጅቶች ሲጠቁ ወደ ሱዳን ሄዱ። ሕዝቡ ግን ከሞት የተረፈው ችግሩን ሲጋፈጥ ከረመ። በአጤ ቴዎድሮስም ዘመን የዚህ ዓይነት ችግር በሕዝቡ ላይ እንደደረሰበት ማገናዘብ ይቻላል። ታዲያ ይህን ሕዝብ ያስጨረሱት መኳንንቶች ራሳቸው ናቸው ማለት ይቻላል። አጤ ቴዎድሮስ ከወሎ ወደ ሸዋ ዘመቱ። ምክንያቱም አቶ ሰይፉ በመሸፈታቸው ምክንያት እርሳቸውን ለማስገበር ሄዱ።

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 138 "አጤ ቴዎድሮስ የአቶ ሰይፉን መሸፈት ስለሰሙ ልጃቸውን ደጃዝማች መሸሻን ራስ ውቤን አቡኑን ዕጨጌውን ካህናቱን የአደባባይ ኢየሱስን የግምጃቤት ማርያምን ጽላት የያዙትን ሥዕል ቤቶችን በጠቅላላው የቤተመንግሥቱን ዕቃና ጓዝ መቅደላ አምባ ውስጥ አግብተው ደረቅ ጦር ሁነው በ1852 ወደሸዋ ገሠገሡ ሰላ ድንጋይ በደረሱ ጊዜ ወታደር ሳይታዘዝ አገር በመዝረፉ ሠላሳ ሰባት ወታደሮች እጅ እግራቸውን አጥተዋል። ከተንታ በተነሡ በስምንት ቀን አንኮበር ደረሱ።"

"ከዚህም ላይ ጥቅምት ሁለት ቀን በተደረገው ጦርነት ከንጉሡ ወገን የጦር አለቃ ተማርኮ ወደ አቶ ሰይፉ ቀረበ እርሳቸውም ይህ አሁን የሚዋጋው ጦር የማን ነው አንተስ የማን ነህ ብለው ጠየቁት ምርኮኛውም እንዴት አላወቁትም አጤ ቴዎድሮስ ናቸው እኮ ብሎ በነገራቸው ጊዜ ጦርነቱን አቋርጠው ሠራዊታቸው ሳይሰማ በስውር ሸሹ ጦሩ ግን ከጧት የጀመረ እስከጨለማ ድረስ አላስገባም በማለት በቅጥር ውስጥ እንዳለ ሆኖ የሰይፉን መሸሽ የማያውቅ ወታደራቸው ጃንሆይ ጃንሆይ እያለ ሲጮህ አጤ ቴዎድሮስ ሰምተው ሠራዊቱን



ግባበት እያሉ በማደፋፈር ወደፊት ስለገፋበት ቅጥሩን እያፈረሰ ገባበትና የአንኮበር ጦርነት በዚህ ዓይነት ተፈጸመ" ሲሉ ጽፈዋል።

እንዲህ ባለ ጦርነት ድል አድርገው አደላድለው ቢመለሱም ሸዋ ከመሸፈት አልዳነም። ከዚያም በኋላ በ1857 ዓም አጤ ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ከትውልድ አገራቸው ሲገቡ ተከታዮቻቸውን አብዝተው ነበሩ።

በጎንደር ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜ፤ የወልቃይት ተወላጅ ናቸው። አልገብርም ብለው በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ሸፈቱ። አጤ ቴዎድሮስም እንደ ደጃዝማች አመዴ በሽርና እንደ ደጃዝማች ተድላ ጓሉ ጠንክረው ባይዘምቱባቸውም በተደጋጋሚ ደብድበዋቸዋል። ነገር ግን እንኳን ያኔ ዛሬም ቢሆን ወልቃይት ጠገዴ በርሃው ከባድ በመሆኑ ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜ አጤ ቴዎድሮስን ሊያመልጡ ችለዋል።

ውለው አድረው የአጤ ቴዎድሮስ ኃይል እየቀነሰ እርሳቸው ሙሉ በሙሉ ፊታቸውን ወደ እንግሊዝ ጦር ሲያዞሩ ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜ ጎንደርን ይዘው ፊታቸውን ወደ ወሎ አዙረው ነበር። ከዚህ ላይ ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜን እንግሊዞች መሸፈታቸውን ማወቃቸው እንጂ ደብዳቤ ይላኩላቸው አይላኩላቸው የሚያብራራ ሰነድ ሊገኝ አልቻለም። በእንግሊዞች ግን መታወቃቸው አልቀረም። ያም ሆነ ይህ ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜ ለመንገሥ ጥረት አድርገዋል። ባልታሰበ ሰዓት ደጃዝማች ዋግ ሹም ጎበዜ፤ በለሳ ላይ ሚያዝያ 1860 ዓም ወግተው ገደሏቸው።

<u>ሐሌፍ መጽሔት</u> ቁ 1 ነሐሴ 1984 ዓም ገጽ 18"አንዳንዶቹ የሥልጣን ርክክቦሽ ጦርነቶች አጭር አንዳንዶቹም ረዥም ናቸው። በጣም ወደኋላ መሄዱን ትተን የዘመነ መሳፍንትን ፍጻሜ ለማምጣት ከተደረገው ጀምሮ ያለውን በምሳሌነት እንይ! የዘመነ መሳፍንትን አገዛዝ አስወግዶ አንድ ኢትዮጵያና ማዕከላዊ መንግሥት እንደገና ለማምጣትና ለማጠናከር መይሳው ካሣ አጤ ቴዎድሮስ ከመባላቸው በፊት ጀምሮ እስከ ለተ ሞታቸው ድረስ ጦርነት ያላካሄዱበት ዓመት አልነበረም። በተለይም በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን የነበረው ጦርነት ከባድ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

መቅደላ ታስረው የነበሩት የውጭ አገር ሰዎችና ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ የሆነ በአገር ላይ በደል አድርሰዋል:: በተለይም የአቡነ ማቲያስ ተባባሪዎች አንዳንድ የበስማም ቄሶች::

<u>የእሥራት ዘመን በአበሻ አገር</u> መጽሐፍ ገጽ 174 "ኅበዜ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ከአቡኑና ከራሳም ጋር ግንኙነት ስለነበራቸው የ1859 ክረምት ከመግባቱ በፊት መቅደላን ለመያዝ መምጣቴ ነው ሲሉ ለአቡኑ መልክትና ጥቂት መቶ ብር ልከው አቡኑን በሚቻላቸው ሁሉ እንዲረዷቸው ስለጠየቁ አቡኑም አምባውን ለመያዝ ከመጡ በሚቻላቸው ሁሉ እንደሚረዷቸው ሙሉ ተስፋ ሰጥተው ላኩባቸው" ይሉና::

"አቡኑ አምባውን ለመያዝ የነበራቸው እቅድ ወዲያውኑ የሚተማመኑባቸውን ሰዎች መርጠው መሣሪያ ለእኛ ሊልኩልንና እኛም በአሽከሮቻችን ርዳታ የታሰርንበትን እግረ ሙቅ ፈትተን ለምናምናቸው አሽከሮቻችን የጦር መሣሪያ አድለን መደራጀታችንን ለአቡኑ ስናስታውቃቸው የክህነት ልብሳቸውን ለብሰውና::"

"መስቀላቸውን ይዘው 200 በሚሆኑ ቀሳውስትና ደብተራዎች ታጅበው ሊወጡና በግልጽ አጤ ቴዎድሮስንና የሚከተላቸውን ሁሉ አውግዘውና ገዝተው አሁንም ሠራዊቱ ታማኝነቱን ለቴዎድሮስ እንዳያደርግ ለመስበክ ሲሆን እኛም ከፖርቱጋሎቹና ከታማኞቻችን ጋር ቁጥራቸው 65 ስለሚሆን::"

"አቡኑም አምሳ የሚሆኑ የታመኑ ተከታዮች ስለማያጡ ሁለት መቶ የሚሆኑ ቀሳውስትና ደብተራዎች ጭምር በማሰለፍ ሁኔታውን ግራ አጋብተን ከወዲያም በኩል የሚንቀሳቀስ ሰው ቢኖር ያለምሕረት ለመምታትና ካስፈለገም በመጀመሪያው በር ቀሳውስቱን አሰልፈን የውጩን በር እኛ የኅበዜ ሠራዊት ደርሶ አምባውን እስከ ያዘ ድረስ ለመከላከል ነበረ" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህ ወጥቶ የነበረው እቅድ በአቡነ ሰላማ እና በደጃዝማች ዋከሹም ኅበዜ ገብረ መድኅን እና በአውሮፓውያን ሰዎች ነበር:: ሁኔታው ግን ሳይፈጸም ቀርቷል::



# ምዕራፍ 4

## የደጃዝማች ንጉሤ መሸፈትና አገር መሸጥ!

<u>ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ</u> ሊትማን ያሳተመው ገጽ 26 "አገው ንጉሤ የትግሬው ሽፍታ" ሲሉ ጽፈዋል:: ደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤልን አስመልክቶ ብዛት ያላቸው ደራስያን ሙሉ በሙሉ የትግራይ ተወላጅ ያደርጓቸዋል:: አንዳንዶች ደግሞ አገው ንጉሤ በማለት ይጠሩአቸዋል:: አገው ንጉሤ የሚባሉበትን አስመልክቶ ግልጽ የሆነ ሰነድ ላገኝ አልቻልኩም:: በወቅቱ ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ከነበሩት ደራስያን መካከል አለቃ ዘነብ ከላይ እንደተጠቀሰው "አገው ንጉሤ የትግሬው" ሲሉ ጽፈዋል::

<u>ስማቸው ያልታወቀው የቴዎድሮስን ታሪክ</u> የጻፉት ገጽ 27 "አገው ንጉሤ አገው ተሰማ ሲባሉ የነበሩ ሁለቱ ደጃች ንጉሤ ደጃች ተሰማ ተባሉ፤ጠቅልለው ትግሬን ያዙ" ሲሉ ወንድማቸው ደጃዝማች ተሰማን ሳይቀር አገው ተሰማ ብለው ጽፈዋል::

ደጃዝማች ንጉሤ አንዳንድ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ትግሬ ናቸው ይላሉ ለዚህም ተጨባጭ አድርገው የሚወስዱት የካቲት 3 ቀን 1845 ዓም ደጃዝማች ካሣና ደጃዝማች ውቤ የተዋጉ እለት አብረው ሲዋጉ የተማረኩ ናቸው:: አንዳንዶቹ የሚሉት ትግሬን የሚገዙት ደጃዝማች ውቤ ስለነበሩ ደጃዝማች ካሣ ደጃዝማች ውቤን ሊወጉአቸው ወደ ደረስጌ ሲያመሩ ደጃዝማች ንጉሤ የትግሬን ጦር ይዘው መጥተው ደጃዝማች ውቤ ጋር ሁነው ሲዋጉ የተማረኩ ናቸው ይላሉ:: በእርግጥ የትግሬ ተወላጅ ካልሆኑ ከአጤ ቴዎድሮስ ሲሸፍቱ ትግራይ ሊገቡ አይችሉም::

ዶ/ር ኃይሌ ወልደ ሚካኤል <u>አብሮነት በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 113 "የትግሬው አገው ንጉሤ" ይላሉ:: ይህ ታሪክ በተለያዩ መጻሕፍት የተጠቀሰ ሲሆን ከፍ ብየ ሆነ ዝቅ ብዬ የምገልጻቸው የታሪክ መጻሕፍት ደጃዝማች አገው ንጉሤ በአብዛኛው የትግራይ ተወላጅ መሆናቸውን ያብራራሉ:: ስለዚህ ደጃዝማች

ንጉሤ ወልደ ሚካኤል አንድም ሁለትም የሌለበት የትግራይ ባላባት ናቸው። እስኪ ሌሎችን የታሪክ መጻሕፍት ከዚህ በታች እንመልከት።

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 76“ ንጉሡ ለኢትዮጵያም ለቤተ ክርስቲያንም ያሰቡት አሳብ ከግቡ እንዳይደርስ በጎጃምና በሰሜን የነበሩ እንደ ደጃች ንጉሤ ያሉ ጠላቶቻቸው የካቶሊክ እምነት ተከታይ ከሆነው ኢትዮጵያዊ ከሚባለው ሕዝብ ጋር ከኢጣሊያና ከፈረንሳይ መንግሥት ወኪሎች ጋር እየተመሣጠሩ ትግላቸው ፍጻሜ እንዳያገኝ ያውኳቸው ነበር” ሲሉ ጽፈዋል።

<u>የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 267 “የትግራዩ ደ/ች ንጉሤ ወ/ሚካኤል አገው ንጉሤ ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር ሀገር ቆርሶ የመሸጥ ውል መዋዋላቸውን አጤ ቴዎድሮስ ሲሰሙ ውሉ በተግባር ላይ ሳይውል ቶሎ ለማጥፋት በፍጥነት ተጉዘው ትግራይ ገቡ። በዚያም አገው ንጉሤ ለፈረንሳይ ዕውቅና ለመስጠት የፈረንሳይን ባንዴራ በአድዋ ከተማ አውለብልበው ነበር።”

“ውሉ የፈረንሳይ መልእክተኞች በቀይ ባሕር ዳርቻ በዙላና በአንፊላ መሀል ያለውን አዳዳ የተባለውን ቦታ እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ በደጃ/ች ንጉሤ ተወክለው ሙሉ ሥልጣን የጨበጡት አባ እምነቱ የተባሉ ሲሆኑ የፈረንሳይ ተወካይ ደግሞ ከአድዋ ሾልኮ ወደ ምጽዋ ሲገባ የፈረንሳይ መንግሥት ዙላንና የዲሲን ደሴቶች ጭምር ከዊዳ እስከ ዘይላ ድረስ ያለውን የኢትዮጵያን ቀይ ባሕር እንዲይዝ የሚል ውል ተዋዋሉ። ከዚህ የውል ስምምነት 5ኛው አንቀጽ ይህ የሰጠኋችሁ ስጦታ ለፈረንሳይ ንጉሥ እስከ ልጅ ልጅ ድረስ ጸንቶ ይቆያል የሚል ነበር። ሆኖም አጤ ቴዎድሮስ ትግራይ እንደገቡ አገው ንጉሤን በማሸነፍ ውሉ በሥራ ላይ ሳይውል አጨናግፈውት የፈረንሳይን መንግሥት የኃፍረት ሸማ አከናንበው ሰደዷቸው” ሲሉ ጽፈዋል።

ዶ/ር ኃይሌ ወልደ ሚካኤል፣ <u>አብሮነት በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 113 “ጌደን የነበረው የፈረንሳይ ቆንስል ላምበርት፣ አቦከን ገዛና በሸዋ ንግድ ላይ ያነጣጠረ ውል ተፈራረመ። ውሉ



ተጨባጭ ውጤት አልነበረውም። ይበልጥ አጤ ቴዎድሮስን ያበሳጫቸው የትግራዩ አገው ንጉሤ የአፋር ባሕር በር የተሰኙትን ዙላን፣አምፊሎን ሃውኪልን ወዘተ ለአጤ ናፖሊዮን ግልባጭ መስጠቱንና ካቶሊክ የሆኑትን አቡነ ጃኮቢስን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሪ ለማድረግ መዋዋሉ ነበር” ሲሉ ጽፈዋል።

ደጃዝማች ንጉሤ ከአጤ ቴዎድሮስ ሸፍተው በትግራይ ራሳቸውን አንቱ ብለው መኖር ጀመሩ። እኚህ ሰው መሸፈታቸው ብቻ ሳይሆን የአገራቸውን ዳር ደንበር ቆርሰው ለፈረንሳይ መንግሥት ለመሸጥ መስማማታቸው ነበር አጤ ቴዎድሮስን ያናደዳቸው። ደጃዝማች ንጉሤ ከፈረንሳይ እና ከጣሊያን መንግሥት በተለይም ከሮማ ቤተ ክርስቲያን ጋር መላላስ ጀመሩ። የሚገርመው ነገር ደግሞ ደጃ/ች ንጉሤ ለፈረንሳይ መንግሥት የላኩት ደብዳቤ አሳዛኝ ነው። ሊነግሥ አገር ሊመራ የፈለገ ሰው የራሴን ግዛት ከፍዬ ልስጣችሁ መጣሪያ ስደዱልኝ የሚል አገር ሊያስተዳድር አይችልም። እስኪ ለንጉሥ ናፓሊዮን የጻፉትን ደብዳቤ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አንብቡት።

ደብዳቤ ቁጥር 1 “ሰኔ 2 ቀን 1848 ዓም አባቴ ይሁኑ እኔም ልጅዎ እሆናለሁ። አሁን አንድ ሽፍታ ንጉሥ ተነሥቶ እኔን በማጥፋት ላይ ነው። ክርስቲያኖችንም እያጠፋ ነው። እንደ እውቅትዎ ይርዱኝ። ቢቻል በነሐሴ ባይቻልም በመስከረም እስከዚያም እቆያለሁ ከወዲያ ወዲህ እያልኩ። አቡነ ያዕቆብን አባቴ አድርጌአለሁ። የእርስዎንም ፈቃድ የማልጥስ ነኝ” ሲሉ ጽፈው ነበር። በነገራችን ላይ ሽፍታ ማለት አገሩን ለማስከበር የተነሣን ሳይሆን የሰው ንብረት የሚዘርፍ መሆኑን ደጃዝማች ንጉሤ አልተረዱትም።

መርዕድ ወልደ አረጋይ <u>KASA AND KASA</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 85 “በቆየው የኢትዮጵያ ፊውዳላዊ ባህል ሽፍታ ሆኖ ዱር የሚገባ ሌብነትና ቅሚያ ያማረው አልነበረም። ሽፍትነት የጨዋ ልጅ ማኩረፊያ ስለነበር ጫካ የሚገባው አብዛኛውን ጊዜ የሚፈልገውን ወይም የሚገባውን ሹመትና ጉልት አለማግኘቱን የሚገልጽበት ዘዴ ነበር” ሲሉ ጽፈዋል።

ስለዚህ ቀደም ሲል ደጃዝማች ንጉሤ የጻፉትን ደብዳቤ የተመለከቱ ሰፈርተኛ ደራስያን ሁሉ አጤ ቴዎድሮስን “ሽፍታ”እያሉ የጻፉ ትክክል አይደሉም። ለወደፊቱም ማረም ያስፈልጋል ማለት ነው።

ሽፍታ ማለት የሰው ንብረት የሚዘርፍ ዓላማ የሌለው የግል ጥቅም ለማከማቸት የተነሣ ማለት ነው:: ወደ ደጃዝማች ንግሤ ደብዳቤ ልመልሣችሁ::

ደብዳቤ ቁጥር 2 "ጥቅምት 22 ቀን 1851 ዓም የአገሬን ነጻነት እንዲጠብቁልኝ እለምናለሁ ከዘራፊውና ከዓመጸኛው ከቴዎድሮስ እጅ ይጠብቁኝ:: ይህንንም ለማድረግ ሁለት ነገሮች ያስፈልጉኛል:: መጀመሪያ ከናንተ ተወካይ ቢላክ ከዚህ በፊት እንደጠየቅሁት ይህ በአገሬ ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ እንዲመለከት እሱንም በአገሬ እንደራሴ አድርጌ እጠብቀዋለሁ:: የፈረንሳይን ባንዴራ እተክላለሁ:: ሁለተኛ የምፈልገው ሁለት መድፎች ከተኳሾቻቸው ጋር ..ነው:: ለአደረጉልኝና ለአገሬም ለሚያደርጉት እርዳታ ከባሕር ዳር ዳርቻ ራስ ዱሜራ የሚባል ዙላን እሰጥዎታለሁ" ሲሉ ደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤል ጽፈዋል::

ደጃዝማች ንጉሤ አንድ የትግራይ ታዋቂ ባላባት ልጅ ጠጋዬ ሳይቀር ወደ ሮም ሲልኳቸው በመጀመሪያ ፓሪስ ከናፖሊዎ ጋር ግንኙነት አድርገው ከሰነበቱ በኋላ ወደ ሮም ሄዱ:: ሮም እንደደረሱ ከፓፓ ፒዮስ ዘጠንኛ ሁለቱ በመገናኘት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን በትግራይ ማስፋፋት እንደሚቻል ተወያይተዋል:: እርሳቸው መልእክት አድርሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ የተሳፈሩባት መርከብ ማዕበል ሲወስዳት ከአንድ ደሴት ጣላቸው::

ልጅ ጠጋዬ ብቻቸውን ሲንከራተቱ ረኃብና ውኃ ጥም ገድሏቸው ላሞራ ቀለብ ሁነዋል:: አቶ ጋብር የተባሉት ግን ከ8 ቀን በኋላ ወደስዊዝ የሚያልፍ መርከብ ስላገኙ ነፍሳቸው ልትተርፍ ችላለች:: አባ እምነቱ የተባሉት ከሌሎች ሦስት የካቶሊክ መነኮሳት ጋር ለብቻቸው ሲንከራተቱ ሰንብተው አልፎ ሀጅ መርከብ አግኝተው ከሞት ተርፈው ወደ ደጃዝማች ንጉሤ ለመድረስ ችለዋል::

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 146 "በ1850 ዓም መልእክተኞች ወደ አውሮፓ ለመሄድ ከምፅዋ ተነሡ::ለጊዜው ወደስዊዝ የሚያልፍ መርከብ ባለማግኘታቸው በዓረቦች የንግድ ጀልባ ተሣፍረው በቀጥታ ወደጅዳ ተጓዙ:: ከዚያም ወደስዊዝ አለፉ:: ስዊዝም በደረሱ ጊዜ አባ ያዕቆብ በዚህ አገር ለሚኖሩ አላዛሪስት ሚሲዮን ጽፈውላቸው ስለነበር በእንግድነት



ተቀብለዋቸው ጥቂት ጊዜ ካረፉ በኋላ በሌላ መርከብ ተሣፍረው በመጓዝ ሮማ ደረሱ:: ሮም እንደደረሱም የማስታወቂያ ሚኒስትር ከነበረው ከካርዲናል ቦርናንዶ ጋር ተገናኙ::"

"ከእነሱም ጋር አማርኛና ዓረብኛ የሚያውቀው ጁስፔ ሳፔቶ የተባለው ቄስ ስለተገኘ አስተርጓሚ ሆነ:: ጥር 18 ቀን 1851 ዓም ከፒዮስ 9ኛ ጋር በካርዲናሉ አቅራቢነት ተገናኙ፤አባ እምነቱ የተባለው መነኩሴ ከደጃዝማች ንጉሤ የተነገረውን መልእክት ከደብዳቤው የተረፈውን በጁሴፔ ሳፔቶ አነጋጋሪነት ደኅና አድርጎ አስረዳና ጁሴፔ ሳፔቶ በበኩሉ ከእንግዲህ ሐበሻ የሚረዳትን ባታገኝ ወደ ፕሮቴስታንት ወይም ወደ እስልምና ሃይማኖትና አምልኮ መግባቷ ነው ሲል ጨምሮ አሳሰበ" ሲሉ ጽፈዋል::

እነዚህ በጃቸው መጽሐፍ ቅዱስ የያዙ ውስጣቸው ተኩላ የሆኑ የሃይማኖት አስተማሪዎች ደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤልን በማግኘታቸው ተደሰቱ:: የፈረንሳይ ውል የሚዋዋልና የባሕር በር የሚረከብ ቡድን በሩፌል የሚመራ ወደ ትግራይ መጣ:: የፈረንሳይ መንግሥት በኢትዮጵያ ለመግባትና ከደጃዝማች ንጉሤ ጋር መዋዋል አጤ ቴዎድሮስ በሰላዮቻቸው አረጋገጡ:: ቀደም ብሎ አጤ ቴዎድሮስ ደጃች ንጉሤን ለመውጋት ሲዘምቱ ሊያገኙት አልቻሉም ነበር:: ይህ የሆነው የትግራይ መኳንንቶች እየተከላከሉላቸው ነበር:: ኋላ ግን በደጃዝማች ንጉሤ ተግባር የትግራይ ሕዝብ ተከፋ::

አገሩን የሚወደውና ለባዕድ አሳልፎ ላለመስጠት ሲዋጋ የኖረው የትግራይ ሕዝብ ባስነሡት አድማ የፈረንሳይ መንግሥት ከደጃች ንጉሤ ጋር ባደረጉት ውል የኢትዮጵያን ቀይ ባሕር ዳርቻ መሬቶች ተረክበው አጤ ቴዎድሮስ የሚጠፉበትን የጦር መሣሪያ ለደጃዝማች ንጉሤ ለመስጠትና ለማድረስ በሚዘጋጁበት ወቅት አጤ ቴዎድሮስ ደጃች ንጉሤን ድል አደረጉ:: ውሉም ደጃች ንጉሤ ሲሞት አብሮ ሞተ::

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 173 "አገው ንጉሤ እስከሚወድቅበት ቀንና ሰዓት በደመ ነፍስነት የፈጸማቸው ወንጀሎች በንጉሡ ነገሥቱ ሕይወት ላይ የተሰነዘሩ ከመሆናቸውም ይልቅ አገሩን ለውጭ መንግሥታት ለመሸጥ ያደረገው ሙከራ ከባድ ቅጣት እንደሚጥለው ከአጤ ቴዎድሮስ

በሚሰጠው ፍርድ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የኢትዮጵያ ነገሥታት እንደሚያምኑበት በፍትሐ ነገሥት የተደነገገ መሆኑን አውቀን ቅጣቱ በአግባብ የተፈጸመ ነው የሚል የሕሊና ፍርድ እንደሚጣልበት ሕገ መንግሥቱ ያስገድዳል" ሲሉ ጽፈዋል።

እነዚህ የሃይማኖት ሰባክያን ሁሌም ለትውልድ አገራቸው ክብር እንጂ ለሃይማኖቱ ቀናዒ ስላላይደሉ ይዋል ይደር እንጅ በሡልጣን ኢብራሂም የዋህነት አሰብ 12 ኪሎ ሜትር ጋሻ መሬት በመግዛት ጣልያን ጦርዋን ምጽዋ አውርዳ ቀስ በቀስ በኢትዮጵያ ተዘርቶ የልጅ ልጆቻቸው ወያኔዎች ለሥልጣንና ለጥቅም ሲሉ ኢትዮጵያን ያለ ባሕር በር አስቀሯት። እነሆ ዛሬ አገራችን ከደረሰችበት ደረጃ ልትደርስ ቻለች።

# ምዕራፍ 5

## የደጃዝማች ካሳ ምርጫ መሸፈት!

<u>አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ የተወለዱ ለኢትዮጵያ የተሠዉ ንጉሠ ነገሥት ናቸው</u> በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 4 "አጤ ቴዎድሮስ በመኳንንትና በመሳፍንት የተከፋፈለች ኢትዮጵያን የአንድ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ካደረጉ በኋላ ቤተ መንግሥታቸውን ጎንደር አዘዞ ሎዛ ማርያም አድርገው ስለነበር።"

"1ኛ አጤ ምኒልክ ኃይለመለኮት፤
2ኛ ራስ መሸሻ ቴዎድሮስን የመጀመሪያውን ትልቁን ልጃቸውን
3ኛ ራስ ቢተወደድ መንገሻ አትኮምንና
4ኛ አጤ ዮሐንስን ከሌሎች ለኢትዮጵያ ይጠቅማሉ ከሚሏቸው ወጣቶች ጋር መርጠው በጎንደር አዘዞ ተክለ ሃይማኖት ሲያስተምሯቸው ከቆዩ በኋላ ቤተ መንግሥቱ ከጎንደር አዘዞ ሎዛ ማርያም ወደ ደብረ ታቦር ሲዛወር እነዚህን ተማሪዎች ዛሬ ለትምህርት ወደ አውሮፓና አሜሪካ እንደሚላከው ወደ ቋራ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ተልከው ትምህርታቸውን አጠናቀው እንደተመለሱ።"



"አጤ ምኒልክን፤ደጃዝማች ራስ መሼሻ ቴዎድሮስን ደጃዝማች፤ ራስ ቢትወደድ መንገሻ አትክምን ደጃዝማች ሲሉ አጤ ዮሐንስን ባላምባራስ ስላሏቸው በዚህ ተቀይመው ጫካ ገብተው በሽፍትነት ሲኖሩ አጤ ቴዎድሮስ ከእንግሊዞች ጋር ተጣልተው በነበረ ጊዜ ከእንግሊዞች ጋር ውስጡን ተላልከውና ከወደቡ ጀምሮ በመቀበል መንገድ በመምራትና በማስተባበር የኢትዮጵያን ምሥጢር ሁሉ ለውጭ ጠላቶች በመንገር የኢትዮጵያ ዳር ድንበር እንዲደፈር የመቅደላ ቤተ መንግሥት እንዲዘረፍ ተከፋፍላ የነበረች ኢትዮጵያን አንዲት ኢትዮጵያ ያደረጓትን ታላቁንና ጀግናውን አጤ ቴዎድሮስን እራሳቸውን በራሳቸው እንዲገድሉ አስደርገዋል" ሲሉ ጽፈዋል።

ደጃዝማች አባ በዝብዝ ካሳ ምርጫ ከጎንደር ነገሥታት የሚወለዱ ዘመነ መሳፍንቱን ከመሠረቱት ከራስ ስሑል ሚካኤል ዘር የሚመዘዙ ናቸው። ለአጤ ፋሲል 7ኛ ተውልድ በመሆናቸው አጤ ቴዎድሮስ በነገሡበት ወቅት ጎንደር መጡ። አጤ ቴዎድሮስም ከልጃቸውና ከሌሎች የመኳንንት ልጆች ጋር ማሳደጋቸውና ባላምባራስ የሚል ማዕረግ መስጠታቸው አይዘነጋም። ነገር ግን ደጃዝማች ሳይባሉ በመቅረታቸው አኩርፈው ትግራይ ገቡ።"

"ከዚያም ደጃዝማች ካሣ ምርጫ መጠናከር ሲጀምሩ ከላይ እንደተጠቀሰው እንግሊዞች አጤ ቴዎድሮስን ለመውጋት ሲመጡ ቅድሚያ ፈቃደኛ የሆኑት ደጃዝማች ካሳ ናቸው። ይህን ታሪክ የዛሬው የወያኔ ቡድን አይቀበልም። በተለይም እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ንብረት ዘረፉ ሁሉ ታሪክን እየዘረፉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ እየካዱ ናቸው። "ታሪክ ይታመማል እንጂ አይሞትም" እንዲሉ አበው።

ደጃዝማች ካሣ ምርጫ፤ከማንም በፊት ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ግንኙነት ያደረጉና የውጭ መንግሥታት ኢትዮጵያን መጥተው እንዲወሩ ጥሪ ያደረጉ የመጀመሪያው ናቸው። ከእርሳቸው ቀጥሎ በማንኛውም ነገር እስረኞችን ለማስፈታት እርዳታ እንደሚያደርጉ ደጃዝማች ዋግ ሹም ጎበዜ ተጻጽፈዋል። ዛሬ እነ ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ "ንጉሥ ምኒልክ ተባባሪ ናቸው" ያሉት ግን በእውነቱ ከእውነት የራቀ ነው "የአባባን እከክ ወደ እማማ ለከክ" እንዲሉ አበው፡አጤ ምኒልክ እንግሊዞችን መርተው መጥተዋል የተባለው ሐሰት ነው።

ደጃዝማች ካሣ ምርጫ የኋላው አጤ ዮሐንስ ሥልጣን ለማግኘት ሲሉ አገራቸውን ያስወረሩ ከደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤል ቀጥለው ዋና ተወቃሽ ናቸው:: እንግሊዞችም የእርሳቸውን ድጋፍ ባያገኙ ሌላው ቢቀር የእህል ችግር ስለሚያገኛቸው አጤ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ እንኳን ረጋ ብለው የአገሪቱን ቅርሳቅርስ ለመዝረፍ ጊዜ አያገኙም ነበር:: ለዚህ ዋናው ተወቃሽ ለመሆናቸው ደጃዝማች ካሣ ምርጫ ከእንግሊዝ ጦር አዛዥ ጋር የተነሡት ምስል ፎቶ ዋቢ ምስክር ነው::

ዶ/ር ተወልደ ትኩእ <u>የኢትዮጵያ አንድነት እና ኢጣሊያ</u> በቷባለው መጽሐፋቸው ገጽ 136 "የዋግሹም ጎበዜ እና የበዝብዝ ካሣን ምሳሌ በመከተል ምኒልክም ከመቅደላ ሸሽቶ ሸዋ ገብቶ ሥልጣን ለመያዝ በቅቶ ነበር:: እነዚህ ሁሉ ፀረ አጤ ቴዎድሮስ አመጸኞች ቴዎድሮስን ለመዋጋት ወደ ኢትዮጵያ የገባውን የእንግሊዝ ሠራዊት እንደነጻ አውጭ ነበር የተመለከቱት:: የቴዎድሮስን ፍጻሜም በደስታ ነበር የተቀበሉት:: አጤ ቴዎድሮስ በዘመነ መንግሥቱ በሕይወቱ በኢትዮጵያውያንም ሆነ በውጭ ሀገር ዜጎች ጠላቶችን እንጂ ወዳጆችን አላፈራም" ሲሉ ጽፈዋል::

በእርግጥ "የእንግሊዝን ሠራዊት እንደነጻ አውጭ ነበር የተመለከቱት" ያሉት ሊቅ ተወልደ ደጃዝማች ካሣ ምርጫን እንጅ ሌሎችን አይመስለኝም:: ዋግሹም ደጃዝማች ጎበዜ በደብዳቤ ቢተባበሩም ከእንግሊዝ ጦር መሪ ጋር አልተገናኙምና የእንግሊዝን ጦር እንደ ነፃ አውጭ አልቆጠሩትም:: እንደ ነፃ አውጭ ቢቆጥሩትማ ኑሮ ጄኔራል ናፒር "ይምጡ"እያለ ሲልክባቸው መሂድ ይችሉ ነበር:: በእርግጥ አጤ ቴዎድሮስን አይወዱም ትክክል ነው:: ነገር ግን የእንግሊዝን ወታደር እንደ ነጻ አውጭ አልተመለከቱትም::

<u>ኢትዮጵያና ዕድሏ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 125 "በዝብዝ ካሣ ለአጤ ቴዎድሮስ ታማኝ ሆነው ቢቆዩም የቴዎድሮስ ውድቀት ዘመን ሲቃረብ ከእንግሊዞች ጋር ተስማምተው ከትግራይ ክፍለ ሀገር እስከ ምጽዋ ወደብ በሠራዊት ተጠናክረው ነበር:: የእንግሊዝ ጦር አጤ ቴዎድሮስን ለመዉጋት ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ጊዜ ካሳ መንገዱ እንዲቃና በማድረጋቸው የእንግሊዞችን ወዳጅነት ስላተረፉ ኋላ



ሥልጣን ለመያዝ እንዲችሉ የእንግሊዞችን እርዳታ ሙሉ ድጋፍ አግኝተዋል::"

"እንግሊዞች አጤ ቴዎድሮስን ለመውጋት ከምጽዋ እስከ መቅደላ ያለውን 650 ኪሎ ሜትር ለመጓዝ የበዝብዝ ካሳን ድጋፍ ባያገኙ ኖሮ በየመንገዱ ሕዝቡ ግጭትና መሰናክል ስለሚገጥማቸውና ምግብም ለማግኘት አስቸጋሪ ስለሚሆንባቸው ቴዎድሮስን ድል የማድረጉ ሁኔታ አጠራጣሪ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: ኮሎኔል አስራት ቦጋለ እንዳሉት ጥሩ ግምገማ ነው::

ሻለቃ ጌታቸው የሮም <u>ስም ከመቃብር በላይ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 366 "አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ በተነሡበት ጊዜ ከውስጥ የተነሡባቸው መሳፍንትና ትናንሽ ነገሥታት ይህን ዓላማቸውን ሲቻላቸው በፊት ውጊያ ሲጨንቃቸው በሽፍትነት እያመፁባቸው የተረጋጋ መንግሥት እንዳይመሠርቱ አድርገዋቸው ነበር::"

"ይህ ሁሉ አልበቃ ያላቸው መሳፍንት በመጨረሻው አስተባብረው ያመጡት የእንግሊዛውያን ጦር ወደ መሀል አገር መግባት የቻለው በዚህ በር ነበር:: ቴዎድሮስ እጅ ሰጥቶ መማረክ ወይም በሽሽትና በስደት መሞት ታሪካቸውን እንደሚያጎድፈው ወታደሮቻቸውንም እንደሚያሸማቅቅ ስላወቁ ራሳቸውን ሠውተው አለፉ" ሲሉ ጽፈዋል::

# ክፍል ስምንት

## ምዕራፍ 1

### የኢትዮጵያና የአውሮፓውያን ግንኙነት

ከዚህ መጽሐፍ ላይ ወደ ኋላ ተመልሰን ታሪክ መመርመር እንዳለብን ተገንዘብኩኝ:: ማንም ክርስቲያን የሆነ አገር ሁሉ ኢትዮጵያ አገር መሆንዋን ይረዳል:: በተለይም መጽሐፍ ቅዱስን ጠንቅቆ የሚያነብ ማለቴ ነው:: የቀድሞ ክርስቲያኖች የኢትዮጵያን ታላቅነት ያምኑ ነበር:: ለምሳሌ ልዑል እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረ በኋላ ከገነት• የሚፈሱ ወንዞች ሲመዘገቡ አንዱ ግዮን መሆኑ አይዘነጋም::

በነገራችን ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ከገነት የሚፈሱ ወንዞች የተባሉትን የኢትዮጵያ የታሪክ መጻሕፍት ሁሉንም በኢትዮጵያ የሚፈሱ መሆናቸውን ጽፈዋል:: ተከዜ፤አዋሽና ባሮ ግዮን መሆናቸውን የጻፉ ብዙ ናቸው:: ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት ለክርስቶስ የእጅ መንሻ የሚያመጡለት ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን በመዝሙረ ዳዊት ተጽፏል:: ኋላም ክርስቶስ ሲወለድ "የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው" ብለው ሄሮድስን የጠየቁት ሰብአ ሰገል ኢትዮጵያውያን ናቸው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስደቱ ዘመን ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ ከድንግል ማርያም ጋር መጥቶ መኖሩን የታሪክ መጻሕት ጽፈዋል:: እንዲያውም ሰሜን ተራራ ላይ ከዋልያዎች ጋር ሥዕል ተሥሎ በታሪክ መጽሐፍ ላይ ወጥቶአል:: ሲያትል ዋሽንግተን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በያመቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ ገዳማት የሚልኩት ገንዘብ አለ:: የገዳማቱ አበምኔቶች ገንዘቡ የደረሳቸው መሆኑን በምስል ድምጽ በቪዲዮን ተቀርጸው የላኩት ካሴት ክር አለ::

<u>ሲያልት ቅዱስ ገብርኤል</u> ቤተ ክርስቲያን ከሚረዱአቸው ገዳማት አንዱ ጎንደር ጣራ ገዳም ሲሆን አበምኔቱ ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ"



ቅድስት ድንግል ማርያም በስደቷ ጊዜ ከዚህ ቦታ ላይ ዓርፋለች" በማለት ይናገራሉ:: ሐዋርያትም በኢትዮጵያ ክርስትናን አስተምረዋል:: ኋላም በሐዋርያት ሥራ የተጻፈው ባኮስ ጃንደረባው ኢትዮጵያዊ መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ በመመዝገቡ አውሮፓውያን ኢትዮጵያን ጠንቅቀው ያውቃሉ::

ይህ ብቻ ሳይሆን በፈረንጆች አጠራር "ፕሬስተር ጆን" ብለው የሚጠሩት የአንድ ንጉሠ ነገሥት ደብዳቤ በ12ኛው ክፍለ ዘመን አውሮፓ ተሰራጭቷል:: ይህ ደብዳቤ ከኢትዮጵያ ወደ አውሮፓ የተሰራጨበት ዘመን አውሮፓውያን ኢየሩሳሌምን ከእስላሞች ለመቀማት ጦርነት በገጠሙበት ዘመን በመሆኑ በምሥራቅ አፍሪካ አጋዥ ኃይል አገኘን ብለው በማሰብ ኢትዮጵያ ያለችበትን አውሮፓውያን ለማወቅ ጥረት አድርገዋል:: ምንም እንኳ በእስላሞች አቸናፊነት ጦርነቱ ቢጠናቀቅም ኢትዮጵያን ለማግኘት ብዙ ጥረት ተደርጓል::

ይህ በዚህ እንዳለ የፖርቱጋል አሳሾችና የሃይማኖት ሰዎች በ1510 ዓም ሸዋ መጥተው ከአጤ ልብነ ድግል ጋር ግንኙነት ለማድረግ ሲሞክሩ አጤ ልብነ ድንግል ገበጣና ጉግስ በመጫወት ጊዜ አግኝተው ሳያናግሯቸው 6 ዓመት ተቀመጡ:: ይህ በሆነበት ወቅት አጤ ግራኝ አሕመድ በቱርኮችና በየመን በግብጽ በሌሎችም የዐረብ አገሮች የተሟላ የጦር መሣሪያ ታጥቀው ከሐረር ጀምረው የአጤውን መንግሥት ለማናጋት ሲነሡ የአጤ ልብነ ድንግል እናት እቴጌ እሌኒ ለፖርቱጋል መንግሥት የጦር መሣሪያ እርዳታ እንዲልኩላቸው ተማፀኑ::

ነገር ግን ወጣቱ ተዋጊ አጤ ግራኝ አህመድ ጊዜ የማይሰጡአቸው ሆኑ:: ከሸዋ እስከ ባሕረ ነጋሽ እየተከታተሉ ያሳድዷቸው ጀመር:: ለትንሽ ጊዜ ዕረፍት አግኝተው የነበሩት ከትግራይ ተከዜን ተሻግረው ወልቃይት ውስጥ በተቀመጡ ወቅት ነበር::

ይህ በዚህ ሳለ እቴጌ እሌኒ ለፖርቱጋል መንግሥት የላኩት "የድረሱልን" ደብዳቤ ሲደርሳቸው በዶም ክርስቶፎርን ደጋማ የሚመራ 400 ወታደሮች ምጽዋ ደረሱ:: የፖርቱጋል ወታደሮች ምጽዋ ገቡና ከእቴጌ ሰብለ ወንጌል ጋር ግንኙነት አደረጉ:: በወቅቱ

አጤ ልብነ ድንግል ሙተው ልጃቸው ደጃዝማች ገላውዴዎስ የአጤ ግራኝ አህመድን ጦር እየተዋጉ ነበሩ።

ኋላም ደጃዝማች ገላውዴዎስ ከወላጅ እናታቸው ከቴጌ ሰብለ ወንጌል መልእክት ሲደርሳቸው ወደ ትግራይ ተሻግረው ከዶም ክርስቶፎር ደጋማ፤ ጋር ተገናኝተው ተመካከሩ። ተባብረው አጤ ግራኝ አህመድን ጦርነት ገጠሙአቸው። ነገር ግን የአጤ ግራኝ አህመድ ጦር ከሐረር እስከ ባሕረ ነጋሽ እየጠረገ የመጣ ኃይለኛ በመሆኑ የማይቀመሳቸው ሆነ። በዚህ ወቅት የመጡት 400 ወታደሮች ከሁለት ቀን ጦርነት በኋላ ግማሾቹ ሲሞቱ ግማሾቹ ወደ መጡበት አገራቸው ተመለሱ።

ዶም ክርስቶፍ ደጋማ 20 የማይሞሉ ወታደሮችን ብቻ ይዘው ከደጃዝማች ገላውዴዎስ ጦር ጋር ሁነው ውጊያውን ተያያዙት። ነገር ግን እርሳቸውም በአጤ ግራኝ አህመድ ጦር ተማረኩና ተገደሉ። በዚህ ወቅት በአንድ የከንባታ ጦረኛ አጤ ግራኝ አህመድ ሲቆስሉ የተመለከተ የፖርቱጋል ወታደር "እኔ መታሁት ግራኝን" ብሎ ለደጃዝማች ገላውዴዎስ ተናገረ።

አጤ ግራኝ አህመድ ቁስላቸው ጠንክሮባቸው ሞቱ። በዚህ ወቅት ደጃዝማች ገላውዴዎስ አጤ ሁነው በኢትዮጵያ ነገሡ። ያ የከምባታ ጦረኛ መሸለም ሲገባው አጤ ገላውዴዎስ ለአፈ ሙሌው ለፖርቱጋሉ ሰጡት። ከዚህ ወቅት ጀምሮ የፖርቱጋልና የኢትዮጵያ ግንኙነት ሲጀምር አውሮፓውያን ኢትዮጵያ የተባለች አገር መኖሯን ጠንቅቀው አወቁ።

ኋላማ በብዛት ፖርቱጋሎች ገቡና አጤ ሱስንዮስን አሳምነው የኢትዮጵያ የመንግሥት ሃይማኖት ካቶሊክ መሆን አለበት ብለው እንዲያውጁ አደረጉ። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጦርነት ወደ ጦርነት እንዲገባ አድርገዋል። ተዋሕዶ አማኞች በአንድ ቀን ብቻ 24 ሺህ ሰዎች ደንቀዝ ላይ ታርደዋል። ይህ ጦርነት የኢትዮጵያን ሕዝብ በአጤ ግራኝ አህመድ ካለቀው ይልቅ ሕዝቡን አስጨረሰ። በዚህ ወቅት አጤ ሱስንዮስ ታመሙና ልሳናቸው ተዘጋ።

የካቶሊክ ካህናት በጸሎትና በጸበል ቢሞክሩ ለውጥ አላሳዩም። ታዲያ ደጃዝማች ፋሲል ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ላሉት አባቶች "አባቴ



ታመዋል ኑና በጸሎታችሁ እርዱኝ" ብለው ላኩባቸው። የማኅበረ ሥላሴ ገዳም አባቶችም ጎርጎራ ቤተ መንግሥት መጡና ጸሎትና ምህላ ሲያደርጉ ሰንብተው ጸበል ሲረጯቸው አጤ ሱስንዮስ "ሃይማኖት ይመለስ ፋሲል ይንገሥ" ብለው ተናገሩ።

ከዚህ ወዲህ ተዋሕዶ ሃይማኖት ነፃ ስትወጣ ካቶሊኮች ወደ ሀገራቸው እንዲሄዱ በአጤ ፋሲል ሲታዘዙ ብዙዎቹ ወደ ሀገራቸው ሄዱ። ነገር ግን አንዱ ተንኮለኛ የካቶሊክ መነኩሴ አድዋ ሲደርስ "አሞኛል" ብሎ ተኛ። ከዚህ ቦታ ላይ የካቶሊክን ሃይማኖት መሥርቷል። ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያን የሚያፈርሱ አንዳንድ ግለሰቦች የሚወለዱበት ቦታ ይህ አድዋ ሆነ።

ከዚህ ወቅት ጀምሮ አውሮፓውያን ኢትዮጵያን በገናናነትና በሃይማኖት ክርስቲያን መሆንዋን ጠንቅቀው አወቁ። የኢትዮጵያ ቀጥተኛ (ኦርቶዶክስ)ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቆች ከኢየሩሳሌም ወደ አውሮፓ ገብተው ሃይማኖትንና የግእዝን ፊደል የአማርኛን ቋንቋ አስተምረዋል። በተለይም አባ ጎርጎርዮስ የተባሉት የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ሁለት ታላላቅ መጻሕፍትን ይዘው መላ አውሮፓን ዞሩ።

አባ ጎርጎሬዮስ ወደ አውሮፓ የሄዱበት ዘመን በ1640 ዓም ሲሆን ለኢትዮጵያ ታሪክና ለተዋሕዶ ሃይማኖት ምሰሶ ሁነዋል። እርሳቸው ምንም እንኳ የተዋሕዶን ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን መሥርተው ማስተማር ባይችሉም የሃይማኖቱን መሠረትና ሥርዓት የግእዝን ኃያልነት ለአውሮፓ ምሁራን አስተምረዋል። ለዚህም ነው ዛሬ ድረስ ጀርመን አገር በዩንቨርስቲ ደረጃ የግእዝ ትምህርት የሚሰጠው።

ለምሳሌ አባ ጎርጎርዮች ጀርመን አገር ከ12 ዓመት በታች ያሉትን ሕፃናት ሰብስበው ግእዝ እና አማርኛ ቋንቋ አስተማሩአቸው። እነዚህ እርሳቸው ካስተማሯቸው መካከል ሉድፍ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው። ዶልፍ ብዙ መጻሕፍትን በግእዝ እና በአማርኛ ቋንቋ ጽፈዋል። ለምሳሌ እነዚህ መጻሕፍት የታተሙበትን ዘመን ተመልከቱ።

1ኛ ግእዝ ሰዋሰው በ1661   2ኛ ግእዝ ላቲን መዝገበ ቃላት
3ኛ አዲስ የኢትዮጵያ ታሪክ  4ኛ የኢትዮጵያ ታሪክ 1698

5ኛ የአማርኛ ሰዋሰው መዝገበ ቃላት1698
6ኛ አማርኛ ላቲን መዝገበ ቃላት 7ኛ የዳዊት መዝሙር 1701
8ኛ የኢትዮጵያ ዶክትሪን የተባለ መጻሕፍት ጽፈዋል።

ዶልፍን ግእዝና አማርኛ ያስተማሩ አባ ጎርጎርዮስ ናቸው። በነገራችን ላይ ትንሽ ወደ ኋላ መለስ ብለን ታሪክ ስንመረምር በ1513 ዓም ላይ አንድ መዝሙረ ዳዊትና ሌሎች የሃይማኖት መጻሕፍት በሮማ ታተመ። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በ1548 ዓም ገደማ እዚያው ሮማ አንድ የግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ ታተመ። ይህ አውሮፓ የተፈጠረው አዲስ መማሪያ የአፍሪካን ፊደል ግእዝን ቀርጸ መጽሐፍ ቅዱስን አተመበት።

አማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ከዚያው ሮማ የታተመ ቢሆንም ዓመተ ምሕረቱን ግን ግልጽ ሁኖ የተጻፈበት ሰነድ ላገኝ አልቻልኩም። 200 የሚሆን በአማርኛ ቋንቋ የታተመ መጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ የገባው ግን በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ሲሆን ያመጡትም ማርቲን ፍላድ ናቸው። ለሥልጣኔ አንጎላቸው ክፍት የነበሩና ከዘመኑ ሰዎች በምዕተ ዓመት ቀድሞ አሳቢ በሆኑት ቴዎድሮስ ዘመን አባ አብርሃም በተባሉት ኢትዮጵያዊ ሊቅ የተተረጎመ የተሟላ መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ ፊደላት በአማርኛ ቋንቋ ታተመ። ከዚህ ወዲህ ደግሞ የብርቲሽ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በአማርኛ ቋንቋ የታተመ መጽሐፍ ቅዱስ በመላ ኢትዮጵያ አሰራጭቷል።

በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች አውሮፓውያን ኢትዮጵያን ጠንቅቀው ያውቃሉ። በተለይም ይህ ግማሽ መጽሐፍ ቅዱስ የሚቀበለው ትርኪ ምርኪ ሃይማኖት የራሳቸውን መሠረት ሊያቆሙ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ይሽቀዳደሙ ጀመር። እነዚህ የሃይማኖት ድርጅቶች እምነት ብቻ ሳይሆን የሚሰብኩት ትውልዱ በማንነቱ እንዳይኮራ ነባሩን የተዋሕዶ ሃይማኖት እንዳይማር ለማድረግ ጥረት አድርገዋል። ይህን ማድረግ ብቻ ሳይሆን አንዱን ጎሳ ካንዱ ጎሳ ጋር የሚያቃርን ታሪክ እየጻፉ አውሮፓ ውስጥ ይበትኑት ጀመር። እነዚህ የሃይማኖት አስተማሪዎች የጻፉትን መጽሐፍ እያነበቡ እሽቅድድም ማድረግ ጀመሩ።

የሚገርመው ነገር ደግሞ እነዚህ የውጭ ሃይማኖት ሰባክያን ክርስትናን ለማስፋፋት ጥረት ማድረግ የጀመሩት ክርስትና



ሃይማኖት የተቀበለውን ሕዝብ እንጂ አህዛብን አልነበረም። ለክርስትና ሃይማኖት ቀናዒ ቢሆኑማ ኑሮ ቦሲንያ ክርስቲያኖች በቱርክ ሲደበደቡ ታዲያ ለምን አልደረሱላቸውም?

ስለዚህ አውሮፓውያን ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ክርስቲያን የነበረውን ሕዝብ አስቀይረው የነሱ ሃይማኖት አማኝ ለማድረግ ዓላማቸው ሲሆን ሌላው ግን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት መንግሥታቸው እንዲይዝ ለማድረግ ነበር። እያንዳንዳቸው የወንጌል ሰባክያን የጻፉትን መጽሐፍና የግል ደብዳቤያቸውን ጥሩ አድርጎ መመርመር ይቻላል። የእነዚህን የወንጌል ሰባክያን ጽሑፍ መነሻ አድርገው ሌሎች የክርስ ምድር መርማሪዎች ወደ ኢትዮጵያ ፊታቸውን አዞሩ።

እነሱም ያልተበላ መሬት ያላት መሆኗን ለመንግሥታቸው በጽሑፍ አስታወቁ። ወቅቱ አፍሪካን በቅኝ ግዛት ለመያዝ የሚመኙበት ዘመን በመሆኑ መንግሥታቶቻቸውም ከኢትዮጵያ ጋር በተለያዩ ጊዜ ግንኙነት አደረጉ። ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የአውሮፓ አገሮች አንዷ እንግሊዝ ስትሆን እርሷም ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት ያደረገችበትና ከተለያዩ የመሳፍንት ገዥዎች ጋር የተዋዋለችበትና ወዳጅነቱ ጠንክሮ መኖሩን ኋላም በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ደርሶ ጦርነት ያማዘዝ መሆኑን ከዚህ ዝቅ ብሎ የምጠቅሳቸው ምዕራፎችን በጥሞና ተመልከቷቸው።

## ምዕራፍ 2

## የእንግሊዝ እና የኢትዮጵያ ግንኙነት!

ከአውሮፓ አገሮች መካከል አንዷ እንግሊዝ ናት። በተለይም ኢትዮጵያ በዘመነ መሳፍንቱ ተከፋፍላ ባለችበት ወቅት አገር ለመጎብኘት የመጣው ጀምስ ብሩስ በብዛት የኢትዮጵያን መጻሕፍትና ቅርሳቅርስ መውሰዱ አይካድም። ይህ ከሆነ ጀምራ በፈረንሳይና በእንግሊዝ መካከል ባለው መፎካከር ቀይ ባሕርን ፈረንሳይ እንዳትይዝባት እንግሊዝ የሃይማኖት ሰባክያንንና ነጋዴዎችን በቀይ ባሕር ዙሪያ አሰማራች። እነሱ የወንጌል ሰባክያን

እያሉ ሰላዮቻቸው አገር አሳሾችና ከርሰ ምድር አጥኚዎች ቀስ በቀስ ወደ ኢትዮጵያ ተሰማሩ።

በዚህ ላይ እንግሊዝ ደግሞ ሕንድን በቅኝ ግዛት ይዛለች። ሌላ ተጨማሪ የሸቀጥ ማራገፊያ አገር ትፈልጋለች። ይህ ብቻ አይደለም ሌላው ደግሞ ወንጌል እናስተምር እያሉ የሚመጡት ጽላተ ሙሴ የት እንዳለች ለማወቅ ሙከራም ማድረጋቸው አልቀረም። በዚህ ምክንያት የእንግሊዝ ተጓዦች ሆኑ የሃይማኖት አስተማሪዎች ለመንግሥታቸው የኢትዮጵያን ሁኔታ በየጊዜው ማስታወቃቸው አልቀረም። ይህ ከሆነ ጀምሮ እንግሊዝ ከኢትዮጵያ ጋር ሕጋዊ ግንኙነት ማድረግ ፈለገች።

ለምሳሌ ጀምስ ብሩስ የወሰደው መጽሐፍ ብዙ ነው። ጀምስ ብሩስ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ1764 ዓም በፊት ነው። አንዳንዶች ደግሞ ከጀምስ ብሩስ በፊት እንግሊዞች ስለ ኢትዮጵያ ብዙ የሚያውቁ ናቸው ይላሉ። ወደ ኋላው ዘመን ስንመጣ እንግሊዞች ከኢትዮጵያ ጋር ያደረጉአቸውን ውሎች በጥሞና ለሚመለከት ብዙ ጥናት ያደረጉ ይመስላል። ለምሳሌ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ያሳተመች ቀደም ብላ ነበር።

በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት በሸዋና በደብረታቦር ከመሳፍንቶች ጋር ያደረጉአቸውን ውሎች በጥሞና ላስተዋለው ቀደም ብለው የኢትዮጵያን ሁለመና ጠቃሚ መሆኑን የተገነዘቡ መሆናቸውን ይገልጻል። በተለይ በ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ19ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ አንሥቶ ግንኙነት የተጀመረ መሆኑን ሰነዶች ያስረዳሉ።

የእንግሊዝ መንግሥት ኢትዮጵያን ካስመረመረ በኋላ ቆንስል ለመላክ ያደረገው ውል ኢትዮጵያን የሚጠቅም ሳይሆን የሚጎዳ ውል መሆኑ አይዘነጋም። ለምሳሌ ፈረንሳይ ከሸዋ መሳፍንት ጋር ቀደም ከንጉሥ ሣሕለ ሥላሴ ኋላም ከልጃቸው ከንጉሥ ኃይለ መለኮት ጋር መፈራረማቸው አይዘነጋም። እንግሊዞች ከሸዋ መሳፍንት ብቻ ሳይሆን ቅድሚያ ግንኙነት ያደረጉት ከትግራይ መሳፍንት ጋር ነበር።



1ኛ እንግሊዞች ከትግራይ መሳፍንቶች ጋር ያደረጉት ግንኙነት ሶልት የተባሉት እንግሊዛዊ ትግራይ የመጡት በ1798 ዓም ሲሆን ያስተናገዷቸው ራስ ወልደ ሥላሴ ናቸው። እርሳቸውም የእንግሊዝን መንግሥት የጦር መሣሪያ ላኩልኝ ማለታቸው ታውቋል። ከዚህ ወዲህ አቶ ሶልት ሌሎችን ተመራማሪዎች በመያዝ ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያ ተመላልሰዋል።

አቶ ሶልት ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሱ በኋላ በጥቅምት በ1804 ዓም ደብዳቤ ጽፈውላቸዋል። ይህ ደብዳቤ ግማሹ በግእዝ ሲሆን አማርኛም አለው እንዲህ ይላል "ሀገሬን ሦስት ዓመት ሙሉ አንበጣ በላው፤ፈጀው አሁንም ጠላት ተነሥቶብኝ ጎንደር ወጣሁ፤ቀን ቢሰጠኝ ጎንደር ብቀመጥ መጣሁ" ሲሉ ለአቶ ሶልት ጽፈውለታል። ይህም ብቻ ሳይሆን ሌላ ብዙ ደብዳቤዎች አሉ። ነገር ግን በዚህ ወቅት የተዋዋሉት አንድም ውል አልተገኘም።

2ኛ ከዚህ በኋላ ደግሞ ፈረንሳይ ቀድማ ሸዋ ስለገባች እንግሊዞች ደግሞ ባጥኝ መልክ ቂስ ክራፕ መጥተው ሸዋን ጎብኝተዋል። እርሳቸው ፈረንሳይ ከሸዋ ጋር ያደረገችውን ውል በመስማታቸው ቀንተው ለመንግሥታቸው መልክእት ላኩ። መንግሥታቸውም በ1832 ዓም በኮርንዋሊስ ሐሪስ፤ የሚመራ ቡድን ሸዋ ድረስ መጣ። በዚህ ወቅት ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የወዳጅነት ውል ተፈራርመዋል። ከሀገራቸው አርቅቀው ያመጡት ረቂቅ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል።

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 143 "ፕላውዴን በራስ ዐሊ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ኢትዮጵያ እንደገባም ራስ ዓሊን ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር አስተዋወቀ። በዚህ ዓይነት የፖለቲካ ግንኙነት ተስማምተው ሲሠሩ ሳይታሰብ የራስ ዓሊ ውድቀት ሆነ። ፕላዊዴን ራስ ዓሊን ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ተራ ሰው ሁኖ ካስተዋወቀ በኋላ በቆንስል ደረጃ ተመደቦ በኢትዮጵያ ብዙ ጊዜ እንደተቀመጠ የሚታመን ነው።"

"አጤ ቴዎድሮስ ፕላውዲን ራስ ዓሊን በማታለል ያደርገው የነበረውን የተንኮል ሥራ አስቀድመው ያውቁ ስለነበር መልኩን ለማየት አይፈቅዱም ነበር። ቢሆንም ዮሐንስ ቢል በነገሩ ገብቶ ስለ ፕላውዲን ትልቅነትና ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ደኅና አድርጎ

እንደሚያስተዋውቃቸው በሰፊው እየዘረዘረ ስለነገራቸው በእርሱ አቅራቢነት ከአነጋገሩት በኋላ በራስ ዓሊ ቤት በነበረው ማዕረግ (በቆንስል) በአምባሳደር ደረጃ ተቀብለውታል" ሲሉ ጽፈዋል።

ፕላውዲን ወደ ኢትዮጵያ ተሳከ። ጉዳይ ፈጻሚ ፕላውዲ ከምጽዋ ጎንደር ከዚያም ከዋናው ከራስ አሊ ጋር ተገናኝቶ አንዳንድ ውሎችን ፈጽሟል። አጤ ቴዎድሮስ በመጀመሪያው በፕላውዲን ላይ ቂም የያዙበት ራስ አሊን የወዳጅነት ፊርማ ሲያስፈርማቸው ልክ ሸዋ ላይ እንግሊዞች ያስፈረሙበትን ቅጅ ይዞ ራስ አሊን አግባብቶ አስፈርሟል ተብሎ በመነገሩ ምክንያት ነው።

ይህም "ዜጎችን የሚመለከት ክስ ከኢትዮጵያ የፍትሕ ተቋማት ሥልጣን ውጭ ሆኖ በቆንሲሉ እንዲታይ መደረግ አለበት" የሚለውን አንቀጽ አጤ ቴዎድሮስ አልወደዱትም ነበር። ኋላ ግን እጅግ በጣም ወደውታል። ብዙም አምነውታል። የሥልጣኔን ጮራ እንዲያዩ ከነበራቸው ብሩህ ጭንቅላት ላይ በርቷል። ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ተቀራርበው ወዳጅነት መሥርተው አገራቸውን ሊያሳድጉ እንደሚችሉ ተረድተዋል።

<u>ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ---</u>የተባለው መጽሐፍ ገጽ 24 "አጤ ቴዎድሮስ ዙፋኑን ከያዙ በኋላ ቆንስል ፕላውዲን ከእርሳቸው ጋር ተስማምቶ ለመሥራት ያደረገው ጥረት እምነታቸውን አክብሮታቸውን አትርፎለታል" ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ኋላማ እንዲያውም በጣም አቅርበውት ነበር። ቆንሲል ፕላውዲንን የወንድማቸው ልጅ ደጃዝማች ጋረድ በመግደላቸው ምክንያት በጣም አዝነዋል። የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ግንኙነት ከብዙ ዘመን ጀምሮ ነው። የሁለቱን አገሮች ግንኙነት በተመለከተ ራሱን ችሎ የዲፕሎማቲሲ ግንኙነት ሠነድ የሚያመለክተው ከ1798 ዓም የጀመረ መሆኑ ነው። ከዚህ ወዲህ የእንግሊዝ መንግሥት መልክተኞችን ወደ ኢትዮጵያ ልኳል።

ደብረ ታቦር የመጡት መልእክተኞች ከራስ አሊ አሉላ ጋር ባደረጉት ውይይት ራስ አሊ አሉላ ከእርሳቸው በፊት በነበሩት መሳፍንቶች ድክመት ምክንያት የኢየሩሳሌም ገዳም ለኢትዮጵያውያን እንዲመለስላቸው ጠይቀዋል። ሌላው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ሆኑ



ንጉሥ ኃይለ መለኮት የዚህን ገዳም ጉዳይ አንሥተዋል። ኢየሩሳሌም የነበረው የእንግሊዝ ቆንስላ ከቱርክ ፓሻ ጋር መነጋገራቸው አልቀረም። ነገር ግን ለእንግሊዝ ከቱርክና ከኢትዮጵያ የሚቀርባት ቱርክ በመሆንዋ ለቱርክ ወግና የኢትዮጵያን ውል ቸላ ብለዋለች።

ኢትዮጵያን ዘመነ መሳፍንቱ ቀፍድዶ ይዟት በነበረበት ወቅት እንግሊዞች በቆንስል ደረጃ ግንኙነት ለመመሥረት በትንሹ ራስ አሊ ዘመን አቶ ፕላውዲ ደብረታቦር መጥቶ ግንኙነት ጀምሮ ሳለ ራስ አሊ ከደጃዝማች ካሳ ጋር ሲዋጉ የተማረከ ሲሆን ዮሐንስ ቤልና ፕላውዲ ደጃዝማች ካሳን ደግፈው እስከ ሰሜን አብረው ሂደዋል።

በዚህ ምክንያት አጤ ቴዎድሮስ ተብለው ሲነግሡ እነዚህ የእንግሊዝ ዜጎች ለአጤ ቴዎድሮስ ብዙ ለመርዳት ጥረት ማድረጋቸው አይዘነጋም። አጤ ቴዎድሮስም እነዚህን የእንግሊዝ ዜጎች ያዳምጡአቸው ነበር። በወጣትነታቸው ወቅት ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ሲማሩ ብዙ ጊዜ በኢየሩሳሌም ነዋሪ የነበሩ መነኩሴ መምህራቸው ስላስተማሩአቸው እነዚህ የእንግሊዝ ዜጎች ሲከልሱላቸው ኢትዮጵያን ለንደን ለማድረግ ከፍተኛ ጉጉት አደረባቸው።

የአጤ ቴዎድሮስን ጀግንነት ሆነ የኢትዮጵያን ታላቅነት ቆንስል ፕላውዲ ለመንግሥታቸው ማስተዋወቃቸው ግልጽ ነው። እንዲያውም የቆንስልነቱን ማዕረግ የረሱት ይመስላሉ። ማለት ቆንስል ፕላውዲ አጤ በሄዱበት ቦታ ሁሉ አብረው እንደ አንድ ወታደር ሁነው የዘመቱ ናቸው። ይህን የእርሳቸውን ተግባር የእንግሊዝ መንግሥት ባይወድላቸውም እርሳቸው ግን አጤ ቴዎድሮስን ከመውደዳቸው በላይ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ብዙ ጥረት ያደርጉ ነበር።

አጤ ቴዎድሮስ ሊያሠሩት ላቀዱት የጦር መሣሪያ ሠራተኞችን ለማግኘትም የጣሩ ነበሩ። ለመንግሥታቸው የጻፉት ደብዳቤ "አጤ ቴዎድሮስ ለወታደሮቻቸው የጦር መሣሪያ እንደማግኘት የሚያስደስታቸው ነገር የለም" ሲሉ ጽፈው ነበር።

በእርግጥ የእንግሊዝ መንግሥት ወደ ምድብ ቦታቸው ጽህፈት ቤታቸው ምጽዋ እንዲመለሱ ያደረገውን ውትወታ ናቅ አድርገው ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር አብረው ደክመዋል። ዮሐንስ ቤል የተባሉት

ግን በቆንስል ደረጃ የተቀመጡ ባይሆኑም የአጤ ቴዎድሮስ ወታደር ነበሩ ማለት ይቻላል። ለዚህም ነው ሊቀ መኳስ ያሏቸው አጤ ቴዎድሮስ፤ እነዚህ ሁለት እንግሊዞች አጤ ቴዎድሮስ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያጠነክሩ ባላቸው ችሎታ ሁሉ አስረዷቸው።

አጤ ቴዎድሮስ ቀደም ሲል ያን ያህል ይጠሉት የነበረውን ፕላውዴን የወንድማቸው ልጅ በመግደሉ ምክንያት ማዘን ብቻ ሳይሆን ተበሳጭተዋል። ይህ የአጤ ቴዎድሮስ ጸባይ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያውያን ሁሉ ጸባይ ነው። ይከደኛል ብለው ሳይጠረጥሩ ከልባቸው ነበር የወደዱት። ፕላውዴም ለአገሩ መንግሥት ደግጋሞ እቅዳቸውን ዘርዝሮ ከመጻፍ አልተቆጠበም ነበር።

ቆንሲል ፕላውዴን ኑሮ ቢሆን አውሮፓውያን በአጤ ቴዎድሮስ አይታሰሩም ነበር። የእንግሊዝ መንግሥትም ያን ያህል ወጭ አያወጣም ነበር። ጦርም አያዘምትም ነበር። በቆንስል ፕላውዴን ቦታ ጉዳይ ፈጻሚ ካሜሮን መምጣቱና የኢትዮጵያ እና የእንግሊዝ መንግሥት ግጭት ከዚህ ዝቅ ብሎ ባለው ምዕራፍ ይቀጥላል።

## ምዕራፍ 3

### የጉዳይ ፈጻሚ ካሜሮን መምጣትና መታሰር!

በአጤ ቴዎድሮስ የተጻፈ ደብዳቤ እንግሊዝ አገር ሲደርስ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ካሜሮን የሚባል ጉዳይ ፈጻሚ ወደ ኢትዮጵያ ይልካል። አጤ ቴዎድሮስ ካሜሮንን እንደ ፕላውዲ በማየት የልባቸውን ስሜት ሳይደብቁ ነገሩት። ፍላጎታቸው በኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ ማምረት ሲሆን ለዚህ ቅዱስ ዓላማ አስተማሪ ከእንግሊዝ መንግሥት እርዳታ ጠየቁ ይህ ብቻ ሳይሆን ቱርኮችን አስመልክቶ ሌሎች ጉዳዮችን ሳይቀር ነግረው ገንዘብ ሰጥተው ለደብዳቤያቸው መልስ ይዞ እንዲመጣ ላኩት።

ቆንስል ካሜሮን በሰላም አጤ ቴዎድሮስን ተሰናብቶ ወደ ምጽዋ ሄደ። ከዚያም አጤ ቴዎድሮስ የሰጡትን ደብዳቤ በፖስታ ልኮ እርሱ ወደ ከሰላ ተመልሶ ከቱርኮች ጋር ሲገባበዝ ሲከርም ለፈረንሳይ



መንግሥት ደብዳቤ አሲዘው የላኩት ሰው ደብዳቤውን አድርሶ ጎንደር ሲገባ ቆንስል ካሜሮን ግን ደብዳቤው ይድረስ አይድረስ እንኳን ሳያጣራ ወደ አጤ ቴዎድሮስ ሠፈር መጣ። አጤ ቴዎድሮስ ቆንስል ካሜሮንን ከእንግሊዝ አገር አጅበውት የሚመጡ የእጅ ባለሞያዎች ናቸው ብለው ሲጠብቁ፤ እርሱ ግን ከቱረኮች ጋር ሁኖ ሲያማቸውና በሕዝባቸው ላይ ሲቀልዱባቸው መሰንበቱን ቀደም ብሎ የደረሳቸውን ወሬ የሚያጠናክር ሆነ።

እንዲያው አጤ ቴዎድሮስ "ለደብዳቤዬ መልስ አመጣህልኝ ወይ" ሲሉት ቆንስል ካሜሮን ግን "አላውቅም" ሲላቸው አጤ ቴዎድሮስ ተቆጡ። አስተርጓሚው ግን ለአጤ ቴዎድሮስ አስቀድሞ መልእክት መላኩ ታውቋል። ይህ ብቻ ሳይሆን አስተርጓሚው አቶ እንግዳ ወርቅ፤ የኢትዮጵያን ባህላዊ ቀረርቶና ፍከራ እንዲፈክሩ በጉዳይ ፈጻሚ ካሜሮን ታዘዙ። አቶ እንግዳ ወርቅ፤ ጥሩ ገጣሚና አቀንቃኝ መሆናቸው ግጥሙ ይመሰክራል።

"ጃሎ በሉ፤መገን፤ በሉ ጎራው በሉ፤ጀግና በሉ
ይርቀን እንደሆን ምቀኛችን፤ በሽታችን ሁሉ፤
ጃሎ በሉ ጎራው በሉ ያቀምስሃል ያሰው እጁን እንዳመሉ"

በማለት አቶ እንግዳ ወርቅ፤ አቅራርተዋል። ይህን ከዚህ በላይ ያለውን ግጥም ዛሬ ካሉት ባህላዊ ድምጻውያን መካከል ድምጻዊ ወረታው ውበቴ፤ ትንፋሹን አምቆ በመሰንቆ ቢያጉረመርመው ስንቱ ይሸንጠው ነበር። ጃሎ ብለው የደረደሯቸው ግጥሞች ቱርኮች የቋንቋው ምሥጢሩ ስላልገባቸው እንጂ እነሱንም ጭምር የሚነቅፍ ለመሆኑ "ያቀምስሃል ያሰው እጁን እንዳመሉ" ያሉት ቀደም ሲል አጤ ቴዎድሮስ ቱርኮችን መደብደባቸውን የሚገልጽ ሲሆን ጃሎታቸውን ካሰሙአቸው በኋላ ደግሞ ከዚህ በታች ያለውን ፎክረዋል።

"ዘራፍ ቆፍጣናው ዘራፍ የዛለት
ዘራፍ የዛ ለት ደፋር ከፈረ የተለየለት
አባሮ ገዳይ በአባቱ መሬት
አልሞ ተኳሽ የማይሳሳት
ወዳጅ ሲመስል ጠላት ሆነበት
የበላበትን ሰባሪ ወጭት

ልቡ ማይገኝ በሱ ዛተበት
እርሱን ሊያጠቁ ተማከሩበት"

በማለት ፈክረዋል:: ይህን በተለይም "ወዳጅ ሲመስል ጠላት ሆነበት፤ የበላበትን ሰባሪ ወጭት ልቡ ማይገኝ በሱ ዛተበት፤ እርሱን ሊያጠቁ ተማከሩበት" የምትለው የፍከራ ግጥም ቆንስል ካሜሮን ከቱርኮች ጋር ሲዶልቱ ሰምተዋል:: ይህን ግጥም የገጠሙ በቆንስል ካሜሮን ተቀጥረው ቢሠሩም የአገር ጉዳይ ሁኖባቸው የሆነውን ሁሉ ለአጤ ቴዎድሮስ አስቀድመው መላካቸው ትክክል ሊሆን ይችላል:: ቆንስል ካሜሮን ምንም ሳይዙ ከአጤ ቴዎድሮስ ፊት ሲቀርቡ "ለምን ለደብዳቤው መልስ አላመጣህም" ብለው ሲጠይቁአቸው "አላውቅም" የሚለው መልስ ተገቢ አልሆነላቸውም::

በዚህ ምክንያት አጤ ቴዎድሮስ ተቆጥተው አሰሩአቸው:: የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ከአጤ ቴዎድሮስ የሚላክለትን ደብዳቤ ባያቃጥሉትም በሥርዓት ቢያስቀምጡትም እንዴት ተደፈርን በሚል ኩራት ለንግሥቲቱ ባለማድረሳቸው የተነሣ አጤ ቴዎድሮስ ተናቅሁ ማለት ብቻም ሳይሆን ከእንግሊዝ አገር የሚመጡት "ታላቋ" እያሉ ሲያሞግሱ "ለምን አስር ግዜ ታላቋ ታላቋ ትላላችሁ ሁሉም በሀገሩ ታላቅ ነው" ያሉት ቃል ከእንግሊዝ የውጭ መሥሪያ ቤት ወሬው በመድረሱ ምክንያት ይበልጥ የአጤ ቴዎድሮስን ደብዳቤ አሽገው አስቀመጡት::

የአጤ ቴዎድሮስ ደብዳቤ "ቱርኮች አገሬን ይዘውብኝ ባላጋራ ሁነውብኛልና መርከብ የለኝ በባሕር አልችላቸውም:: በእግዚአብሔር ኃይል የምሰደውን በረከት ከሎሌዬ የሚቀበል ሰው ይስደዱልኝ ብዬ የፍቅር ደብዳቤ ሰጥቼ (ካሜሩንን) ሰደድሁት:: ከወዲያ ተላክሁ ብሎ የመጣበትን ከዚህ ተማክሮኝ የሄደበትን ጉዳይ ትቶ ከቱርኮች ከማይወዱኝ ሰዎች ሂዶ ሲያዋርደኝ ሲንቀኝ ሰንብቶ መጣ" ሲሉ አጤ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቪክቶርያ ጽፈዋል::

ከዚህ በላይ ወጣ ገባ እያለ የተጠቀሰው አጤ ቴዎድሮስና የእንግሊዝ ግንኙነት በጉዳይ ፈጻሚ ካሜሮን ምክንያት ተበላሸ:: ይሁን እንጂ የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የአጤ ቴዎድሮስን ደብዳቤ ለንግሥት ቪክቶርያ አላደረሰም ነበር:: ጉዳይ ፈጻሚው ሆኑ የሌሎች አውሮፓውያን በአጤ ቴዎድሮስ



የመታሰራቸው ቁጥር መጨመርና የእንግሊዝ መንግሥት መደፈር ምክንያት የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤቱ የተደበቁትን ደብዳቤዎች ፈላልጎ ለንግሥት ቪክቶርያ አቀረቡ:: ነገር ግን አንዴ ተበላሽቷል::

አጤ ቴዎድሮስ የአገራቸው ደኅንነት ስጋት ላይ የጣላቸው ከእንግሊዝ ንግሥት እርዳታ ለጠየቁት ደብዳቤ በተደጋጋሚ መልስ ቢጠብቁም አለማግኘታቸው ነበር:: ቁጣቸውና ቅሬታቸው እየበረታ ስለመጣ 60 የሚሆኑ አውሮፓውያን እንዲታሰሩ ተደረገ:: ይህ እርምጃ እንደተወሰደ ዲፕሎማቱ ካሜሮን ለአጤ ቴዎድሮስ መልስ እንዲልክ ለሀገሩ መንግሥት በጥብቅ ቢያሳስብም::

ከንግሥት ቪክቶርያ ለአጤ ቴዎድሮስ የደረሳቸው መልስ አጥጋቢ ሆኖ ስላላገኙት እሥረኞቹን አልፈቱም:: አጤ ቴዎድሮስ የተበታተነችውን አገር አንድ ለማድረግ ሲነሡ የገጠማቸው ዋናው ችግር ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ ማምረት አለመቻሏ ነበር::

<u>The Abyssinian Difficulty</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 53 **The Emperor's letter would have been taken on by sailing how' or buggalow, to use the Indian equivalent,to Aden. The Political Agent at Aden, which come under the government of India, forwarded them by steamer to Bombay, and they eventually reached the Foreign Office on 12 February 1863,three and a half months later.**

**By the time Cameron's despatch of 31 October reached the Foreign Office it had been joined by others he had written in November with the result that when those concerned despatch but several later despatches as well. The English text of the letter was not disclosed for some time,and until it was made public it was supposed to contain sevral fanciful demands and Suggestions, including a proposal of Marriage to the Queen."**ሲሉ ጽፈዋል::

በተለይ ይች አንዲት መሥመር እንግሊዞችን አስቆጥታ ትሆናለች:: ለምሳሌ **including a proposal of Marriage to the Queen."** የምትለው ቃል አጤ ቴዎድሮስ ንግሥት ቪክቶርያን ለማግባት

የጠየቁ መሆናቸውን ያብራራል:: ስዚህ የእንግሊዝን የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር መሥሪያ ቤት አበሳጭቷል:: ለዚህም ነው በተደጋጋሚ የተላከው ደብዳቤ ለንግሥቲቱ ሳይደርስ የቀረ::

የንግሥት ቪክቶርያ ባለቤታቸው መሞታቸውን አጤ ቴዎድሮስ ጠንቅቀው አውቀዋል:: ለዚህም ይሆናል "ላግባሽ" ያሉት? ስለዚህ ቅድሚያ ቆንስል ካሜሮን ደብዳቤያቸውን መልስ ለማምጣት ጥረት ባያደርጉም ቅሉ ሌሎች የውጭ ጉዳይ ጽፈት ቤቱ ሠራተኞች "እንዴት ንግሥታችንን ላግባሽ ብሎ ጠየቀ" ብለው ተቆጥተው ይሆናል ማን ያውቃል::

አባቶቻችን ሲተርቱ "በሴትና በቄስ የመጣ ጠብ አይበርድም" ይላሉ:: ምናልባት ይህን ቃል ብዙ ሰዎች አይቀበሉት ይሆናል:: ነገር ግን በሴት የመጣው ጠብ የሚለው በሔዋን ምክንያት የሰው ልጅ የደረሰበትን መከራ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል:: በቄስ የተባለው ቃል ደግሞ አንዱን ሃይማኖት ለመከፋፈል ምክንያት የሆኑት ጳጳሳትና ካህናት መሆናቸውን የዓለም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መመልከት ይቻላል::

ዛሬ ከሌላው ርቀን ሳንሄድ ከእኛ አገር ኢትዮጵያ ብንመጣ እንኳ ቤተ ክርስቲያን እየታመሰች ያለችው በጳጳሳት ምክንያት መሆኑን አእምሮ ያለው ሁሉ የሚስተው አይመስለኝም:: በቄስ እስተርን ምክንያት የመጣው ጥላቻ ሌሎች አውሮፓውያን ሁሉ እንዲታሰሩ ሁነዋል:: የታሰሩበት ምክንያት ቄስ እስተርን አጤ ቴዎድሮስን ወቅሶ በመጻፉና ወይዘሮ ፍላድ በጻፉት ደብዳቤ ምክንያት ሌሎች እንዲታሰሩ አደረገ::

ቀደም ብሎ አጤ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቪክቶርያ ልከውት የነበረው ደብዳቤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አፍኖት የነበረው ሁሉም ተሰብስቦ ለንግሥት ቪክቶርያ ተሰጣቸው:: እርሳቸውም አጤ ቴዎድሮስ የጻፉላቸውን ደብዳቤዎች መልሳቸውን በለሰለሰና በሚያግባባ መልክ ጻፉላቸው:: ነገር ግን የአጤ ቴዎድሮስን ጥያቄ የሚመልስ የእጅ ጥበበኞችና መሣሪያ አምራቾች ይላክላቸው የተባለውን የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤቱ አልተቀበለውም ነበር::



ሆርሙዝ ራሳም ከኤደን ወደ ኢትዮጵያ ምጽዋ ገብተው ለአጤ ቴዎድሮስ መምጣታቸውን ደጋግመው ደብዳቤ ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስ ግን ና ወይም አትምጣ የሚል መልስ ተሎ አልላኩላቸውም:: ሆርሙዝ ራሳም ግን ደጋግመው ደብዳቤ ከመጻፍ አልተቆጠቡም:: ኋላ ተፈቅዶላቸው ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ተገናኙ::

አጤ ቴዎድሮስም በክብር ተቀብለው አስተናገዱአቸው:: ከንግሥት ቪክቶርያ የመጣላቸውን ደብዳቤ እና የሜዳ መነጽር ሰጥተው ከቆንስል ካሜሮን ጋር የተፈጠረውን ችግር አንድ ባንድ ዘርዝረው አስረዷቸው:: በእርግጥ ራሳም የፕላውድን ያክል ባይሆኑም እንደ ካሜሮን ባይከፉም አጤ ቴዎድሮስ የሚፈልጉትን ለማወቅ ጊዜ የወሰደባቸው አይመስልም::

<u>ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ ከ1778-1967 ዓም</u> የተባለው መጽሐፍ ገጽ 36 "ቤተ እሥራኤልን ወንጌል ሲሰብኩ የነበሩ ሚሲዮናውያን የንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድና ድጋፍ ሳይለያቸው፤ ስብከታቸውን ያለችግር ያከናውኑ ነበር:: ከሚሲዮያውያኑ አንዱ ቀሲስ ስተርን ወደ እንግሊዝ አገር ለመመለስ ንጉሠ ነገሥቱን ተሰናብተው ጉዟቸውን ይቀጥላሉ::"

"ጥቂት ቀናት ከተጓዙ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ በሌላ አቅጣጫ ተጉዘው የሠፈሩበትን በሩቅ ሲያዩ አቅጣጫቸውን ለውጠው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሠፈር ይሄዳሉ:: ሠፈር እንደደረሱ ከአጋፋሪው ወይም ከእልፍኝ አስከልካዩ የቤተ መንግሥት ወግና ሥርዓት ተከትለው ቀጠሮ ሳይጠይቁ፤ ተንደርድረው ከነትጥቃቸው እልፍኝ ይገባሉ:: በሁኔታው የተገረሙት ንጉሠ ነገሥት ለምን ቀጠሮ ሳይቀበሉ እንደገባ ቢጠይቋቸው ቀሲስ ስተርም ሆነ አስተርጓሚው አሽከራቸው የሚያረካ መልስ አልሰጡም::"

"የቀሲስ ስተርን ድፍረት አስተርጓሚው ጌታውን የቤተ መንግሥቱን ደንብ ባለማስጠናቱ ነው ብለው ንጉሠ ነገሥቱ አመኑ:: ርእሰ ብሔሩን በውጭ አገር ሰው በማስደፈሩ አስተርጓሚው ወዲያው እንዲገረፍ አዘዙ:: ቀሲስ ስተርን የአሽከራቸውን ስቃይ ሲያዩ ጣታቸውን ነከሱ:: ጣታቸውን በመንከሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ እንደተደፈሩ ቆጥረው ቀሲስ ስተርንን አስገረፏቸው::"

“ከዚያ ሌሎች ፈረንጆች በተንኮል በሚጠረጥሩት በባርዴል ጥቆማ ጓዛቸው ሲበረበር ቀሲስ ስተርን የደረሱት Wanderings Among the Falashas in Abyssina Together with the Description of, the Countrv and Its Various Inabitants ትርጉም “በአበሻ አገር ከፈላሻዎች ጋር መባዘንና የንዋሪውና የአገሪቱ መግለጫ”የተሰኘ መጽሐፍ ተገኘ:: መጽሐፉ ሲመረመር ንጉሠ ነገሥቱ የኮሶ ሻጭ ልጅ፤ኢትዮጵያውያንም ጨካኝ ሕዝቦች እንደሆኑ የሚገልጽ ጽሑፍ ተገኘበት:: በዚህም ሳቢያ ጓዛቸው በድጋሚ ሲበረበር ንጉሠ ነገሥቱን የበለጠ የሚያስቆጣ፤ሚስስ ፍላድ የጻፉት ደብዳቤ ተገኘ::

በደብዳቤው ውስጥ ንጉሠ ነገሥቱን ነፍሰ ገዳይ አድርገዋቸዋል:: ይባስ ብሎ ሌላው ሮዜንታል የተሰኘው ሚሲዮናዊ ስለ ንጉሠ ነገሥቱ የግል ሕይወት የጻፈው የነቀፋ ደብዳቤ ተገኘ:: ንጉሠ ነገሥቱ በታላቅ አክብሮት የተንከባከቧቸው አውሮፓውያን ስለ ሕዝባቸውና ስለእርሳቸው የነበራቸው ንቀትና ጥላቻ ስለአስቀየማቸው ውለታ ቢሶቹን ያለ ርኅራኄ እንዲቀጡ ወስነው ቀሲስ ስተርንና ሮዜንታል በእግር ብረት ታሰሩ:: ሚስስ ፍላድ በሴትነታቸው ምክንያት አስተያየት ስለተደረገላቸው፤የግብረ አበሮቻቸውን ጽዋ አልቀመሱም:: ከዚህ በኋላ ሌሎቹም አውሮፓውያን በጥርጣሬ ዓይን ይታዩ ጀመር” ሲሉ ጽፈዋል::

ሚሲዮናውያን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል እየሰበኩ ሕዝቡን አያከብሩትም:: ዛሬም ቢሆን እኛ ኢትዮጵያውያን የምናመልክበትን የአምልኮት ቦታ ሳይቀር ይነቅፋሉ:: ይህ ሴራቸው ደግሞ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ነው:: እናንተ አጤ ቴዎድሮስ በነበሩበት ዘመን ሁናችሁ ይህን የመሰለ በሕዝቡ ላይ ንቀት የሚያሳይ ሰው ብታገኙ ትበሳጫላችሁ:: ደግሞም በዛሬው አመለካከታችሁ ሳይሆን የዛሬ 150 ዓመት በፊት ሁናችሁ ብትመለከቱት ምናልባት አጤ ቴዎድሮስ ካደረጉት በላይ ሳትጨክኑ አትቀሩም:: ለዚህ ነው “አባቶቻችን በሴትና በቄስ የመጣ ጠብ አይበርድም” ያሉት:: አዎ በቄስ ስተርንና በወይዘሮ ፍላድ የተጻፈው አጤ ቴዎድሮስን በማበሳጨቱ ሌሎች አውሮፓውያንም በያሉበት እየተለቀሙ ታሰሩ::



# ምዕራፍ 4

## የውጭ ሃይማኖተኞችና አጤ ቴዎድሮስ!

የውጭ ሃይማኖት የሚለውን ምዕራፍ ስጽፍ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ከምጀምር ወደ ኋላ ተመልሼ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተንኮል ሴራ በፈላስያን ስም የተስደዱት መነኮሳት መምጣት ከጀመሩበት ጀምሮ መጥቀስ አስፈላጊ ይሆናል:: ክርስትና ሃይማኖት ከተመሠረተ ጀምሮ ኢትዮጵያ ገብቶ ኑሮአል:: ክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ተስፋፍቶ መኖሩ እንዳለ ሁኖ የውሸት ድርሰት “አባ ሰላማ ካሣቴ ብርሃን ክርስትናን አመጣልን” የሚለው ትረካ ከእውነት የራቀ ነው::

አባ ሰላማ ያመጣልን ክህነትን ነው:: ክርስትና ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት ሁኖ የታወጀው በ330 ዓም ሲሆን ከዚያ በፊት በሌላው ክፍለ ዓለም በክርስትና አስተማሪዎች ላይ ብዙ ችግር ሲደርስባቸው ነገር ግን ከ12 ሐዋርያት 6 በኢትዮጵያ ሲያስተምሩ ምንም ችግር አልደረሰባቸውም ነበር::

<u>የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 688-689 “የኢትዮጵያ ነገሥታት ከጥንት ጀምረው ሀገራቸውን አስከብረው ባሕር ማዶ እየተሻገሩ ሲያስገብሩ ሲያንቀጠቅጡ የነበሩ ሲሆኑ በኋላ ኢትዮጵያ በሀገር ውስጥ በተነሣው ብጥብጥና በውጭ ሀገር መንግሥታት ተፅዕኖ የተነሣ በሀገር ውስጥ ኅብረት ጠፍቶ እርስ በርስ በመበጣጠስ ምክንያት የተነሣ ኢትዮጵያ ወደ ኋላ ወደ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ወድቃ ብትገኝም የአንድነት ምልክት የነበረውን የዘውድ መንግሥት እንደያዘች እስከ እኛ ዘመን ደርሳ ትገኛለች::”

“በጎንደር ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ላይ ዘመነ መሳፍንት በተባለው ዘመን አርቀው ማሰብ የማይችሉና በትምህርት ብስለት የሌላቸው መሳፍንት በየቦታው እየተነሡ ሕዝቡን እርስ በርሱ እያዋጉ የኢትዮጵያን አንድነት ቢያናጉም አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያ በአንድ ዘውድ በአንድ መንግሥት መመራት ይገባታል ብለው ስለተነሡ የኢትዮጵያ አንድነት መሠረቱ ተጠብቆ እስከ ጊዜያችን ደርሷል::”

"በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ኤውሮፓውያን የቅኝ ግዛት ያስፋፉበት ወቅት ስለነበረ ኤውሮፓውያን ኢትዮጵያን ተቀራምተው ለመያዝ በነበራቸው እቅድ መሠረት በሃይማኖት ስም ሚሲዮናውያንን ወደ ኢትዮጵያ ልከው ብዙ የተንኮል ድርጊት ሲፈጽሙ ነበር። አጤ ቴዎድሮስ የኤውሮፓውያንን ተንኮል በሚገባ ተረድተውት ስለነበር ሚሲዮናውያኑን ወደ ኢትዮጵያ ለምን መጣችሁ?"

"ብለው ጠየቋቸው። ሚሲዮናውያኑም የክርስትና ሃይማኖትን ለማስተማር አሉ። አጤ ቴዎድሮ በየት በኩል መጣችሁ? ብለው ጠየቁ። ሚሲዮናውያኑም በግብጽ በኩል አልፈን መጣን አሉ። አጤ ቴዎድሮስም ከግብጽ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ የሚገኘውን እስላም አስተምራችሁ አጥምቃችሁ ነውን ኢትዮጵያ የደረሳችሁት? ብለው እነዚህን ሰላዮች ከኢትዮጵያ አባርልኝ ከኢትዮጵያ ስንዝር መሬት ቀርቶ በእግራቸው ላይ የሚገኘውን አቧራ እንኳ ከእግራቸው ላይ ሆኖ ባሕር ተሻግሮ እንዳይሄድ ምፅዋ ሲደርሱ እግራቸውን አጥባችሁ ሸኟቸው ብለው አዘዙ" ሲሉ ዶ/ር ሀብተ ማርያም አሰፋ ጽፈዋል።

<u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 34" ሚሲዮናውያኑ የመጡት ወንጌል እንሰብካለን ፍቅር እናስፋለን ብለው ነበር። ሺ ከአምስ መቶ ዓመት ክርስትናን ተቀብሎ በቆየ አገር ወንጌል እንሰብካለን ማለት ግን ለቴዎድሮስ አጉል መመጻደቅ ሆኖ ታየው" ሲሉ ጽፈዋል።

ሊቀ ጠበብት ባሕሩ ዘውዴ እንዳሉት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የአውሮፓውያን ክርስትናን እናስተምር ማለት የማይዋጥላቸው ከመሆኑም በላይ በትክክል ክርስትናን ለማስፋፋት ከሆነ ኢትዮጵያ ከመምጣት ይልቅ አውሮፓ ውስጥ የተስፋፍውን እስላም አስተምረው ክርስቲያን ለምን አያደርጉም ነበር? ይህ የሰላይ ሃይማኖት ፀረ ኢትዮጵያ አንድነት መሆኑን እንኳን የውጭ ኃይሎች ይቅርና ዛሬ የራሳችን ወንድሞቻችን የአመጽ ሃይማኖት ተቀብለው በጥቅም የኢትዮጵያን አንድነት የካዱ መሆናቸውን አስተውሏቸው።

አጤ ቴዎድሮስ የካቶሊክን ሃይማኖት የተቀበሉ አባ ገብረ ሚካኤል የሚባሉ መነኩሴ ቢያስቸግሯቸው "የሮማ ወርቅ አታሎህ እንደሆነ እኔ አብልጬ ልስጥህ ወደ ጥንቱ ሃይማኖትህ ተመለስ" ብለው



ለምነዋቸው ነበር። ነገር ግን አባ ገብረ ሚካኤል አልመለስም በማለታቸው ታስረው ሙተዋል። የሮማ ቤተ ክርስቲያንም "ብፁዕ" ብላቸዋለች።

አጤ ቴዎድሮስ የአውሮፓን ሃይማኖት ሴራ ተረድተውት ነበር። ለምሳሌ ደጋግመው የሚሉአቸው "የአውሮፓ ሐሳብ ለእኛ ሰውር አይደለም። አገር ለመያዝ ከፈለጉ መጀመሪያ ወንጌላዊ ሰባኪ ተብሎ ሰላዩን ቆንስል ይሾማሉ። ከዚያም የሰላይ ዘር ይበዛል። ቆንስሉንና ዝርያውን የሚጠብቅ ጦር ይላካል። እንዲህ ያለ ነገር በአገሬ ላይ እንዲካሄድ አልፈቅድም። እኔ የሂንዱሴታን ራጅ አይደለሁም። ቆንስል ከሚልኩብኝ ይልቅ ጦር ቢላኩብኝ እመርጣለሁ "እያሉም ይናገሩ ነበር።

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጭር ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 76 "አጤ ቴዎድሮስ ከምዕራባውያን ጋር ለመጣላታቸው ምክንያት ከሆኑት ነገሮች አንዱ ለኦርቶዶክስ ቀናዒ መሆናቸው ነው" ሲሉ ጽፈዋል። ቀሲስ ዘመነ ትክክል ናቸው። ነገር ግን እንደእርሳቸው የተረዱ ብዙ ካህናት ያሉ አልመሰለኝም።

በነገራችን ላይ አጤ ቴዎድሮስ የእስላም ሆነ የክርስቲያን አስተማሪ ከውጭ አገር መጥቶ ሕዝባቸውን እንዲያስተምርባቸው አልወደዱም ወቅቱ የአውሮፓ ሰላይ ሃይማኖት ድርጅቶች በአፍሪካ የተሰማሩበት ወቅት ስለነበር የሰላዩ ሃይማኖት አስቀድሞ የሚገድለው የማንነት ምንጭ እምንትን ነው። ይህን በመረዳታቸው አጤ ቴዎድሮስ ከላይ እንደተነበበው እስላም ሆነ ክርስቲያን የራሱን ሃይማኖት አጥብቆ መያዝ ይኖርበታል የሚለው ፍልስፍናቸው ዛሬ ያሉ የምንቸገረኝ መሪዎች ከሚያደርጉት የተለየ መሆኑን መመልከት ይቻላል።

<u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966</u> በተባለው መጽሐፉ ገጽ 40"የስብከት ሥፍራቸውንም ቢሆን በኦርቶዶክስ አማንያን ዘንድ እንዳያደርጉ ተከልክለው በፈላሾችና በመሳሰሉት ያልተጠመቁ ሕዝቦች ዘንድ መወሰን ነበረባቸው። እንደ ደብተራ ዘነብ ያሉ አንዳንድ ዋነኛ ሰዎችን ወደ እምነታቸው መቀየር ቢችሉም የካቶሊኮችን ያህል መስፋፋት አልቻሉም።

እነዚህ የውጭ ሃይማኖቶች እንኳን በዚያ ወቅት ዛሬም ቢሆን ተከታያቸው እንዲሆን የመለመሉት ኢትዮጵያዊ ሰው የኢትዮጵያን አንድነት እንዲያስጠብቅ ፍላጎት የላቸውም፡፡ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ከሁሉም ይበልጥ ሴራ ያሴረው ስተርን የተባለው ጀርመናዊ ትውልዱ ይሁዳዊ ነው፡፡ እስተርን ሲወለድ የነበረው ሃይማኖት ይሁዳ ሲሆን ክርስትና የተጠመቀው በእንግሊዝ አገር ነው፡፡

በተለይም ኢትዮጵያ መጥቶ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ለማስቀየር ያደረገው ጥረት ሳይሳካለት በመቅረቱ ተናደደ፡፡ እንዳይሳካለት ያደረገው ዋናው ነገር ደግሞ አጤ ቴዎድሮስ መሆናቸውን ተረዳ፡፡ በዚህ ምክንያት ያለ ስማቸው ስም ሰጥቶ ያለ አመላቸው አመል አውጥቶ ብዙ ነገር የጻፈና ያጻፈ እርሱ ነው፡፡ ይህ በውጭ ሃይማኖት ድርጅቶች ፀረ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሴራ ማሴር የተጀመረው ቀደም ብሉ ነው፡፡ ዛሬስ እንዲያውም ብሶ የኛው ወንድሞች ሲያስተጋቡት መመልከቱ ያሳዝናል፡፡

እሱባለው በለጠ የገሀሃነም ደጆች ፕሮቴስታንታዊ ጅሀድ በኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶነት ላይ ሲፋፋም በተባለው ቅጽ 1 መጽሐፋቸው ገጽ 315 "ሃይማኖትን መካድ ለመጭው ትውልድ ባርነትን ማውረስ ነው፡፡ ይህ አመለካከት ኢች አይ ቪ ኤድስን ለልጅዋ ከምታስተላልፍ ሴት በምን ይለያል? እናት ፈልጋ ልጇን በገዳይ ቫይረስ አትበክልም፡፡"

"አእምሮዋ ጤነኛ የሆነ እናት መጤ ሃይማኖታዊ ስም ያለው ተላላፊና ማንነትን ገዳይ የእምነት ቫይረስ ግን እናት እያወቀች ለልጅዋ የምታስተላልፈው በሽታ ግኝ ነው" ሲሉ ጽፈዋል፡፡ ነጮች አዲሱ ፈሊጣቸው ዛሬ ነባሩን ሃይማኖት ማስካድ ነው፡፡ አጤ ቴዎድሮስ የዛሬ 150 ዓመት ገደማ ይህን ሴራቸውን ነበር በጽኑ የተዋጉት፡፡

ማኅበረ ወይስ ማደስ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 101 "ሕዝብ ያለ አገር አይኖርም፤ለዓላማነቱ የተከበረ አገር ካለ የተከበረ ሕዝብ ይኖራል፡፡ በኢትዮጵያም በሌላው ክፍለ ዓለምም ስለ አገር ክብርና ለዓላማነት ብዙ ሰዎች ተሰውተዋል ብዙ ተሠውተዋል፡፡ ፕሮቴስታንቶች ግን



አገር ስለሚባለው ነገር ምንም ዓይነት ስሜት አይሰጣቸውም፡፡ አገር ኖረ አልኖረ ተከበረ አልተከበረ ተደፈረ አልተደፈረ፤አያሳስባቸውም፡፡ በመሬት ውስጥም ሆነ ውጭ ስላለው አስደናቂ የተፈጥሮ ውበት አያስደንቃቸውም፡፡ አገር ቢወረር ቢደፈር ምንም አይ መስላቸውም፤ እነርሱ ብቻ ደኅና ይሁኑ" ይሉና "ቅርሶች አምልኮ ባይገባቸውም ክብርና እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል፤ የፕሮቴንታንት አስተማሪዎች የሆኑ የፈረንጅ ሚስዮናውያን አገራቸውን ታሪካቸውንና ቅርሳቸውን ምን ያህል እንደሚወዱና እንደሚንከባከቡ በመገናኛ ብዙኃን የምናየውና የምንሰማው ነው፡፡"

"የሚያሳዝነው ግን ፈረንጆች ወደ ኢትዮጵያ በሚሲዮንነት ሲመጡ ታሪክና ቅርስ ከንቱ እንደሆነ ማስተማራቸው ነው፡፡ በዚህ ትምህርት አእምሮአቸው የተሰለበው ኢትዮጵያውያን ፕሮቴስታንትም ስለ ታሪክና ቅርስ ያላቸው አመለካከት በጣም የሚያሳዝን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክና ቅርስ ጥላቻ ያደረበት አንድ ኢትዮጵያዊ ፓስተር በአንድ የጸሎት ፕሮግራም ላይ ሲጸልይ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ! የታሪክና የቅርስን የባህልና የሥርዓትን ፍቅር ከዚህ ሕዝብ አእምሮ ታስወጣ ዘንድ በኢየሱስ ስም እለምንሃለሁ ብሉ ጸለየ" ሲሉ ጽፈዋል፡፡ እነኚህ ሰዎች አገር አፍቅሮቱንና ባህልን መለየት አይችሉም፡፡ የምንለብሰው ልብስ ጥለቱ ከዘርፉ ያለው ከመጽሐፍ ቅዱስ የታዘዘ መሆኑን አልተገነዘቡም፡፡ እነሱ ከሚያነቡት 66 መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ልስጣቸው፡፡

<u>ኦሪት ዘኍልቁ</u> 15፥37 "እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው-ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በላቸው፡፡ እነርሱም ትውልዶቻቸውም በልብሶቻችሁ ጫፍ ዘርፍ ያደርጉ ዘንድ በዘርፉም ሁሉ ላይ ሰማያዊ ፈትል ያድርጉ ዘንድ እዘዛቸው፡፡ የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ ሁሉ ታስቡና ታደርጉ ዘንድ እርስዋን በመከተል ያመነዘራችሁባትን የልባችሁንና የዓይናችሁን ፈቃድ እንዳትከተሉ ትእዛዜን ሁሉ ታስቡና ታደርጉ ዘንድ ዘርፍ በልብሳችሁ ላይ እንዲታይ ይሁን፡፡ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ አምላክ እሆናችሁ ዘንድ ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ" ይላል፡፡

ከዚህ በላይ የተነበበው መጽሐፍ ቅዱስ እስከዛሬ ድረስ የባህል ልብስ መልበስ የእግዚአብሔር ትእዛዝ መሆኑን ወንድሞቼን

አልተረዱትም። ቤተ ክርስቲያን ሲኬድ የአገር ልብስ መልበስ ነጩር አድርገው ይመለከቱታል። ታዲያ የተሳሳቱ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ወይስ ሌሎች? ደጋግሜ የምለው ነገር አለ። ያም የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የሚያስጠሏት ካህናቷ እንጅ እምነቷ ግን በጣም ግልጽና እውነተኛ ሃይማኖት ናት።

ዲያቆን አሐዱ አሰረስ የዛሬዋ ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 75 "መናፍቃን ኢትዮጵያን አብዝተው የሚፈታተኗት የሕዝቡን አንድነት የሃይማኖቱን ጽናት ተመልክተው ነው። በተለይም ኢትዮጵያ ያላት ታሪክ በሙሉ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመገኘቱ ሕዝቡ ታሪኩን ቅርሱንና ባህሉን ጠብቆ በመኖር ለየትኛውም አገር ለቅኝ ግዛት ምቹ ባለመሆኑ አጥብቀው ቤተ ክርስቲያናችንን እንዲጠሏት ሆኖአል" ሲሉ ጽፈዋል። ይህ ትክክለኛ ታሪክ ነው።

ዛሬም እየተደረገ ያለ መሆኑን ሕሊና ያለው ሰው የሚረዳው ሀቅ ነው። የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ቀደም ሲል ጀምራ የኢትዮጵያን አንድነት ስትፈታተን የነበረች ናት። ዛሬ ተሳክቶ የእግራቸው ማረፊያ አነ አባ ማስያስ አሰብ ራስ ገዝ አስተዳደር ላይ 12 ጋሻ መሬት ከገዙ ጀምሮ የኢትዮጵያ አንድነት ተናጋ።

የአድዋ ጦርነት በዳግማዊ አጤ ምኒልክና በባለቤታቸው በእቴጌ ጣይቱ ብጡልና በሌሎች ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ድል ሲመታ አውሮፓ ተንጫጫ በተለይም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የተማረኩትን ምርኮኞች ለማስፈታት የሮማው (ፖፕ) 13ኛ ሊዮን እንዲህ ሲሉ ጽፈው ነበር።

"ለኃያሉ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለዳግማዊ ምኒልክ! የምመክርዎትን እመዛገኑው የልግሥና ሥራ እንዲያደርጉ እለምንዎታለሁ። የዚህ የዘመቻ ድል በእጅዎ ብዙ የኢጣሊያ ምርኮኞች አሳልፎ ሰጥቶዎታል። የእነዚህም የኢጣሊያኖች መማረክ በዚህ አገር ያሉትን በሺ የሚቆጠሩትን የእናቶቻቸውንና የሚስቶቻቸውን የልብ ኀዘንና ጭንቀት ከማበርከት በቀር ምንም ያህል የገርማዊነትዎን ኃይልና ዝና ሊያስፋፋ አይችልም። እኛም ክቡራችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበልነው አደራ እንደ ልጆቻችን ያህል እንወዳቸዋለንና እነዚህን ምርኮኞች በቶሎ በነጻ እንዲለቋቸው



በቅድስት ሥላሴና በድንግል ማርያም ወይም በዓለም ካለው በሚወዱት ስም እለምንዎታለሁ።"

"ኃያሉ ንጉሥ ሆይ! ይህንን የምለምንዎትን እንደ ክፉ ሰው እምቢ ማለትዎ በመንግሥታት ፊት የተገለጸ አይሁን። ይህቺንም የተከበረች ደብዳቤዬን ለምስክር እታሪክዎ መዝገብ ያግቧት። በዚህም በሚያደርጉት የቸርነት ሥራ ርኅሩኅና የሁሉ አባት የሆነው እግዚአብሔር ይክስዎታል።"

"ከዚህም በቀር በብዙ የሚቆጠሩ ሰዎች ሊያመሰግኑዎ ድምጻቸውን ያነሣሉ። ከነዚህም የመጀመሪያዎቹ እኛ ነን። ይህ የልመና ቃል እንዲፈጸም በተስፋ ከመጠባበቅ ጋር ልዑል እግዚአብሔር በንጉሠ ነገሥቱና በቤተ ሰቦቹ ላይ በረከቱን እንዲያወርድ እንጸልያለን። ሮማ ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ግንቦት 11 ቀን 1896" ሲሉ ጽፈው ነበር።

በዚህ በአድዋ ድል አውሮፓውያን የተበሳጩ ቢሆንም በተለይ የኢጣልያ መንግሥትና የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት በኢትዮጵያ ላይ ቂም በመያዝ መቆየታቸው አይዘነጋም። የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ለ40 ዓመታት ሲዘጋጅ ኑሮ በ1928 ዓም ኢትዮጵያን ለመውረር ሲነሣ የሮማ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወረራውን ደግፈው የሚዘምተውን ወታደር ባርከው ከደረታቸው ያለውን መስቀል እያወለቁ አስረከቡ።

እነዚህ ጳጳሳት የሰው ልጅ ደም እንዲፈስ ሲመርቁ የዓለም ሕዝብ የታዘባቸው ቢሆንም ደፍሮ ፖፑን የተቃወመ የለም። እውነትና ግልጽነት ያጠቃቸው መጽሐፍ ቅዱስን ያጠኑ የኢትዮጵያውያን መደፈር ያንገበገባቸው አንድ ጋዜጠኛ ብቻ ከዚህ የሚከተለውን ጽሑፍ መጻፋቸው በታሪክ ለዘላለም ሲወሳ ይኖራል።

እኒህ ሰው የሰዊድን ተወላጅ ሲሆኑ ስማቸው ኢሳክሲንድሩም ይባላሉ። እርሳቸው በወቅቱ የጻፉትን ሙሉውን አንባብያን እንዲያውቁት ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከተባለው መጽሐፍ ገጽ 11 19 የተገኘውን ይሆናል በአባሪ ቁጥር 3 ይመልከቱ።

Richard Noll <u>When Catholics Die</u>- በተባለው መጽሐፋቸው page 135 " The Pope Wants to be in Charge of the emerging one-World religion. Heading the global Church. however, is just a stepping stone toward accumulating greater World-wide polical powre.

ትርጉም "ፖፑ በማደግ ላይ ያለው አንድ የዓለም ሃይማኖት ኃላፊ መሆን ይፈልጋሉ:: የዓለምን ቤተ ክርስቲያን ለመምራት የሆነው ሆኖ የበለጠ ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ሥልጣን ለመሰብሰብ መረማመጃ ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

ወደ ኋላ መለስ ብለን በ451 ዓም የነበረውን የሃይማኖት ልዩነት ያመጡት ሮማውያን ናቸው:: በተለይም የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ሃይማኖት በ1632 ዓም አጤ ፋሲል "ሃይማኖታችሁን ይዛችሁ አገሬን ልቀቁ" ብለው የፖርቱጋልን ካቶሊክ ማባረራቸው አይዘነጋም:: በነገራችን ላይ ሮማውያን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም ዙሪያ ይህ ፍላጎታቸው እንደነበር አይካድም::

Christoper Knight and Robert Lomas <u>The Second Messiah</u> በተባለው መጽሐፋቸው page "126 The Roman Catholic Church had always considered that it had the right to rule the temporal affairs of the World.

ትርጉም "የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም ራሱን የዓለማዊ ጉዳዮች ገዥ እንደሆነ ያስባል"ሲሉ ጽፈዋል:: በዚህ ስበብ ሌሎች አውሮፓውያን በሃይማኖት ተከፋፍለው የግል ችግራቸውን ይዘው ለእኔ ለእኔ እየተባባሉ ሁሉም ወደ ኢትዮጵያ ፊታቸውን አዞሩ::

በተለይ ካቶሊኮች በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ያደረጉት ሴራ እጅግ የሚያሳዝን ነው:: የኢትዮጵያን መሳፍንት ወደ ሮማ ቤተ ክርስቲያንና ወደ ኢጣልያን መንግሥት ብሎም ወደ ፈረንሳይ መንግሥት ሂደው የጦር መሣሪያ ማግኘት እንዲችሉ አስጠንቅረው መክረዋል:: ለዚህም ከላይ ደጃዝማች ንጉሴ ወልደ ሚካኤልን እንዲሳሳቱ ያደረጉ እነሱ ናቸው



በነሱ ስበብ ደጃዝማች ንጉሴ ብቻ ሳይሆኑ ደጃዝማች ካሣ ምርጫም እንዲዝቡላቸው አደረጉ:: አትርሱ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ምክንያት ጣልያን ኢትዮጵያ መግባቱን:: ካቶሊኮች ዛሬ የኛን ወንድሞች አሠልጥነው ለቀዋቸዋል:: በኢትዮጵያ ስም ይነግዳሉ:: ከዚህ አሜሪካ ውስጥ አንዴ የሆነውን ታሪክ የነገሩኝ ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ናቸው::

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ <u>በሰልክ የነገሩኝ</u> "በ1980 ዓም አርማንያ በመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት ብዙ ሕዝብ አለቀ:: አርመኖች በያሉበት ተደራጁ በተለይም እንት ቤተ ክርስቲያንን ጋበዙ:: ዋሽንግተን ዲሲ በነበረው ዝግጅት እኔ ሄድኩኝ:: ከአርመን ጳጳስ ቀጥሎ እንት ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳትና ወኪሎች ተቀመጡ:: ከነሱ ቀጥሎ ሌሎች ክርስቲያኖች ተቀመጡ:: ባንድ ወገን ደግሞ የአሜሪካ የመንግሥት ባለሥልጣናት ተቀመጡ:: ታዲያ ስንገባ ስማችን ያለበት ባጅ ተሰጥቶናል::

ከባጃችን ጋር ያለው ቁጥር ከምንቀመጥበት ወንበር ቁጥሩ አንድ ነው:: የእኔን ወንበር አንድ ኢትዮጵያዊ የካቶሊክ ቄስ ቀድሞ ሄዶ ተቀምጦበታል:: እኔ በተሰጠኝ ቁጥር ከወንበሬ ስደርስ ቆሞ ብሏል:: የለኝ አግራሞ መቆም በመሆኑ ቆምኩኝ:: ወዲያው አስተናጋጁ መጣና "የት መጣህ? ብሎ ጠየቀኝ እኔም የመጣሁበትን ከነገርኩት ኋላ ወንበሬ መያዙን ነገርኩት:: ወዲያው ሄደና" የት ነህ ብሎ ለጠይቀው ኢትዮጵያዊ የካቶሊክ ቄስ ነኝ አለው:: አስተናጋጁም ይህ ወንበር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወንበር ስለሆነ ነሥ ብሎ አስነሣልኝ" ብለውኛል::

የጎን መጽሔት ጋዜጣ ሕዳር 12 ቀን 1992 ዓም "ሚሲዮናውያን ዛሬት ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ነበር:: አጤ ቴዎድሮስ ምን ጥበብ ስለተምሩናችሁ አሏቸው:: ቃለ እግዚአብሔር ማስተማር ንችላለን አሉአቸው:: አጤ ቴዎድሮስም ለንቱን ክርስቲያን ያልሆን ግር አልፋችሁ ከናንተ ቀድሞ ክርስትናን ለተቀበለ ሕዝብ ምን ቃለ ግዚአብሔር ታስተምሩታላችሁ? ንሳ ዓለሜ እዚያው ሺልባቸው ረስ ሸኘልኝ የትድበት ሀገሬን ትቢያ ያዘው እንዳይሄዱ ሚሲዮናውያን እየራገፉ ላኩልኝ ብለው አዘዙ:: በዚህ ምክንያት ዙ ሚሲዮናውያን ተበረሩ እንዳንዶቹ ግን መድፍ እንሥራለን ላላቸው [illegible] ላይ ያሠሯቸው [illegible] ሲሉ ጽፈዋል [illegible]

ከዚህ ላይ መወሳት ያለበት ታሪክ ደግሞ አለ:: ያም ለዚህ ሁሉ ችግር መሥኢው የኛዎቹ ካህናት መሆናቸውን መርሳት የለብንም:: መጽሐፍ ቅዱስን አስመልክቶ ጥያቄ ሲነሣባቸው ተሳድበው ከመሄድ ይልቅ ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ የማይሰጡ በመሆናቸው ነው::

የቤተ ክርስቲያን እውቀት ያላቸው ብዙ ሲሆኑ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀታቸው የበለጸጉ ትንሾች በመሆናቸው ነው:: ወንጌል እንሰበክ ብለው የሚመጡትን ሰዎች በቂ መልስ የማይሰጡአቸው በመሆኑ ራሳቸው አጤ ቴዎድሮስ ሃይማኖትን አስመልክቶ ይወያዩ እንደነበር እንግሊዞች የጻፉት መጽሐፍ ዋቢ ነው::

Darrell Bates The Abyssinian Difficulty በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 31 "He often came there to share their simple meals, and spent long hours talking to them both about practical matters and about questions of religious belief::

ትርጉም "አጤ ቴዎድሮስ የጠቢባኑን ተራ ምግብ ለመጋራት ዘወትር ይጎበኙአቸው ነበር:: ለረጅም ሰዓታት ስለ ወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታና ሃይማኖታዊ እምነት ያወያዩአቸው ነበር::" ሲሉ ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስ አገሪቱን ለማስከበር ወታደር ማደራጀትና የጦር መሣሪያ ማሠራት፤ ሌላም ሌላ አገርን አስመልክቶ መልፋት ብቻ ሳይሆን ሃይማኖትን አስመልክቶ ራሳቸው ይወያዩ እንደነበር ከዚህ በላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ያስረዳል::

## ምዕራፍ 5

### እንግሊዞች ጦር ወደ ኢትዮጵያ አዘመቱ፤

የእንግሊዝ መንግሥት ጦር ወደ ኢትዮጵያ ከማዝመቱ በፊት ቀድሚያ አጤ ቴዎድሮስን በመላ ሊያስገድሉ ጥረው ሳይሳካላቸው መቅረቱን አስመልክቶ በቅርቡ ካገኘሁት አንድ የታሪክ መጽሐፍ ለመረዳት ችያለሁ:: የአጤ ቴዎድሮስን ለጦር መሣሪያ ያላቸውን ስሜት በማወቃቸው ወደ ጎላ ረጭቶ የሚተኮስ ጠበንጃ መርተው ልከው እንደነበር ያብራራል:: የሚልበት ለእንግሊዞችና ለወደፊቱም



ታሪኩን ለሚያጠና ሰው መጽሐፉንና ገጹን መግለጽ ስለሚያስፈልግ ከዚህ በታች የምመዘግበው የታሪክ መጽሐፍ ይሆናል::

አለቃ ተክለ ኢየሱስ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 122 "የራሳምን መታሰር እንግሊዞች በሰሙ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስን ሊገሉ ጥበብ ፈለጉ:: በትተኩስ ተራግሚ ልብ ደቅታ የምትገድል አዲስ ዓይነት ጠበንጃ ሠርተው በረከት ሰደዱ:: አጤ ቴዎድሮስም ተቀብለው ሊተኩሰው ሳለ ጳጳሱ አቡነ ሰላማ አንተ መጀመሪያ አትተኩስበት በሌላ ሰው እጅ መጀመሪያ ይፈተን አለ:: ንጉሡ ግን ግድ ካልተኮስሁበት ብሉ አስቸገረው::"

"ጳጳሱም ገዘተው:: ከዚያ ጋሻ ጃግሬ አሽከር ነበረው ቢተኩሰው የጓሊት ረግጦ ልቡን ደቅቶ ገደለው:: ባሩዱን ሲቀምሙ ኃይለኛ አድርገው ቀምመውት ነው እንጂ ከጠበንጃው አይደለም:: አጤ ቴዎድሮስ ባሽኬቋ ሞት አዘኑ:: የምወደው አሽከሬ ሞቶብኛልና የልቅሶ ግጥም ያበርክቱልኝ ብሉ ወደ ደጃች ብሩ ላኩ:: ደጃች ብሩም ቅን አይመልስ ነበርና እንዲህ አለ::"

"አቡኑ ባይገዝት ያባሪያ ባይኖር
የሀበሻ መከራ ያልቅለት ነበር
ብለህ ንገርልኝ ብሉ ላከ" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህን ጥቅስ በሚመለከት ብዙ ጥናት የሚጠይቅ ይሆናል:: ምክንያቱም ጠበንጃውን ማን አመጣው? እንደዚያ የአጤ ቴዎድሮስን አሽከር ከገደለ ጠበንጃውን ያመጣው ሰው ሌላው ቢቀር መታሰር ነበረበት:: ስለዚህ ለወደፊቱ ታሪክ ሊያበጥረው የሚገባ በመሆኑ ባልፈው ይሻላል::

ሁሴን አህመድ ሜጀር ጀኔራል መሰዋዕትነት እና ፅናት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 14 "የእንግሊዝ ምክር ቤት ባስተላለፈው ውሳኔ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የአቢሲኒያው ንጉሥ ከደፈረን ሌሎች ቅኝ አገሮችን ለወደፊት መግዛት ሆነ ማስተዳደር የማንችልበት ደረጃ ላይ ስለምንደርስ ወታደራዊ ዘመቻ እንዲደረግና እሥረኞች እንዲፈቱ ትእዛዝ ሰጠ" ሲሉ ጽፈዋል::

የእንግሊዝ ምክር ቤት አጤ ቴዎድሮስ እስረኞችን ስላለቀቁ የጦር ኃይል ልከን ማስፈታት አለብን ብሎ ውሳኔ በማሳለፉ ጄኔራል ናፒር በተባለ አዛዥ የሚመራ ከህንድ ወደ ኢትዮጵያ 32.000 ጦር አዘመተ። ይህን ጦር ኢትዮጵያ ለማዝመት የፈጀው ገንዘብ በእንግሊዝ ታሪክ የመጀመሪያ ነው።

እንግሊዞች ወደ ኢትዮጵያ ጦር እንዲያዘምቱ የተገደዱት ለታሰሩት ዜጎቻቸው አስበው ሳይሆን ዋናው ዓላማቸው ወሬው ሕንድ ድረስ ዜጎቻቸው መታሰራቸው ተሰምቶ ስለነበር ቅኝ ግዛታቸው ሊያፈነግጥ እንዳይችል ለማድረግ በማሰባቸው ነው። ይህም ብቻ አይደለም ሌላው ደግሞ ቴዎድሮስን ከደበደቡ በኋላ ላይ ሌሎች እንዳይነሱ ዝም ማሰኘት እንችላለን ብለው በማሰብ እንጂ ለዜጎቻቸው ክብር ብቻ ተብሎ ታስቦ አልነበረም ዘመቻው።

<u>አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 257 "ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ መካ የሚሔዱ ኢትዮጵያውያን ምእመናን በየደረሱበት አገር የአበሻ ንጉሥ የእንግሊዝን ንግሥት አሽከሮች በሰንሰለት አስሮ ካስቀመጣቸው አራት ዓመት አለፈ እያሉ በማውራታቸው ወሬው እየተዛመተ በመላው ዓለም ተዳረሰ። የእንግሊዝ መንግሥትም ይህ ወሬ እንዳይሰማ ቢደብቅም ወሬው እየተስፋፋና እየገነነ ሄደ።"

"ሄንሪ ዱፍተን እንደጻፈው ከጅዳ እስከ ቻይና ግንብ ከኬፕ ጋርዲፉ እስከ ጉልድ ኮስት ተዳረሰ ይላል። ያኔ የእንግሊዝን መንግሥት ደካማ ነው እያሉ እንግሊዞችን ከገራቸው ለማስወጣት ይዶልቱና ያስቡ ጀመር። እንግሊዞች በየደረሱበት ሁሉ ይሰደቡና ይናቁ ጀመር። በያሉበትና በየደረሱበትም በማፌር አንገታቸውን ያቀረቅሩ ጀመር። በእነዚህ በእስረኞች ምክንያት ኢትዮጵያ በማትታወቅበት አገር ሁሉ ገነነኛ ሆነች። እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያ በኤሮፓውያኖች ምክንያት በመላው ዓለም ላይ ስሟ የተጠራው ሁለት ጊዜ ነው።"

"አንደኛው የቴዎድሮስ ኤሮፓውያኖችን ማሠሩ ሲሆን ሁለተኛው ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በኤሮፓውያን ላይ አድዋ መንደር ውስጥ ያስገኙት ድል ነው። የእንግሊዝ መንግሥት ከቴዎድሮስ ጋር ያለውን ግንኙነት በሰላም ለመጨረስ እንደማይቻል ካወቀ በኋላ የጦር እዋጅ አወጀ" ሲሉ ጽፈዋል።



ጦር ወደ ኢትዮጵያ እንደሚያዘምቱ ለአውሮፓ አገሮች ሳይቀር ተናግረው ነበር። ለዚህም ብዙ የአውሮፓ አገሮች ሰላዮቻቸውን መላካቸው አልቀረም። ምክንያቱም ኢትዮጵያን መሀል ድረስ ገብቶ ለማየትና ለማጥናት ከዚህ የሚሻል ጊዜ ሊኖራቸው አይችልምና ነው። ይህን አስመልክቶ የታሪክ ሰነድ እንዲህ ያብራራል።

<u>ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታኒያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ</u> -የተባለው መጽሐፍ ገጽ 65 "የእንግሊዝ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመውረር መወሰኑን አውሮፓ እንድትሰማ፣የቅኝ ግዛት ለማስፋት ፍላጎት ካላቸው አገሮች መካከል ፈረንሳይ፣ፕሩሽያ፣አውስትራልያ፣ስፔን፣ ሆላንድ ጣልያንና ቱርክ ከወረራው ትምህርት ለመቅሰም ከናፒየር ሠራዊት ጋር መኮንኖች ለመላክ ጥያቄዎቻቸውን ለእንግሊዝ መንግሥት ከየአቅጣጫው አቀረቡ።"

"የእንግሊዝ መንግሥት ጥያቄያቸውን በጥንቃቄ በማጥናት የቱርክ መንግሥት ሲቀር በተመልካችነት ብቻ ጦሩን አጅበው የሚዘምቱ ለፈረንሳይ ሦስት ለቀሩት ለእያንዳንዳቸው ሁለት በድምሩ አሥራ ሦስት ታዛቢ መኮንኖች ፈቀደላቸው። የቱርክ መንግሥት ጥያቄ ተቀባይነት ያላገኘው የኢትዮጵያን ገዥዎችና ባላባቶች በማስቀየም ከእንግሊዝ ጦር ጋር እንዳይተባበሩ ያደርጋቸዋል በሚል ስጋት ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

መችም በወቅቱ በእንግሊዞች ኃያልነት የተወሰደውን አቋም ለመተቸት አስቸጋሪ ነው። ምንም እንኳ ከአውስትራልያና ከአሜሪካን ከካናዳ ተደብድበው የወጡ ቢሆንም ሕንድን በበላይነት የሚገዙበት ወቅት ነበር። በዚህ ብቻ አላበቁም የቱርክ የበላይነት እየተናደ መጥቶ ስለነበር የዓረቡን ዓለም ባልስትንያን ጨምሮ ለመያዝ ሐሳብ እንደነበራቸው አይዘነጋም። በአፍሪካ ዙሪያ እንዲሁ እያንኳኩ ናቸው። ይህን ሰፊ አገር ሕንድን የምትገዛው የታላቋ ብሪታንያን ዜጎች በአንድ ባላደገ አገር በተለይም ደግሞ በወቅቱ በነበረው የእነሱ የበላይነት ዜጎቻቸውን አስሮ ያሉም ደግሞ ዲፕሎማቲክ ዝም ማለቱ ከባድ ነው።

በእርግጥ ለችግሩ መንሥኤ ዋናው በመጀመሪያ ቆንስል ካሜሮን ሲሆን ሌላው ደግሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴራቸው ነው። አጤ ቴዎድሮስ የጀመሩትን የወዳጅነት ደብዳቤ በሥርዓት

አስተናግደውት ቢሆን ኑሮ ይህ ሁሉ ችግር አይደርስባቸውም ነበር፡፡ ታዲያ ምን ይደረግ? ወቅቱ እነሱ የሚሰደቡበትም ጭምር ሆነ? በዚህ ሰዓት ያላቸው ምርጫ የመንና ግብጽ የሚቀመጠው ቆንስላቸው በተደጋጋሚ ባሳሰባቸው መሠረት ደጃዝማች ካሣ ምርጫን ማግኘታቸው ተዘርዝሯል፡፡

የልጅ ልጅ ነኝ ባዩ ደጃዝማች ዘውዴ "አጤ ቴዎድሮስን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው የከዳው" ብለዋል ከዲቪዲው የምስል ክር ላይ፡፡ ወያኔ መቸም ለምንም ለምን መላ አያጣም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴም መሪውን አልካደም፡፡ አገሪቱንና መሪውን ለውጭ መንግሥታት አሳልፎ አይሰጥም! አልሰጠም አልካደም፡፡ የካደ መኳንንቱ ሲሆን በተለይ ደጃዝማች ካሳ ምርጫ ዋናው ናቸው፡፡

## ምዕራፍ 6

## እንግሊዞችና ደጃዝማች ካሳ ምርጫ!

ራሳም ከታሰረ በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት አጤ ቴዎድሮስ የጠየቁትን ባለሞያ ለመላክ ተስማማች፡፡ ነገር ግን ቅድሚያ እስረኞች ምጽዋ መግባት አለባቸው ብላ ወሰነች፡፡ አጤ ቴዎድሮስ ደመወዝ የማይከፍሏቸው ከሆነ የእንግሊዝ መንግሥት ለመክፈል ፈርማለች፡፡ ዋናው ከእንግሊዝ አገር ምጽዋ ድረስ ከመጡ በኋላ ወደ አጤ ቴዎድሮስ መድረስ አልቻሉም፡፡ እንግሊዞች ባለሞያዎችን ወደ አጤ ቴዎድሮስ ከመስደዳቸው በፊት እስረኞች ምጽዋ መግባት አለባቸው ብላ ወስናለች፡፡ አጤ ቴዎድሮስ፣ደኅና መጥተው ነበር፡፡ ራሳምን በመያዝ ይዘው ሌሎችን እስረኞች ለመስደድ ከተስማሙ በኋላ አቅዋማቸውን ቀየሩ፡፡

እስረኞችን አልሰድም አሉ፡፡ ከዚህ ላይ ነው የእርሳቸው ስሁተት በመጀመሪያ ያቀዱት መልካም እቅድ ነበር፡፡ ምክንያቱም ራሳምን ይዘው ሌሎችን እስረኞች ልከዋቸው ቢሆን ኑሮ ምጽዋ ላይ ቀጭ ብለው የነበሩት ባለሞያዎች ኢትዮጵያ ገብተው አጤ ቴዎድሮስ ያቀዱትን መሣሪያ ማምረት ይችሉ ነበር፡፡



የእንግሊዝ መንግሥት ልኳቸው የነበረው የተለያዩ የእደ ጥበብ ባለሞያዎች ዓይነትና ብዛት መሐንዲስ ማቴው፣ኤድዋርድ ታልቢት የሚመራ አንድ መሐንዲስ፣አንድ አናጢ፣አንድ ልዩ ልዩ ዕቃዎች የሚሠራ፣ አንድ ጠበንጃ ሠሪ፣አንድ ብረት አቅልጦ የሚሠራ ሌላ ደግሞ ግምጃ ቤት ባለሞያ ብዛታቸው 7 ናቸው፡፡

አውሮፓውያንን አስረው አለቅ በማለታቸው ምክንያት እንግሊዞች ወደ ጦርነት ለመግባት ሲወስኑ ቅድሚያ አጤ ቴዎድሮስን ከሚጠሉት መኳንንቶች ጋር ለመወዳጀት ጥረት አደረጉ፡፡ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ሸፍተው የተቀመጡትን መኳንንቶች መርጦ የነሱ ሰው ማድረግ ትልቁ እቅዳቸው ሆነ፡፡

ለዚህም ደግሞ የታሰሩትና ያልታሰሩት አውሮፓውያን በየቦታው በአጤ ቴዎድሮስ ላይ የሸፈቱትን መኳንንቶች ስም ዝርዝርና የሚገኙበትን ቦታና በአካባቢያቸው ያላቸውን ተሰሚነት ዘርዝረው፣ ጻፉላቸው፡፡ በወቅቱ ለእንግሊዞች ይጠቅማሉ ተብለው የተመዘገቡት መኳንንቶች ስማቸው ከተጠቀሱት መኳንንቶች መካከል ሦስቱ የኢትዮጵያ ነገሥታት ለመሆን በቅተዋል፡፡

ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታኒያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 60 "የላስታው የዋግ ሹም ጎበዜ፣የትግራዩ ደጃዝማች ካሣ ምርጫ፣የወሎዎቹ እመቤቶች ወይዘሮ መስታውትና ወይዘሮ ወርቂት፣የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ፣የወልቃይቱ ጥሶ ጎበዜና የጎጃሙ ተድላ ጓሉ፣ተጠናክረው ነበር" ሲሉ ጽፈዋል፡፡

ደጃዝማች ተድላ ጓሉ ከእንግሊዞች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አላደረጉም፡፡ እንዲያውም እርሳቸው በጥቅምት 1860 ዓም ሳይሆን አይቀርም ያረፉት፡፡ ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜ ጎንደሬው ወልቃይት ሁነው አልገብርም አሉ፡፡

የአጤ ቴዎድሮስ ኃይል ቀንሶ ትንንሽ አውራጃዎችና ወረዳዎች እያስቸገሩ ሲመጡ አጤ ቴዎድሮስ በአንድ ልብ ወደ መቅደላ ሲገሰግሱ ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜ ጎንደርን አልፈው በለሳ ላይ መሸጉ፡፡ ከእንግሊዝ ጋር ያደረጉት ግንኙነት ድጋፍ ወይም ተቃውሞ የለም፡፡

ሌላው ዛሬ ደጃዝማች ዘውዱ ገብረ ሥላሴ "አጤ ቴዎድሮስን ለማስገደል እንግሊዝን መርተው የመጡ አጤ ምኒልክና ሌሎች ናቸው እንጂ አጤ ዮሐንስማ እንግዲያ መግባቱንስ ግቡ እንዴት ነው የምትወጡት? ብለው ጠይቀዋል" በማለት በዲቪዲው የገለጹት ትክክል አይደለም።

አጤ ምኒልክ እንግሊዝን መርቶ ለማምጣት ምንም የተጫወቱት ሚና የለም። እንግሊዞች ወደ መቅደላ ሲቀርቡ በአጋጣሚ ወሎ መሄዳቸው ግን ታውቋል። መቅደላ ቀርበው ሰንብተው ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል። ይህን በማድረጋቸው እንግሊዞችን መሩ ማለት ግን በታሪክ አይቻልም።

በተለይ ደጃዝማች ተድላ ጓሉ፤እንግሊዞችን መርቶ ለማስገባት ቀርቶ ደብዳቤ እንኳን ከእንግሊዞች አልደረሳቸውም። አጤ ቴዎድሮስን እጅግ ካስቸገሩ መኳንንቶች መካከል ዋናው እልህቸውን ያስጨረሱአቸው ደጃዝማች ተድላ ጓሉ ናቸው። በዚህ ጀግንነታቸው እንግሊዞች ስማቸውን ቢመዘግቡትም ቅሉ ደብዳቤ ከእንግሊዞች አልደረሳቸውም። በመሠረቱ እርሳቸው ያረፉት እንግሊዞች ሊመጡ 2 ወር ሲቀራቸው ነው።

ወይዘሮ መስታወትና ወይዘሮ ወርቂትም ቢሆን አስቀድመው ከእንግሊዞች ጋር ያደረጉት ምንም ዓይነት ተግባር የለም። እንግሊዞችንም መርተው አልመጡም። አጤ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ ከጀኔራል ናፒር ጋር መገናኘታቸው እንጂ ሌላ ያደረጉት ሴራ የለም። በመጠኑ ድጋፍ ሊያደርጉ ያቀዱት ደጃዝማች ዋግሹም ጎበዜ፤ ሲሆኑ እርሳቸውም በወቅቱ መቅደላ አካባቢ አልነበሩም።

አጤ ቴዎድሮስ ጎንደርን ሲለቁባቸው ደጃዝማች ተሶ ጎበዜ ቆላውን አስገብረው ጎንደርን እልፈው በለሳ ላይ መሸገው ስለነበር እርሳቸውን ለመውጋት ወደ ጎንደር ገስገሰዋል። ወርኑት ተፋናሞ ደጃዝማች ተሶ ጎበዜን ድል አድርገው ወዲያውኑ ወደ መቅደላ አልሄዱም።

ጀኔራል ናፒር "የምጠሩኝ መቅደላን ያረከቡኝ" ብሎ ቢልካባቸው ስላላመኑአቸው ሳይቀበሉ ቀሩ። በዚህ ምክንያት ጀኔራል ናፒር መቅደላን በፈረሰ አምባው ባለ ስቀር እሳት ለተመለሰ ጊዜ፤ ደጃዝማች ዋግሹም ጎበዜ በእርግጥ ወሰሉ ልከዋል



'ናልባት ለጀኔራል ናፒር፤ እህል ገዝቶ እንዲጠቀም ሳይፈቅዱለት ይቀሩም። ይህን ማድረጋቸው በእኔ ዘንድ እንግሊዝን መርተው 'ጥተዋል የሚለውን ለማግኘት የተጻፉትን ሰነዶች ብመለከት ቅርቡ እንደ ደጃዝማች ዘውዱ ገብረ ሥላሴና አንዳንድ የወያኔ ራስያን ከሚሉት በቀር ከቀድሞ ሰነዶች ሳገኝ አልቻልኩም።

ጃዝማች ካሣ ምርጫ፤ ግን ቀደም ሲል ጀምሮ አቅሞግቸው 'ሆኑ እንግሊዞችን መርተው መጥተዋል። ዛሬ ይህን ብሉ 'ጽሐፍ ቀርቶ በጨዋታ እንኳን ማንሣት በወያኔ ዘንድ "አገሌ ፀረ ግሬ ነው" ብለው እንደሚያወሩ አላጣሁትም። በመሠረቱ ጃዝማች ካሣ የኋላው 4ኛው አጤ ዮሐንስ በሠሩት ጀግንነት በረን ስንኮራባቸው በተሳሳቱት ስህተት ደግሞ አብረን ነው 'ናፍርባቸው እንጂ ዛሬ ወያኔ በሥልጣን ላይ ስላለ ብቻ ስማቸውን ታንሡ መባሉ ትክክል አይደለም።

anna Mantel-Nieko Kasa Aad Kasa ---page 196 Napier's my passon to Mekdela without trouble, Among this intrnal rce were wag shum gobeze from lasta and bezbiz kasa from gray two futuer emperors of Ethiopia. ሲሉ ጽፈዋል።

ኔራል ናፒር ጦር ያለ ምንም ስጋት ምጽዋ ላይ ጭንቱን አራግፎ ደጃዝማች ካሣ ምርጫ መልእክተኛ ላኩ። ደጃዝማች ካሣ ርጫም ያለ ምንም ማቅማማት በደስታ ተቀበሉት። ዛሬ የወያኔ ትስያንና ደጃዝማች ዘውዱ ገብረ ሥላሴ እንደሚሉት ሳይሆን ክለኛ ታሪክ እንደሚለው ማለት ነው። አቶ ጳውሎስ ኞኞ ኞውንም ታሪክ በታሪክ አበጥረው የጻፉት በመሆናቸው ለዛሬው ትልድ ሆን ለወደፊቱ ትውልድ ትክክለኛውን ታሪክ መዝግበን ትቀመጥ ያኖርብናል። ታሪክ ምንጊዜም ታሪክ ነው።

ኔ ቴዎድሮስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 271 281 "ናፒር ያው ላይ መጀመሪያ ከሚያገኛቸው ከደጃች ካሣ ጋር በቀል ጋር መቀሟ መሆኑን አውቀ። በዚህም ምክንያት ይህን ነታቸውን የሚያበረክቱ የሚገናኙበትንም ቦታ የሚያስወስኑ ክተኞች በስንኤሊ ወደ ደጃች ካሣ ተላኩ።"

"በኮሎኔልነት ሲያገለግል የኖረው አሁን ብርጋዴየር ጄኔራል ሆኖ የተሾመው ሜርዌዘር የመልክተኞቹ መሪ ሲሆን በውስጡም ጀምስ ግራንት እና የኢትዮጵያን መኳንንት እስከ አጤ ዮሐንስ ዘመን ሲያበጣብጥ የኖረው ሙዚንጀርም አብሮ ነበር። በጠቅላላው 13 መልክተኞች ያሉበት ቡድን ጥር 18 ቀን ከሜጀር ጄኔራል ናፒዬር ተልኮ ወደ ደጃች ካሣ ሄዱ። ጥር 23 ቀንም ከደጃዝ ካሣ ዋና ከተማ አድዋ ገቡ።"

"መልክተኞቹ አድዋ እንደደረሱም በመርጫ ወርቄ ወንድም በገብሩ ወርቄ ባልደረባነት በገቡ በማግሥቱ ከደጃች ካሣ ጋር ተገናኙ። ገብሩ ወርቄ ከሕንድ አገር ቦምቤይ የተማረ በመሆኑ እንግሊዘኛ በሚገባ ይችላል። ለባልደረባነት የተመረጠውም በዚሁ ምክንያት ነበር። ደጃች ካሣ የፍሬውን ገኘ ጉግሣን አማካሪያቸውን የፀራገብረ ሚካኤልን፤የሰላዋውን ገኘ ኃይለ ማርያምን፤የገራልታውን ሐጎስን፤ የአክሱምን ንቡረዕድ ገብረ ውበትን፤ሹም ተምቤን አኑንን ሹም አጋሜ ጥርሶን፤የሰባጋዲስን ልጅና ሌሎችንም መኳንንት ይዘው ተቀበሉአቸው።"

"መልክእተኞቹም የመጡበትን ጉዳይ ሳይሆን የወዳጅ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ታላቅ ግብር ተደረገ። በማግሥቱ የመጡበትን ጉዳይ ንግግር ተጀምሮ ከናፒዬር የተጻፈውን ደብዳቤ መልክእተኞቹ ለደጃች ካሣ ሰጡ። ደብዳቤው ተነቦና ተተርጉሞ እንዳበቃም ደጃች ካሣ ሲናገሩ ፥አባቶቼ ከእንግሊዝ ጋር ወዳጅነት እንደነበራቸው ሁሉ እኔም ወዳጅ በመሆን ከብትና እህል በማቅረብ እረዳለሁ፥ አሉ።"

"በዚህና ከናፒር ስለሚገናኙበትም ቦታና ጊዜ ተስማምተውና ወስነው የናፒዬር መልእክተኞች ጥር 27 ቀን ከአድዋ ተነሥተው ጉዞአቸውን ጀመሩ። ከመልእክተኞቹም ጋር ሊቀ መኳስ የአድዋ አዋሳኝ የጎንደብታ ገኘ ናቸው። እናታቸው የሰባጋዲስ ልጅ ሲሆኑ አባታቸው ሊቀመኳስ ደስታ ይባላሉ።"

"ደስታ ደግሞ የጎንደብታው የፌታውራሪ ገብረ አምላክ ልጅ ናቸው። ከመልእክተኞቹ ጋር ሊቀ መኳስ ይልማ ዋና ሆነው አብረው እንዲሄዱ ይላኩ እንጂ ቀሳውስት አርባ ያህል ጦር የያዙና ሃያ ጠበንጃ የያዙ ተከታዮች አብረው ነበሩ። እነኝህ መልእክተኞች



ከናፔዬር ሠፈር መድረሳቸው እንደተሰማ ናፒዬር ከፍተኛ አቀባበል እንዲደረግላቸው አዘዙ።"

"ከዚያም የመልክተኞቹ የሁለቱም ወገን ቡድን ከናፐዪር ጋራ ተገናኝተው በሰፊው ከተነጋገሩ በኋላ በማግሥቱ ኢትዮጵያውያኖቹ መልእክተኞች አንድ ወጥ ልብስ (ዩኒፎርም) በለበሱ ወታደሮች አጃቢነት ተሸኝተው ወደ አድዋ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ሁለቱም ወገኖች የተስማሙት የትግራዩ ገኘ ደጃች ካሣና የእንግሊዙ አዛዥ ሌተና ጄኔራል ናፒዬር ሐራማት ውስጥ ማያ አደብ ከተባለው ቦታ እንዲገናኙ ተወስኖ ነበር።"

"በቀኑ ቀጠሮው ናፒር በ450 ወታደሮች ታጅቦ የካቲት 18 ቀን ማይ አደብ ሲደርስ ደጃች ካሣ አራት ሺህ ከሚሆኑ ጠበንጃና ጦር ከያዙ ወታደሮቻቸው ጋር በዚያው ሠፍረው ነበር። ቀይ ቀለም ያለው የካሣ ድንኳን ተተክሏል። ከካሣ ሠፈር ማዶ ከትይዩ ቦታ የናፒዬር ሠፈር ሆኖ ድንኳን ተተከለ። የድንኳኑ ተከላ ሥራ አልቆ ጥቂት ከቆየ በኋላ ካሣ በወታደሮቻቸው ታጅበው ናፒዬርን ለመገናኘት ወደ ናፒዬር ሠፈር ሄዱ።"

"ካሣ በአስፈሪ ግርማ ታጅበዋል። የተቀመጡበት በቅሎ ግራጫ (ነጭ) ነች። ካሣ በራሳቸው ላይ ያሠሩት ታላቅ ጎፈር ግርማ ሞገስ ሰጥቷቸዋል። ታላቅ ግንጥላ በረጅም ሰው ተይዞላቸው ከበፊታቸው ነጋሪቱ እየተጎሰመ እምቢልታ እየተነፋ የኢትዮጵያን ባንዲራ ቀይ ቢጫ አረንጓዴ የሆነውን (ያኔ እንዲህ ነበር) አስቀድመው በ400 ወታደሮች ታጅበው ሔዱ።"

"የካሣ መምጣት እንደታወቀ ለአቀባበሉ የክብር ዘብ ተሰልፎ ራሱ ናፒዬር ባጌጠ ዝሆን ላይ ተቀምጠና ቀያይ ልብስ በለበሱ ዝሆን ተቀማጮች ታጅቦ ታላቅ አቀባበል አደረገላቸው። ከዚያም ከአቀባበሉ ሥርዓት በኋላ ለመገናኘት ከተዘጋጀው ድንኳን ይዞአቸው ገባ። ጥቂት ዕረፍት እንዳደረጉ የወይን ጠጅ ቀረበ።"

"ወይን ጠጅ ለደጃች ካሣ ሲሰጥ በውስጡ መርዝ ወይም መጥፎ ነገር ያለመኖሩን ለመግለጽ ናፒዬር ራሱ የካሣን ብርጭቆ ተቀብሎ ቀመሰ። በንግግሩም ወቅት እንግሊዞች ስለሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ቀደም ብለው የሚያውቁት ሙዚንጀር እንደሚያዘጋጅላቸው ካሣ

ተናግረው በእርሳቸው በኩል ደግሞ ያለውን ችግር የዋግሹም ጎበዜና በአጋሜ የራስ ባርያው መሸፈት መሆኑን አስረዱ።"

"ናፒዬርም ሲመልስ በአገራችሁ የውስጥ ጉዳይ አንገባም። መሣሪያ ግን እንረዳዎታለን ብሎ በዚህ አሳብ ሁለቱም ወገኖች ተስማምተው ካሣ ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ። ናፒዬር በአገራችሁ የውስጥ ጉዳይ አንገባም ማለቱ የጨዋነት መልስ ቢሆንም ዋናው ቁም ነገር ግን ናፒዬር ከትግራይ ከደጃች ካሣ ግዛት ሲወጣ የሚያጋጥመው ወይም የሚገባበት የዋግሹም ጎበዜ ግዛትና ዋግሹም ጎበዜ በመሆናቸው ነው።"

"ደጃች ካሣ ከናፒዬር ከመለየታቸው በፊት ናፒዬር ወደ ሠፈራቸው እንዲመጣ ጋብዘውት ስለነበረ በዚያው ዕለት ከሰዓት በኋላ ናፒዬር ወደደጃች ካሣ ሠፈር ሄደ። ከካሣ ሠፈር ሲደርስም የካሣ ወታደሮች ተሰልፈው እርምታ በመተኮስ ተቀበሉት።"

"ናፒዬርም ምርጥ የሆኑትን የካሣን ወታደሮች በማየቱ መደሰቱን ለደጃች ካሣ ገለጠላቸው። ከዚያም ከካሣ ጋር ተያይዘው ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀው ድንኳን ገቡ። ከድንኳኑ እንደገቡም የትግራይ ቆነጃጅት ሴቶች እያሳለፉ በትላልቅ ውብ ዋንጫ ጠጅ እየተቀዳ ተሰጣቸው። ግብር ቀርቦ ምግብ ከተበላ በኋላ እምቢልታ ነፊዎችና መሰንቆ መቺዎች ገብተው ጨዋታ ተጀመረ።"

"ካሣም ለጀኔራል ናፒዬር በራሱ ላይ አንበሳ ጎፈር አሠሩለት። በወገቡም ላይ ሰገባው ያጌጠና የሚያምር ጎራዴ አስታጠቁት። በእጁም ጦርና ጋሻ በማስያዝ ሸለሙት። ከዚያ በኋላ ናፒዬር ለመሔድ በሚነሳበት ጊዜ ከድንኳኑ በራፍ ሲደርስ በወርቅ መረሻት ያጌጠች ግራጫ በቅሎ ለመጓጓዣው የተሰጠችው መሆኑ ተነገረው።"

"መልካም አቀባበል እንደተደረገለት ሁሉ አሸኛኘት ተደረገለት። ናፒዬር ጎፈሩን አስሮ ጎራዴውን ታጥቆ በተሸለማት ግራጫ በቅሎ ተቀምጦ ከሠፈሩ ሲገባ እንኳን ወታደሮቹ ጓደኞቹ የሆኑት የእንግሊዝ መኮንኖች እንኳ ናፒዬር መሆኑን አላወቁም ነበር።"

"ከዚህ በኋላ የእንግሊዝ ጦር የመቅደላ ጉዞውን ቀጠለ። የእንግሊዝ ጦር በሚጓዝበት ጊዜ በየደረሰበት ሁሉ ሕዝቡ እየወጣ በማድነቅ



ይመለከተው ነበር። ጉዞው ላይ ፈረሰኞች ይቀድማሉ። ፈረሰኞችም አረንጓዴ ቁምጣ ታጥቀዋል። ቀይ ኮት ደርበዋል። አረንጓዴ ጥምጥም ጠምጥመዋል። ሕንዳዊ ያልሆኑት ወታደሮች ደግሞ ሱሪያቸው ተመሳሳይ ሲሆን ነጭ ኮፍያ (መለዮ)አድርገው ይጓዛሉ።"

"ይህ ሁሉ ታይቶ ያልታወቀ የአለባበስና የሰልፍ ሂደት ሕዝቡ እያየ ቢያደንቅም የበለጠ ግን የሚደነቀው ታላላቆቹን መድፎች የተጫኑት ዝሆኖች በየራሳቸው ላይ ሰው ተቀምጦባቸው ሲጓዙ ማየቱ ነበር። በጉዞው ላይ ናፒዬር በየደረሰበት ሠፈርና መንደር ሁሉ ከሠፈሩ ሹም ጋር ሰላማዊ ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ከብሪትሽ ሙዚየም ለቅርሳዊ ዕቃዎች ፍለጋ ከጦሩ ጋር የመጣው ሪቻርድ ሆልምስ ደግሞ በየቤተ ክርስቲያኑ እየገባ ለሙዚየም የሚሆኑ ዕቃዎችን ይፈልግ ነበር።"

"ከደጃዝማች ካሣ ግዛት ጨርሰው ከመውጣታቸው በፊት ቀጥሎ ካለው አገር ከላስታ ገዥ ከዋግሹም ጎበዜ ጋር በሰላም ለማለፍ መነጋገር ያስፈልግ ነበር። ይህንኑ ጉዳይ እንዲነጋገር ሙዚንጀር ተልኮ ቀድሞ ሄደ። በዚያን ጊዜ ለዋግሹም ጎበዜ ጦር ዋና አዛዥ የነበሩት ደጃች መሸሻ ስለነበሩ በተከዜ ሸለቆ ዛጎል ዛፍ ከሚባል ሥፍራ ከሙዚንጀር ጋር ተገናኙ።"

"ከናፒዬር በተላከው መልዕክት መሠረት ደጃች መሸሻ ተስማምተው የእንግሊዝን ጦር እየመሩና እየጠበቁ ያለምንም ችግርና ኮሽታ ደላንታ ደረሱ። የእንግሊዝ ጦር ደላንታ ላይ የስንዴ በተባለ ቦታ ሠፈር አድርጎ ሳለ ናፒዬር ራሱ ለአጤ ቴዎድሮስ የመጀመሪያውን ደብዳቤ ጻፈ።"

"ደብዳቤውም በእንግሊዝ ንግሥት ትእዛዝ ከጦር ሠራዊቴ ጋር መቅደላ አጠገብ ደርሻለሁ። የታዘዝኩትም በእርሶ እጅ የሚገኙትን መልእተኞች ራሳምን ቆንስል ካሜሮንን ሐኪም ብላንክንና መቶ አለቃ ፕሪዲዎክስን እና ሌሎቹንም አሁን በግርማዊነትዎ ኃይል ሥር ያሉትን ኤሮፓውያኖቹን ለማስለቀቅ ነው ግርማዊነትዎን የምጠይቀው እነዚህን ሰዎች በተቻለ ፍጥነትና ሰላማዊ ሠፈር ድረስ እንዲልኩልኝ ነው" ብሎ ጻፈላቸው ሲሉ ጽፈዋል።

# ክፍል ዘጠኝ

## ምዕራፍ 1

### የአጤ ቴዎድሮስ ጉዞ ወደ መቅደላ

አጤ ቴዎድሮስ ጋፋት ያሠሩት መድፍ ተጎትቶ እንዲሄድ ትእዛዝ ሰጥተው ከሚያከብሩትና ከአሠሩት ቤተ ክርስቲያን ደብረታቦር መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ አስቀድሰው ሥጋ ወደሙ ተቀብለው ካህናቱንና ታላላቆችን በሥርዓት ተሰነባብተው ጉዞ ወደ መቅደላ አደረጉ።

አጤ ቴዎድሮስ ሲሰናበቱ "ሁለተኛ በዚህ ዓለም አንገናኝም። የምንገናኘው ከመድኃኔዓለም ጋር ይሆናል። ለእኔ ሕይወት ሳይሆን ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጸልዩ" ብለው ተሰናበቱ ይህ አባባላቸው አጤ ቴዎድሮስ ከመቅደላ ወደ ደብረታቦር እንደማይመለሱ ቆርጠው የሄዱ መሆናቸውን ያስረዳል።

አጤ ቴዎድሮስ ከደብረታቦር መንገዳቸውን ወደ መቅደላ ሲያቀኑ መድፉ እየተጎተተ በሚሄድበት ወቅት ተራራማና አስቸጋሪ ቦታ ሲደርሱ እርሳቸው እንደ ተራ ሠራተኛ ቁፋሮ ይቆፍሩ እንደነበርና አንዳንዴም ቀድመው የመሬቱን አቀማመጥ በጥንቃቄ ያጠኑ ነበር።

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው</u> አንበሳ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 204 "አጤ ቴዎድሮስ በ1860 ዓም በመስከረም ወር የመስቀልን በዓል በደብረ ታቦር ከተማቸው ካከበሩ በኋላ ጥቅምት 1 ቀን የመቅደላ ጉዟቸውን ጀመሩ። መድፎች በመንኮራኩር የሚሽከረከሩበት መንገድ እየተ ደለደለ አቀበቱ ቁልቁለቱ እየተስተካከለ ትልልቁ ደንጊያ በባሩድ እየተሰበረና በድጅኖ እየተፈነቀለ የኈጣንና የበሸሎን ቁልቁለት በማስተካከል ሰፋ ያለ መንገድ እያስጠረጉ ከብዙ ድካም በኋላ ከነንዛቸውና ከመድፎቻቸው ጋር በሚያዝያ ወር መቅደላ ገቡ" ሲሉ ጽፈዋል።



መድፉ የሄደበት መንገድ ራሳቸው እየለኩ ያስቆፈሩት ሲሆን ዛሬ ድረስ አውራ ጎዳና ሁኖ የሚያገለግል ነው። አጤ ቴዎድሮስ ዘመናዊ አውራ ጎዳና ቀደም ከደብረታቦር ጋፋት ከዚያም ወደ ሌላ አካባቢ የሠሩ ናቸው። ዛሬ ምናልባት አንዳንድ ወገኖች ታሪክን ያላገናዘቡ ይህን ከዚህ በላይ የተባለውን አይቀበሉ ይሆናል። ለዚህም ነው "ታሪክ ይታመማል እንጅ አይሞትም" የሚባለው።

ብዙ አዳዲስ የፈጠራ ታሪክ እየወጣም ነው። ስለ አጤ ቴዎድሮስ የምጽፈው ግን ለያንዳንዱ ምዕራፍ ዋቢ እየጠቀስኩ በመሆኑ በታሪክ ዘንድ እወቀሳለሁ ብዬ አልጠራጠርም። ከላይ ከመግቢያው እንደጠቀስኩት ዋቢ ሠነድ የማልጠቅስ ከሆነ ምዕራፉን አልጀምረውምና ነው።

<u>ቴክኖሎጂና የዘመኑ ትራንስፖርት</u> በተባለው መጽሔት መስከረም 1990 ዓም ገጽ 41" ለየብስ ትራንስፖርት የመጀመሪያው ዘመናዊ መንገድ ደግሞ በአጤ ቴዎድሮስ የተሠራው ከደብረታቦር ጋፋት፤ ከዚያም ሚሲዮናውያኑ የሠሯቸው ጋሪዎች ከጋፋት ደብረ ታቦር፤ ቀጥሎም ወደ አሞራ ገደል እስቴና ስማዳ ድረስ ያሉት መንገዶች ቀዳሚነት አላቸው።"

"እነዚህ መንገዶች በሚሠሩበት ወቅት አጤ ቴዎድሮስ ራሳቸው እንደተራ ሠራተኛ ተሠልፈው ይሠሩ እንደነበር ዲፍተን የተባለው ደራሲ የመዘገበው ስለሆነ በሀገራችን የመጀመሪያው ዘመናዊ መንገድ ሊሆን በቅቷል" ሲል ጽፏል።

ይህን መንገድ በሰላሙ ጊዜ ያሠሩት ሲሆን ጋፋት የተሠራው መድፍ እየተጎተተ የሄደው በዚሁ መንገድ ሲሆን ከላይ ሲደርስ ግን ደግሞ አዲስ መንገድ መሠራት ስለነበረበት ራሳቸው እየለኩና እያዘዙ መንገዱን በመሥራትና በማሠራት ጉዞአቸውን ወደ መቅደላ አደረጉ።

<u>የደብረታቦር ዳግማዊ ቴዎድሮስ ት/ቤት 50ኛው</u> ዓመት በዓል በተባለው መጽሔት ገጽ 11 "አጤ ቴዎድሮስ በ1850ዎቹ ዓመታት ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ አስደናቂ የሆኑ የአውራ ጎዳና አውታሮች ለመዘርጋት ሙከራ ያደረጉበት ሥፍራ ነው። አጤ

ቴዎድሮስ የጋፋት ሠራተኞችን ወታደሮቻቸውንና የአካባቢውን ሕዝብ በማስተባበር ደብረታቦርን ከጎንደር፣ ከጎጃምና ከመቅደላ ጋር የሚያገናኙ መንገዶችን አሠርተዋል::"

"በኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹ ዘመናዊ የመንገድ አውታሮች የተዘረጉት የደብረታቦር ከተማ ላይ ቢሆንም ወረታን ከወልደያ ጋር የሚያገናኘው አውራ መንገድ እስከተሠራበት ጊዜ ድረስ በመገናኛ እጦት ምክንያት የአካባቢው ሕዝብ ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ለመጓጓዝ ምን ያህል ሲሰቃይ እንደቆየ የሩቅ ጊዜ ትዝታ አይደለም" ሲሉ ጽፈዋል::

<u>የእሥራት ዘመን በአበሻ አገር</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 244 "ከዚህ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ አስቸጋሪ ቀጥተኛ መሳበሪያ ወደ ሆነው ቦታ ወርደው ሠራተኞቹን መምራት ያዙ:: እኛም ከመንገዱ በአንደኛው በኩል ሆነን ሁኔታውን እንድንመለከት ሰደዱን:: ሌሎችንም መኳንንቶቻቸውን ሥራ ሰጧቸው:: ያን የመሰለ ከባድ መድፍ እንደዚያ ካለ ተራራና ገደል ሥፍራ ጎትቶ ለማውጣት ከቴዎድሮስ አመራር በስተቀር ሌላ ሰው ሊያደርገው እንደማይችል በፍጹም አምናለሁ" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህን ተራራና አስቸጋሪ መንገድ እኔ እንደ አቶ ጳውሎስ ኞኞ ሳልጎበኝ ነው ይህን መጽሐፍ የጻፍኩት:: አቶ ጳውሎስ ኞኞ ግን ከደብረታቦር ተነሥተው መቅደላ ድረስ መድፉ የሄደበትን መንገድ አይተው ነበር አጤ ቴዎድሮስ የሚለውን መጽሐፋቸውን የጻፉት::

<u>መጽሐፈ ቡዳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 63
"እንግሊዞች መጡ ሀገርክን ሊወጉ
ኢትዮጵያ ሀገራችንን ቅኝ ግዛት ሊያደርጉ
ከኛ የሚበልጠው የጦር መሣሪያቸው
መድፍ መትረየሱን በዝሆን ላይ ጭነው
አዲስ ጦር መሣሪያ ታጥቋል ወታደሩ
የጦር ልምድ ያለው በዓለም በሀገሩ" ሲሉ ጽፈዋል::



# ምዕራፍ 2

## የእንግሊዝ እና የኢትዮጵያ ጦርነት በመቅደላ

<u>የእሥራት ዘመን በአበሻ አገር</u> በተሰኘው መጽሐፍ 265 "ጃንሆይ እኛን አሰናብተው ከስደዱ በኋላ ከድንጋይ ላይ ተቀምጠው በሁለቱም እጆቻቸው ራሳቸውን ደግፈው አቀርቅረው ማዘን ስለጀመሩ ራስ እንግዳ ለምን ያዝናሉ እነዚህን ነጮች መልሰን እናምጣና ገድለናቸው ተዋግተን እንሙት ስላሉዋቸው አጤ ቴዎድሮስ በቁጣ አንተ አህያ ባለፈው ሁለት ቀን ውስጥ የፈጀሁት ሰው አይበቃምን? እነዚህን ነጮች እንግደልና አበሻን በደም እንዳጥባት ነውን የምትፈልገው? ብለው እንደሰደቧቸው ሰማን" ሲሉ ጽፈዋል::

አድማሱ ዓለማየሁ ጌታሁን <u>የአራቱ የኩሽ ዘር ግንዶችና የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 152 "የሚወዷቸውን መኳንንቶች እየሳሙ ከኔ ጋር ለመሞት ፍላጎት ያላችሁ ከዚህ ቆዩ የሌላችሁ ግን በደጀን በደጀን ሁናችሁ ወደየፈለጋችሁበት አገር ሂዱ ብለው አሰናበቱአቸው:: በዚህን ጊዜ ሊቀ ሊቃውንት ፍጹም ፍስሐና መላከ ብርሃናት እንግዳ ቀርበው ለምን ወታደሩን ያሰናብቱታል ብለው ቢጠይቋቸው እኔ ሕዝቤን የቀጣሁትና የገደልኩት ከሞት የቀረው አንድ ሆኖ ይተባበርና ትልቅ አገር ለመሆን ይደርሳል ብዬ እንጂ አሁን ራሱ መለያየት ፈልጎ የውጭ ነጭ ሰው ከተከተለ ለምን እነዚህስ ይሞታሉ አሏቸው::"

"ከዚያም ደግሞ ነጋድራስ አፈወርቅ የሚባሉ የአጤው ባለሟል ጃንሆይ እንግዲህ የዚህ የጦር ምክንያት የሆኑትን ነጮች እሥረኞች እንግደላቸውና ሄደን እንሙት አሏቸው:: አጤ ቴዎድሮስ ግን ያገሬን ሕዝብ አንድ ለማድረግ እኔ ያሰቃየሁት አልበቃ ብሎ ደግሞ እነዚህን እንግሊዞች የውጭ አገር ሰዎች ገድዬ ሕዝቤን እንደገና በውጭ ሰዎች እንዲጠቃ አላደርግም ማሰሬ እንኳ ሌላው እንዲፈራ ብዬ ነው ያሠርኳቸው ይኸው በቃቸው ብለው ተናገሩ" ሲሉ ጽፈዋል::

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 401 "እስረኞቹ ከሚቀመጡበት ከላይ ከመቅደላ አፋፍ ከእስር ቤት እየተንጋጉ አጤ ቴዎድሮስ ወዳሉበት ወደ ፍላ (ፉህላ)ሲመጡ ግራና ቀኝ የሚመለከታቸው ወታደር ግማሹ ይኸን ሁሉ ችግር ያመጡብንን ፈረንጆች መፍጀት ነበር ሲል ሌላውም በመሰለው ተናገረ" ሲሉ ጽፈዋል::

ነጋድራስ አፈወርቅ ሆኑ ራስ እንግዳ አልያም የአጤ ቴዎድሮስ ወታደሮች ሁኔታው ሲያበሳጫቸው ይህን ቃል መናገራቸው እውነት ሲሆን አጤ ቴዎድሮስ ግን አርቀው በማሰብ ምክሩን አልተቀበሉም:: አጤ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚመጣውን ችግር ጠንቅቀው የሚያውቁ ስለነበሩ የአውሮፓ እስረኞች እንዲገደሉ የሚለውን ምክር አልደገፉትም:: ከዚህ ላይ የምናጤነው ነገር ቢኖር አጤ ቴዎድሮስ ሕዝብ መግደላቸውን አልካዱም ነገር ግን ቃሉ የሚለው "የአገሬን ሕዝብ አንድ ለማድረግ እኔ ያሰቃየሁት የማይበቃ" የሚለው ቃሉ በግል ቂም በቀል ብለው ሳይሆን ለአገራቸው እድገት ሲሉ ያወጡትን ሕግ የጣሱትን መግደላቸውን አልካዱም::

ዋናው መሠረቱ በዚህ ወቅት እንኳ ለሕዝባቸውና ለአገራቸው ማሰባቸው ጠንካራ መሪ መሆናቸውን ያሳያል:: ኃላፊነታቸውን አክብረዋል:: ኋላም ፈትተዋቸዋል:: በዚያን ወቅት አጤ ቴዎድሮስ እነዚህን መዘዘኛ አውሮፓውያን ገድለዋቸው ቢሆን ኑሮ የመጣው የናፒር ጦር በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሊያደርሰው የሚችለው ጥፋት ተቆጥሮ አያልቅም ነበር:: ምናልባት ይህ ጦር ደጃዝማች ካሳ ምርጫን ቢሆን አያዝንላቸውም ነበር::

አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ እንደደረሱ ጀኔራል ናፒርም መምጣቱን ደብዳቤ ጻፈላቸው:: እርሳቸውም በልበ ሙሉነት ወታደራቸውን ማደራጀት ጀመሩ:: በዚህ ወቅት መቅደላ ታስረው የነበሩ እንግሊዞች ክፉኛ ፈሩ:: መሞታቸው ወቅቱ አሁን መሆኑን ተገንዝበው ይጨነቁ ጀመር::

<u>አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 285 "ዎልድሜር ከልጁና ከሚስቱ ጋር ተላቅሶና ተሳልሞ ከቴዎድሮስ ዘንድ ሲመለስ ንጉሡ



ከተሰበሰበው ሠራዊታቸው ፊት ለፊት ከፈረስ ላይ ተቀምጠው አያቸው:: የተሰበሰበው ሰባት ሺህ ያህል ሰው ይሆናል:: ቴዎድሮስም ንግግ ያደርጉ ጀመር:: ልጆቼ እኒህ የመጡትን ወታደሮች አትፍሩአቸው:: እነሱ ዳዊትን እንደተጋጠመው እንደ ፍልስጥኤማውያን ናቸው::"

"ዳዊት ግን በእግዚአብሔር ኃይል አሸንፈዋለሁ ብሎ ገጠመ:: እኔ የዳዊት የሰሎሞን ልጅ አይደለሁምን:: እግዚአብሔር እኔን የኢትዮጵያ ንጉሥ አድርጎ አልቀባኝምን:: በጦርነትስ ላይ የማልነካ ሁሉን የማስፈራ የእሳት ምሰሶ እየሆንኩ ያረጀሁበት ጀግና አይደለሁምን::"

"እግዚአብሔር በድል ላይ ድል እየጨመረ አልሰጠኝምን:: ዛሬ የእግሊዝን ጦር አበሻ ምድር ድረስ እንዳስመጣሁት ድል ሳደርገው ደግሞ ታያላችሁ:: እንደሕጋችን ወደ ጦርነት የሚሔደውን ሰው እግዚአብሔር ይፍታ እንዳይሉ አቡነ ሰላማ ሞተዋል:: በእርሳቸው ቦታ ሆኜ እኔ እፈታችኋለሁ:: በእግዚአብሔር በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ማንኛውም ወታደር የኤሮፓን ጦር ተቃውሞ የሚዋጋውን ሁሉ በጦር ሜዳ ሕይወቱን ቢያጣ እግዚአብሔር ይፍታው ብለው ንግግራቸውን ሲጨርሱ ወታደሩ እየሸለለና እየፎከረ የእንግሊዝ ጦር ወደ መሸገበት ወደ እሮጌ ወረደ" ሲሉ ጽፈዋል::

<u>ቁስለኛዋ አገር</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 175 "ቴዎድሮስ ለሠራዊቱ ያደረገው ንግግር" ብለው ትምህርተ ጥቅስ ከፍተው ሰፋ አድርገው ዘግበውታል:: ከእርሳቸው በይበልጥ ደግሞ በጣም አስፋፍተው የጻፉት መሪ ራስ ኤ ኤም በላይ ናቸው:: ለማንኛውም ይህን የእርሳቸውን ንግግር ከመጽሐፉ ያገኘሁትን ሙሉ በሙሉ ገልብጬ ለአዲሱ ትውልድ እንዲያውቀው አድርጌያለሁ::

መሪ ራስ.ኤ.ኤም.በላይ <u>የትናትናዋ ኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 299 "በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፡በስም ሦስትነት በባሕርይ አንድነት ሦስትነትን ከአንድነት የማይለየው እግዚአብሔር መርጦ ያነገሠው ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ በዛሬው እለት በአሁኑ ሰዓት በጎኔ የተሰለፋችሁ ጀግኖች አንድነትን የምትወዱና የምትከተሉ ተከታይ ትውልዶች ልንግራችሁና ላስተምራችሁ የምፈቅደው ከዚህ ቀጥሎ

ያለው ቃል ነው:: አባቶቻችን ነገሥታቱ ፈጣሪያቸውን ቢበድሉት ሀገራቸውን ለቱርክ እስላም ሰጠባቸው::"

"መንግሥታቸውንም ለእንደራሴዎቻቸው አሳልፎ ቢሰጥ እንደ ራሴዎቻቸው እርስ በእርሳቸው በተቀያየሙ ጊዜ የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በእርሱ አጋደሉት: አለያዩት ሁሉም በየቤቱ ተነሥቶ ለራሱ ንጉሥ ሁኖ ወገኖቹን ፈጀ!ገደለ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር እኔን ከታናሽነቴ ጀምሮ መርጦ ለሕዝብ ተቆርቋሪና መከታ ሆኜ እንድነሣ አደረገኝ::"

"ለዚህም የራሴን ወገኖች ቀጣሁ.ገደልኩ ለተከታዬ ትውልድ መልካም ሥራና ኃይል ያለው አንድነት እንዲኖረው ስል ሌትኖ ቀን ሳላርፍ ፈጽሞ ደከመኝ ሳልል እሮጥኩኝ.ታገልኩ የውስጡን አረመኔ ሳጠፋ ከባሕር ማዶ ሀገራችንን የሚወርና ሕዝቡን ባሪያ አድርጎ የሚወስድ የቱርክን መንግሥት ሳጠፋ ካህናቱና ጳጳሳቱ ጠላት ሆነው ተነሡብኝ:: እነርሱንም አሰርኩ ነገር ግን አሁን ያመንኩት ሕዝቤ ጠላት ሆኖ ስለተነሣብኝ የሚያሳድሙብኝን የውጭ ሀገር ሰዎች አብሬ አሰርኩ ይሄውም ክርስቲያኑን መንግሥት ወንድማቸውን እኔን ትተው የእስላምን መንግሥት ቱርክን ወደው ለእሱ ስለሚላላኩና ስለሚያግዙ አይቼ ነው ከሀገሬም እንዲወጡ ብል አንወጣም አሉ:: ስለዚህ አሰርኳቸው:: እንጂ አልገደልኳቸውም::"

"አሁን በእነሱ አመካኝቶ የእንግሊዝ መንግሥት ጦር ሠራዊት አንድነታችንን ለማፍረስ ኃይላችንን ለማድከም በቱርክ መንግሥት እየተረዳ ወደ ኢትዮጵያ ምድር ባሕር ተሻግሮ ገባ:: ከዚያ በፊት ሲላላኩ ኑ ድረሱልን ሲሉ የነበሩት መሳፍንት ከሞት ከተረፉት ቀሪዎች ጋር ተገናኝተው እጅና በትር ሆነው መጡብን:: አሁን በአጠገቤ ያላችሁ ሕዝቦቼ የኢትዮጵያ ሠራዊት ለአንድነት የቆማችሁ ሆይ! ያለፈውን መሳፍንት አመራር በማጥፋትና የቀና አስተዳደር በቦታው በመተካት የተለያዩት ወገኖቻችን በማገናኘት የትኛው ጠፍቶ የትኛው መልካም ሥራና ዘመናዊ ጥበብ እንዲስፋፋ ለማድረግ ለአደረኩት ድካሜ የኢትዮጵያ ምድር በስሜ ላይ ትመስክር::"

"መቼም እድሚያቸውን ሙሉ በወገኖቼ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ክፉ ሲያደርጉ የሚኖሩ መሳፍንትና የነገሥታት ቅምጥል ዘሮች ደግ ሥራ



መሥራት ስለማይችሉና መልካም ትምህርትና ጥበብ ማስተማር ቀርቶ በቅን ልቦና የሚሠሩትንና የሚጠበቡትን ተከታይ ትውልድ እንዳይወዳቸው ለማድረግ ስለሚያጠፏቸው እናንተ የኢትዮጵያ ጀግኖች ለቆማችሁለትና ለደከማችሁለት አንድነት ታማኝ ሆናችሁ እነሱን ለማዳን መገኘት የአንድነቱ ጥሪ ነው:: ነገር ግን አንድነታችሁንና ኃይላችሁን ሊያጠፉ ከተሰለፉባችሁ ጠላቶች ፊት መሸሽ ወይም በምን ግዴለሽነት ማለፍ ወገንን አታሎ ሕሊናን ገድሎ ሳይሞቱ ሙቶ በውርደት መቃብር ታፍኖ መኖር ነው::"

"በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ ሀገሩ ላይ የመልካም ሥራና ደግ ሥራው አንድነቱን ነጻነቱንና ዓላማውን ተግባሩን እንዳይፈጽም መንገድ መሪ መሆን ነው:: የድል ባለቤት ኃይላችሁንና አመራራችን የሚለው የሕዝብ ጠላት የሆነው ካለፈው ክፉ ሥራና ከስህተቱ ተገንዝቦ ለመልካም ተግባርና አንድነት ቢመለስ መቀጠል፤ አልመለስም ካለ ምንጊዜም ከአጥፊ መሸሽ አጥፊ እንዲጠፋ መፍቀድ ስለሆነ አጥፊ ጠላቱን አስቀድሞ ማጥፋቱ የሚፈልግ ነው:: ስለዚህ ከተቻለ አጥፊን ጠላትን አጥፍቶ ለመጭው ትውልድ መልካም መሪ መሣሪያ ጠላትን አጥፍቶ የማምለጥ እድል ካልተገኘ መጥፋት የጀግኖች ሥራ ነው::"

"ማንኛውም ትውልድ በወረደ ልማድና በተበታተነ ሥርዓት ታፍኖ በክፉ ሥርዓት ሺህ ዘመን ተዋርዶ ከመኖር ለከፍተኛ አንድነቱ ለመልካም ሥራው በታማኝነቱ ለሀገሩ ክብር ሲል የሞተ ጀግና ወታደር በክብር ይበልጠዋል:: ለተከታዩ ትውልድ የመልካም ሥራው መሥዋእትነት መታሰቢያ ሆኖ ይኖራል:: ይህ ትውልድ ቢያፍነው ሌላው ትውልድ ይገልጸዋል:: ለዚህ ታዛቢ መስካሪ ሀገርህ የኢትዮጵያ ምድር ነው::"

"እነዚህ አሁን የከበቡህ የመሳፍንት ጭፍራዎችና አጃቢዎች የውጭውን ሀገር የእንግሊዝን የጦር ኃይል ይዘው ቢመጡብህ አትፍራቸው:: ለክብርህ ብትሞት በሕይዎት አለህ! ባትሞት ግን የሞትክና የተዋረድህ ነህ! ስለዚህ አሁን ለቀረበልህ ክብር ተነሣ ታጠቅ ተቀበለው ጠላቶችህ መሳፍንት ደስ ይበላቸው:: የዛሬ ደስታ የነገ ኀዘናቸውና ልቅሶአቸው ነው::"

"በየጊዜው ትውልድ ሁሉ የራሱ መብትና ምርጫ መኖሩን ያለፉት ነገሥታት ቢያውቁ ኖሮ ሕዝባቸውን በከንቱ ባልገደሉት ባላጠፉት ነበር:: ለጊዜው ግዛታቸውና ታሪካቸው የሚኖር መስሏቸው ደክመውበት በከንቱ ጊዜያቸው ጋር አለፉ:: ሌሎቹም ገና አሁን ጠላት ሆነውህ አሉ::"

"ነገር ግን የትናትና ሰዎች ስለሆኑ ያልፋሉ ያልኳቸው ከዛሬው ትውልድ ጋር ከእኛ ጋር ሆነው ሳለ የትናትና ትውልድ ተከታይ ናቸው:: እኛ ግን ከእነሱ ስንለይ የዛሬው ትውልድ ባለቤት ነን:: የነገውና የነገውም ወዲያ ትውልድ ባለቤቶች ነን:: ይሄውም መልካም ሥራና መልካም ሥራውን ስለምንመኝና ለአንድነት ለተባበረ ኃይል ለማቆም ስንደክም ስንታገል ነው እንጂ የነገው ትውልድ ባለቤት ለመሆን መልካም ሥራንና አንድነትን ለይቶ የመምረጥ መብት የነገው ትውልድ ነው::"

"አሁን እናንተ ለሕዝባችሁ አንድነት ምንድነው የምትሠሩለት? በሕዝባችሁ አንድነትስ ለእናንተ ምን ያክል ክብር ነው? ሀገር ታኖረዋለች፤ ታስመሰግነዋለች፤ መኖሪያና ሰፈሩ ሆኖ እውነተኛ ትውልድ ትተላለፋለች፤እናንተም ሆናችሁ እኔ ለምን ደከምን? ለምን እንደምንሞት ማወቅ የራሳችን መብት ነው::

ነገር ግን መብታችን የራሳችን ሲሆን ሞታችን ደግሞ በታሪክ የሚኖር ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፍ ሕያው ነው:: ስለዚህ በሕይወታችን እንደምንኖር ቁጠሩት እንጂ ሳይሞቱ ከሞቱት ጋር ያለን አይምሰላችሁ:: የእኛ ሞት ለተከታዩ ትውልድ ክብር ነው:: ስለዚህ ሞታችን ጣፋጭ ማር እንጂ መራራ እሬት አይምሰላችሁ"ብለው የተናገሩ መሆናቸው ከላይ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 299-303 ድረስ ተጽፏል::

ወታደር ሽልሎና ፎክሮ ወደ ጦር ግንባር ተሰማራ:: ጋፋት የተሰሩት መድፎች ተጠመዱ፤አዋጊው ፊታውራሪ ገብርዬ ጎሹና ራስ እንግዳ ደጃዝማች ገልሞ እና ደጃዝማች ዓለሜ፤ሌሎችም ጀግኖች ወደ ግንባር ተሰማሩ:: አጤ ቴዎድሮስ ቀደም ሲል ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ወዳጅ በነበሩበት ወቅት ተልኮላቸው በነበረው ሩቅ በሚያሳይ መነጽር ሲመለከቱ የእግግሊዝ ጦር የበሽሎን ወንዝ ተሻግሮ ወደ እሮጌ ሲመጣ አስተዋሉ::



ወዲያውም አገር በቀል የጋፋት መድፍ ወደ ጠላት እንዲተኮስ ትእዛዝ ሰጡ:: የተመኩበትና የተማመኑበት መድፍ ግን አንድ ተኩሶ ፈነዳ፤ለዘለዓለሙ ዝም አለ:: በተፋፋመ ውጊያ ገብቶ በጀግንነት ሲዋጋና ሲያዋጋ ፊታውራሪ ገብርዬም ወደቀ::

ሌሎችም ጀግኖች መሞታቸው እንዲሁ በየ10 ደቂቃው ይነገራቸው ጀመር:: ልክ በኢዮብ ላይ እንደደረሰው መርዶ በእርሳቸው ላይ ይዘንብ ጀመር:: በዚህ ሰዓት ከባጠገባቸው መጥቶ አንድ መድፍ ወደቀና ሰው ገደለ እርሳቸው ግን ከተቀመጡበት አልተነሡም ነበር::

አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 218 "አጤ ቴዎድሮስ መድፍ የሚያስተኩሱበትን ተመልክተውና አነጣጥረው ቢተኩሱ አሞራ የሚመስል የእሳት ጅራት ያለው ፍላጻ ተወርውሮ መጥቶ ከባጠገባቸው የተተከለውን ድንኳን ቀዶ አንድ ሰው ገደለና ከመሬት ገባ::

ሁለተኛ ጊዜ የተተኮሰው ደግሞ አንድ ትልቅ የቁልቋል ዛፍ ቆራርጦ ከመሬት ሲገባ ተመለከቱ ይህ ሁሉ ሲሆን ሰው ሁሉ ፈርቶ ጥግ ሲይዝ እርሳቸው ግን ጋሻቸውን እንደያዙ ከተቀመጡበት አልተንቀሳቀሱም ነበር::

ወዲያውም የመድፉን አረር እንዲ ቀርብላቸው አዘው እንደጋለ ስለነበር በዕንጨት ቀርቅረው አቀረቡላቸው:: የአረሩም ቁመት አንድ ክንድ ሲሆን በአራት ገጽ ጎድጓዳ አለው:: ንጉሠ ነገሥቱ የጥይቱን አረር ከተመለከቱ በኋላ እኔ እስካሁን የምዋጋው ከሰው ጋር ይመስለኝ ነበር ለካስ ከእግዚአብሔር ጋር ነው አሉ" ሲሉ ጽፈዋል::

እርሳቸው ዘመነ መሳፍንትን ሲያርበደብዱ በነበረበት ወቅት ራስ አሊ ያሉት "ይህ የካሳ ኃይል ሳይሆን እግዚአብሔር እኛን ሊቀጣ ያመጣብን ነው" ነበር ያሉት አጤ ቴዎድሮስም ኃይላቸው መድከሙን ተገነዘቡ ማለት ይቻላል::

## ምዕራፍ 3

## አይ መቅደላ፤ ልጆቿን የምትበላ!

አለቃ ወልደማርያም ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 59 "ሠራዊትዎ ተጨርሶ የመቅደላው ከበር ታገደ:: ይህን ጊዜ ንጉሡ የሚይዘው እንደጠፋው እንደ ሰከረ ሰው ሁነው ከፈረስ ወጥተው ከበር ተነሡ:: እንዲህ ከሆኑ ጊዜ የሚከተልዎን እየተቆጡ ሲሄዱ ከእንግሊዝ ወገን 2 እየገደሉ ተመለሱ:: ስለ ምን ከዚህ ላይ ሳይሞቱ ቀሩ?ጠበንጃስ ሳይተኩስብዎ ቀረ?ቢሉ የሚሞቱበት ሰዓት ገና ስለ ሆነ" ሲሉ ጽፈዋል:: በዚህ ሂሳብ ከሄድን "2 እየገደሉ" የምትለው ቃል እየተመላለሱ እየገደሉ መመለሳቸውን ለመግለጽ ፈልገው ይሆናል::

አለቃ ተክለ ኢየሱስ የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 133 "አጤ ቴዎድሮስ ከታችኛው በር ተቀምጦ ነበረ:: ግን ሠራዊቱ ሁሉ እየከዳ አልቆ ብቻ መቅደላ በር የገባው ጦር ታግዶ ከበሩ አፍ ተራዛሚ ነፍጥ አንግቶ 2 ህንድ ሽጉጥ ግራ ቀኝ ታጥቆ 2 ጨሬ ይዞ እንደ ዘንዶ ምላስ እየሰበቀ ወጥቶ ከእንግሊዞች ሰፈር ገብቶ 2 ገድሎ ተመለሰ" ሲሉ ጽፈዋል:: በእርግጥ ከእንግሊዞች መጽሐፍ በ1971 ዓም ወይም ደግሞ በ1979 የታተመው ከዚህ ዝቅ ብሎ የምጠቅሰው መጽሐፍ 20 መቁሰላቸውና ቆይተው ሁለቱ መሞታቸውን ገልጿል::

The Abyssinian Difficulty በተባለው መጽሐፍ ገጽ 185 "The number of Abyssinian soldiers buried by Napier's troops that moring was 560,but it was estimated that altogether about 700 of the emperor's soldiers were killed in the battle of Aroji, and about 1500 wounded. The British expedition's casualties were 20 of whom two later died." ይላል" ነጋ ወልደ ሥላሴ ደግሞ በኢትዮጵያውያን በኩል የሞቱትን ሆነ የቆሰሉትን ቁጥር መብዛት አይስማሙበትም::



**Tess Press Hstory of World in Photo graphs in 1850-Presnt Day 2008 page 65 on April 13,1868 Over 700 of Tewodros's men were killed and approximately twice as many wounded in just two hours' British casualties were only 20 wounded, with only two of them subsequently dying from their wounds. A few days later, the hostages were released. Tewodros committed suicide to avoid captuer,**

ነጋ ወልደ ሥላሴ ባለታሪክ ኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 181 "በመቅደላው ጦርነት 20 ኢትዮጵያውያን ወታደሮችና ጀሌዎች ሲሞቱ 120 የሚሆኑ ቆስለዋል:: ከእንግሊዝ ዘማች ጦር በኩል ደግሞ 10 በጠና ሲቆስሉ 5 ቀላል ቁስል ደርሶባቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህ እንኳን ሊሆን አይችልም:: ምክንያቱም በአጤ ቴዎድሮስ በኩል ከተሰለፉት ታዋቂ ጀግኖች እንኳን ብንቆጥር ከ20 በላይ ናቸው:: ይህን ከዚህ ልተወውና ከላይ ከእንግሊዘኛው መጽሐፍ የአንዱን ቀን ጥዋት ብቻ የጠቀሰ በመሆኑ ትክክል ይመስለኛል::

በእንግሊዝ በኩል የሞቱ ወታደሮች ዝርዝር አልተገለጠም:: በኢትዮጵያውያን ደራስያን በኩል ሰፋ ብሎ አልተጻፈም:: ያም ሆነ ይህ የአጤ ቴዎድሮስን አሟሟት አስመልክቶ ደግሞ በወቅቱ አብሮ የነበረ ጋዜጠኛ እንዲህ ሲል ጽፏል:: አጤ ቴዎድሮስ ቅዳሜ ሌሊት ለእሁድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ገብተው አስቀደሱ፤ሥጋ ወደሙ ተቀበሉ::

እሑድ ካህናቱንና ከሞት የተረፈውን ወታደር ግብር አበሉ:: ስኞ ጥዋት ጦርነቱ መፋፋም ሲጀምር ከሞት የተረፉትን ወታደሮች ቀስ ብለው ማምለጥ እንዳለባቸው መከረው እርሳቸው ታጥቀው ይጠብቁ ጀመር:: እጅህን ስጥ የሚለውን ማግባቢያ ማሰብ ቀርቶ መስማት አልፈለጉምና::

Acton Roger The Abyssinian Expedition, London, በተባለው መጽሐፍ ገጽ 62 "Why are your people so slow? he said. I am tired of looking out; I am going to rest a while, He then shut himself::

ትርጉም "ሕዝባችሁ ለምን ቀስተኛ ሆነ? አሁንስ ወደውጭ ማንጋጠጡ ሰለቸኝ ጥቂት ማረፍ እፈልጋለሁ፤ከዚያም ራሳቸውን ገደሉ" ሲሉ ጽፈዋል። ይህን ያደረጉ አጤ ቴዎድሮስ ጥቃት በመጥላታቸው ምክንያት ነው። ጥቃት የማይወዱት አጤ ቴዎድሮስ ቀድመው ለመሞት የወሰኑ ለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የለውም። የእርሳቸው በዚህ ምክንያት መሞት ዛሬ ወታደሮች አርአያ አድርገውት ለአገራቸውና ለክብራቸው ሲሉ እየደገሙት ናቸው።

ብ/ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተ ማርያም <u>የጦር ውሎ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 157 "አንድ ሰውና አንድ ጥይት እስኪቀር ድረስ ታግለን የመጨረሻውን ጥይት ጠጥተን የቴዎድሮስን የባልቻ አባ ነፍሶን ታሪክ አድሰን ሞት መሞት አለብን" ሲሉ ጽፈዋል።

ከዚህ በኋላ ሻለቃ ማሞ ተምትሜ፤ከአቅማቸው በላይ ሲሆንባቸው ራሳቸውን መግደላቸውን አስመልክቶ ገጽ 179 ላይ ጽፈዋል። ሻለቃ ማሞ ተምትሜ መማረክ ነውር ሁኖባቸው የአጤ ቴዎድሮስን ጽዋ ጠጥተዋል። ይህ ጀብድ እንዳይፈጸም ነው ወያኔ ዛሬ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ዘመቻ የጀመረው አልገባው ብሎ እንጂ ታሪኩ የሁላችን ነበር።

<u>ኢትዮጵ ጋዜጣ</u> ግንቦት 18 ቀን 1996 ዓም ገጽ 15 "ከኔ የሚቀጥሉት መሪዎቿ ያስተካክሏት ይሆናል.ብለው ተከዙ። ጦርነቱ ግን አሁንም ተፋፍሟል። የጠላት ጦር ተራራውን እየቧጠጠ ወደ አምባው መውጣት ይዟል። ድንኳኖች፤በጥይት ይቀጣጠላሉ፡ እንዲሁም ቤቶች። አጤ ቴዎድሮስ አገራቸውን በሲቃና በሰቀቀን ከተሰናበቱ በኋላ እጃቸውን እንደ መስቀል አድርገው አማተቡ።"

"ወደ መቅደላ መድኃኔዓለም ፊታቸውን አዙረው ሰገዱ፡ ተከታዮቻቸውን ራሳቸውን እንዲያድኑ አሰናበቱአቸው። የእቴጌ ጥሩ ወርቅ ለቅሶ ከዓላማቸው አላነቃነቃቸውም በዓለማየሁ ሞት እጃችንን እንስጥ ቢሏቸው አልሰሙአቸውም። ለዓለማየሁ የምተውለት ኑዛዜ አንዲት ኢትዮጵያ በዓይኑ እንደዞረች ሞተ ብለሽ ሲያድግ ንገሪው ብቻ አሉ። ሽጉጣቸውን ወደራሳቸው አነጣጠሩ። ተኮሱ ራሳቸውን ገደሉ" ሲል ጋዜጣው ጽፏል።



<u>ለምጩን መጽሔት</u> መስከረም 1991 ዓም ገጽ 15 "አጤ ቴዎድሮስ ዝናቸው ለዓለም አብርቷል። እውነተኛ መሪነታቸው ጽኑነታቸው በየትውልዱ ሕሊና እየነቃ የሚሄድ ሆኖ ተገኝቷል። መይሳው ካሣ እንደ ልዩ ፍጡር የሚቆጠሩ ጀግና..ከአገር መዋረድ በፊት እኔ ልውደቅ በማለት ታሪክ የሠሩ ሲሆኑ በትክለ ፍጥረትነታቸው የተደነቁ የሥነ ግጥም ቋጠሮዎች ያሉላቸው መቼም አይጠወልግም። ለአገራችን ተኝታ በማታውቀው እንግሊዝ ሴራ እጄን አልሰጥም አሻፈረኝ በማለታቸው በጀግንነት ተሠዉ" ሲል መጽሔቱ ጽፎ ነበር።

<u>የኢትዮጵያ መንግሥት በወርኃ የካቲት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 5 "ሚያዝያ 5 ቀን በዓለ ትንሣኤውን አከብረው ከባለቤታቸው ከእቴጌ ጥሩ ወርቅ ውቤ ጋር በመቅደላ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ሥጋውን ደሙን ተቀብለው ወደ አዳራሻቸው ተመልሰው በጊዜው ለነበሩት መኳንንትና ሕዝብ ግብር ሲያበሉ ሲያጠጡ ውለው መኳንንቱን እንግዲህ ጊዜው ስለደረሰ መውጫ ብታገኙ ነፍሳችሁን ብታተርፉ መልካም ይመስለኛል እኔ ግን በዚሁ ነፍሴን ለእግዚአብሔር ሰጥቼ ክብሬንና ዘውዴን ለኢትዮጵያ አበርክቼ እሞታለሁ አሏቸው።"

"ጊዜው መሸ ነጋ ሚያዝያ 6 ቀን ሰዓቱ3 ሰዓት መሆኑ ነው። አሁን የእንግሊዝ ጦር የመቅደላን በር ሰብሮ ገባ። ከዚያም ጀግናው አጤ ቴዎድሮስ ወደ ላይኛው የመቅደላ በር ወጥተው በመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አንጻር ቆመው የእንግሊዞችን አቀራረብ ይመለከቱ ነበር። በዚህ ጊዜ አብረዋቸው የነበሩት ባለቤታቸው እቴጌ ጥሩ ወርቅ ውቤ ልጃቸው ሕጻኑ ዓለማየሁ ቴዎድሮስና አብራቸው የምትኖረው ሳጃሜይቱ ምንትዋብ ነበሩ። ሌላ ሰው ማንም አልነበረም።"

"አሁን የእንግሊዝ ወታደሮች እየገሰገሱ ወደ እሳቸው ሲቀርቡ ጀግናው አጤ ቴዎድሮስ በርከክ አሉና ሽጉጣቸውን በአፋቸው ላይ ደቅነው እንደ ውሃ ጠጥተው ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር ሰጥተው ዐረፉ። የጀግናውን ዘውድ ከራሳቸው ላይ ሲያነሡ ጀግናይቱ ምንትዋብ የማነን ዘውድ ማን ያነሣዋል ከባለቤቱ ከጀግናው ጋር በኢትዮጵያ ይቀራል እንጂ ብላ ተራምዳ ዘውዱን ካነሣው ወታደር ጋራ ትንቅንቅ ጀመረች።"

"ጉሮሮውን አንቃ የማትለቀው ስለሆነ አንድ የእንግሊዝ ወታደር ሲተኩስ ጓደኛውንም ምንትዋብንም አንድ አድርጎ ጣላቸው:: አወዳደቃቸውም ከጀግናው አጤ ቴዎድሮስ ሬሣ ሥር ዝቅ ብሎ ነበር:: በዚህ ጊዜ ለእንግሊዝ ታላቅ ኀፍረት ሆነ:: ወዲያው ዘውዱን አንሥተው የአጤ ቴዎድሮስን ሹርባቸውን በሙሉ ቆርጠው በደም የጠለቀውን የሐር እጀ ጠባባቸውን አውልቀው ከነደሙ እጅ አደረጉት:: አሁንማ ማን ይከለክላቸዋል ጀግናይቱ ምንትዋብም ከቴዎድሮስ በታች ወድቃለች"ሲሉ ጽፈዋል::

"ገደልን እንዳይሉ ሙተው አገኟቸው
ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በኛቸው
ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው
ለወሬ አይመቹም ተንኮለኞች ናቸው::
በሰው እጅ መሞት ነውር ሁኖበት
እዩት ተመልከቱት የጀግናውን ሞት
መሳፍንቱን ሁሉ አጭዶ እንደገባስ
መቅደላ ወደቀ የታጠቅ ፈረስ፥
እጁን ለጠላት አልሰጥም ብሎ
ባሩዱን ጠጣው ጠጅ አስመስሎ":: ተብሏል::

እንግሊዞች ሲመጡ ገና "አጤ ቴዎድሮስን አስራችሁ አምጡት እንጂ እንዳትገድሉ" የሚል ትእዛዝ ስለነበራቸው አታለው ለመያዝና ለመውሰድ ነበር አላማቸው ነገር ግን ጀግናው እጄን አልሰጥም ብለው ሲሞቱ እንግሊዞች ኀፍረት ተሰማቸው ይህን አስመልክቶ ሊቀ ጠበብት ባሕሩ ዘውዴ ይህን ብለዋል::

<u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 41-42"በዚህ ድርጊቱም እንግሊዞች የጦር ድግስ ላይ የምፀት ሣቁን ሥቆ አለፈ:: እጁን ይዞ ለመመለስ የተላከው 32.000 የእንግሊዝ ጦር ባዶ እጁን እንዲመለስ ተገደደ" ሲሉ ጽፈዋል::

ጄኔራል ናፒዬር በ24 ሰዓት እጃቸውን እንዲሰጡት በጠየቃቸው ጊዜ "እግዚአብሔር ቢሰጠኝ ሁሉን ልገዛ አሳብ ነበረኝ:: እግዚአብሔር ቢነሳኝ ልሞት አሣቤ ይህ ነበር:: ከተወለድሁኝ እስታሁን ወንድ እጄን ጨብጦት አያውቅም ነበረ ሰዎች ሲሼሹ ተነሥቼ ማረጋጋት ልማድ ነበረኝ ጨለማ ከለከለኝ:: ትላንትና በደስታ ያደራችሁ ሰዎች



እግዚአብሔር እንደኔ አያድርጋችሁ:: እንኳን የሀበሻ ጠላቴን ኢየሩሳሌም ዘምቼ ቱርኮችን አስለቅቃለሁ መስሎኝ ነበር:: ወንድ ያቀፈ ወንድ ተመልሶ አያቅፍም" ብለው ላኩበት::

ስዩም ወልዴ <u>ካሳ እና ካሳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 167 "ኃይለኞችን እንደሕፃን በክንዱ ይዞ የኖረ እንደ ቴዎድሮስ ያለ ቆራጥ በሰው ክንድ፤በጨቋኝ እጅ መያዝን ሊታገሥ አይችልም:: ያገሩን ሕዝብ አንድ ለማድረግ ሲታገል በውስጥም ሆነ በውጭ ያስቸገሩትን ሁሉ ለማሸነፍ ሲል ራሱ በንዴት የቀጣቸው ሳያንስ የሀገሩን ሰዎች ከክፉ ጥፋት ላይ ላለመጣል ያደረገው ውሳኔ ደግሞ የብልህነት ውሳኔ ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

ዓለማየሁ ነሪ ውርጋሶ <u>ኧሰት የባህልና የታሪክ መሠረት አንደኛ መጽሐፍ</u> በተባለው ገጽ 202 "በዘመነ መሳፍንት የተነጣጠሉትን ግዛቶች እንደገና በመመሥረት በዘመናዊ ሥልጣኔ በአንድ ለመምራት፤በምጣኔ ሀብት በጦር ሠራዊት፤በጦር መሣሪያ ፋብሪካ ኢትዮጵያን ወደፊት ለማራመድ በነበራቸው ጽኑዕ ፍላጎትና ባላሰለሰ ጥረታቸው ሳቢያ ከእንግሊዝዋ ንግሥት ቪክቶሪያ ጋር የተፈጠረው አለመጣጣም መነሻ ሆኖ የእንግሊዝ ቆንስልና ሌሎችንም ስላሰሯቸው ጠቡ ከርሮ ያሰቡትን ሁሉ ሳያሳኩ ቴዎድሮስ በጄኔራል ናፒየር ከመማረክ ሞታቸውን መርጠው መቅደላ ላይ ራሳቸውን በሽጉጣቸው ገደሉት" ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስ እስከመጨረሻው ለመታገል ባደረጉት ትግል በትግላቸው ባስገኟቸው ድልና የክብር ሞት ሞቱ:: በእንግሊዝ ጦር አለመማረካቸው ክብርንና ታሪክን ለሚወድ ትውልድ ለኢትዮጵያውያን ክብር አጎናጽፈውናል:: በየጊዜው በተነሡ ወራሪዎች ላይ ድልን እንድንጎናጸፍ ወሳኝ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: ብሔራዊ አንድነትና ማዕከላዊ መንግሥት በመመሥረታቸው ብቻ ሳይሆን ትውልዱ እንዲኮራ አድርገውናል::

የአጤ ቴዎድሮስ ሕይወት ይህንን በመሰለ አሻጥር ቢቋጭም ለኢትዮጵያ የነበራቸው ራእይ አብሮአቸው አልሞተም:: እርሳቸው የለፉለት አብዛኛው በሥራ ላይ ውሏል:: የቀረው ኢትዮጵያዊ ራዕይ የተላበሰ የፖለቲካ ኃይል ብቅ የሚልበት ጊዜ ይመጣል:: ማን ያውቃል አንድ ጀግና ይወለድ ይሆናል!::

# ምዕራፍ 4

## ወይዘሮ ምንትዋብ "ዘውድ ለባለዘውድ" አሉ

"ታሪክ ይታመማል እንጂ አይሞትም" ይባላል:: ወይዘሮ ምንትዋብ የጎጃም ተወላጅ እንደነበሩ ደራሲያን ሁሉ ይስማማሉ:: ዳሩ ግን የወይዘሮ ምንትዋብን አሟሟት አስመልክቶ ከዚህ በፊት ደራስያን ሳይገልጡልን ነበር የቆዩት:: "ይህን ብላ ሰደበቻቸው ይህን ገጠመችባቸው" የሚለው በሰፊው ሲጻፍ በመጨረሻ የሠራችውን ጀብድ ግን አልነገሩንም:: በእርግጥ በስንኙ ከሚነገረው ዜማ ለተመራመረው ሴት መሞቷን ስንኙ ይገልጻል::

"መቅደላ አፋፉ ላይ ጨኸት በረከተ
የሴቱን እናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ" ይላል::

አጤ ቴዎድሮስ የሞቱ እለት ሴቶች መሞታቸውን የሚጠቁም ሲሆን ማንነታቸውን ግን አልጠቀሱልነም:: ለነገሩ የወይዘሮ ምንትዋብን ጀግንነት አስመልክቶ ጽፈው የተዉት ራስ መሸሻ ቴዎድሮስ መሆናቸውና መጽሐፉ ያለበትን ቦታ ታሪኩን ለአንባቢ ያወጡት ቀሲስ ከፍ ያለው መራሒ በሥዕል አስደግፈው ታሪኩን ጽፈዋል::

ቀሲስ ከፍ ያለው መራሒ <u>ምንትዋብ</u> በተባለው መጣጥፍ ገጽ 26 "አጤ ቴዎድሮስ ከጎጃም ባላባታዊ አስተዳዳሪዎች ጋር ሲዋጉ የምንትዋብ አባትና ወንድሞች ሞቱ:: ምንትዋብ በዘመዶቿ መገደል አእምሮዋ ተነክቶ 14 ዓመት ቴዎድሮስ ከዋሉበትና ካደሩበት ሳትለይ እየተከተለች ትሰድባቸው ነበር:: አባ ታጠቅ ቴዎድሮስ አባቷን ወንድሟንና ባሏን ስለገደሉባት ምንትዋብ ኀዘኗን በምሬት ስትገልጥ እንዲህ አለች::"

"ጠጅም እንዳያምረኝ ቀደም ጠጥቻለሁ፤
ሥጋም እንዳይርበኝ ቋንጣ ሰቅያለሁ፤
ቢሻኝ ከወንድሜ ካባቱ እበላለሁ፤



ይህን ስትነግሩት ያኀራል ላመሉ፤
ማናትም ቢላችሁ ምንትዋብ ናት በሉ::
ሺህ ብረት ከኋላው ሺህ ብረት ከፊቱ፤
ይህን ሳታይ ሄደች ኮሶ ሻጭ እናቱ፤
አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ፤
አቃጥሎ ለብልቦ አንድዶ ይፍጃችሁ"::

"በሌላ በኩል ደግሞ ምንትዋብ የቴዎድሮስን ጀግንነት ታደንቅ ስለነበር ገላሱን ፈትጋ ቆሎውን ቆልታ ዳቦውን ጋግራ በአገልግል ይዛ አብራ እየዞረች ቴዎድሮስ በጦር ሜዳ ሲፋለሙ ውለው ሲመለሱ ጀግናው እንካ ብላ እያለች ትመግባቸው ነበር:: በመጨረሻም ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር በተፈጠረው አለመግባባት" ይሉና::

"ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀ ሠራዊት ጋር ሚያዝያ 3 ቀን ዓርብ የስቅለት ዕለት 1860 ዓም ሰላምኮ ሥላሴ ላይ በተደረገው ጦርነት የቴዎድሮስ ጀግኖች ፊትአውራሪ ገብርዬ እና ደጃዝማች ገልሞ ከ600 ጀግኖች ጋር ከወራሪው የእንግሊዝ ጦር ጋር ተፋልመው መቼም በለስ አልቀናቸውምና ሲያልቁ ለቴዎድሮስ የቀረቻቸው ጀግና ምንትዋብ ብቻ ነበረች::"

"ከዓርብ ጀምራ 3 ቀናት ከጀግናው አጤ ቴዎድሮስ ጋር አብራ ውላ የትንሣኤ በዓል ገድፋ ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ዓም በመቅደላ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በር ላይ አጤ ቴዎድሮስ በሰማዕትነት ሙተው ጀግንነታቸውን በገዛ እጃቸው ሲያጡት ከአጠገባቸው የነበረችው ምንትዋብ እንግሊዞች ዘውዱን ከአጤ ቴዎድሮስ ራስ ላይ ለማንሣት ሲሽቀዳደሙ የማንን ዘውድ ማን ይወስደዋል ኢትዮጵያ ላይ ይቀራል እንጂ በማለት አላስነካም ብላ የወታደሩን ጉሮሮውን አንቃ የማትለቅ ስለሆነ አዛገቡ ገደለችው አይደል አትላትም ሲለው አንድ የእንግሊዝ ወታደር ሲተኩስ ምንትዋብንና ጓደኛውንም አንድ አድርጎ ጣላቸው::"

"አወዳደቃቸውም ከጀግናው አጤ ቴዎድሮስ ሬሣ ዝቅ ብሎ ነበር:: በዚህ ዓይነት ለእናት አገሯ ለኢትዮጵያ ሕይወቷን የሠዋች ጀግና ምንትዋብ ነበረች:: ይህን ታሪክ እስካሁን ማንም አልጣፈውም:: እንግሊዞችም በወቅቱ አልጻፉትም:: ምናልባት ጀግናውን ቢያጡ

ሴቷን ገለው መጡ እንባላለን ብለው ሊሆን ይችላል። የራሳቸውንም ወታደር አብረው ስለገደሉት ነገሩ ለፍከራ አያመችምና።"

"አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በዓለመ ሥጋ ሲኖሩ ሰይጣነ ጸሪፍ ያድርባቸውና ሰውን ይሳደባሉ፤ያዋርዳሉ በዚህ ምክንያት መንፈሰ እግዚአብሔር ይለያቸዋል። ሰይጣን ልቡናቸውን ዙፋን አድርጎ አእምሮአቸውን አፍዝዞና አደንዝዞ የእርሱን ተግባር እንዲፈጽሙ ያደርጋቸዋል።"

"አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከዚህ ዓይነቱ ቁርኝት ተላቀው አፍቅሩ ጸላእተክሙ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሟችሁን መርቁ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ የሚለውን ቃለ ወንጌል የሚፈጽሙ አሉ ማቴ.5.45 ለምሳሌ ምንትዋብ ከቀን ብዛት እየተጸጸተች ንስሐ እየገባች ጥላቻዋ ወደ ፍቅር ተለወጠ። በሥጋዊ ሕይወት ውስጥ በስድብ ጀምራ መንፈሳዊ ሕይወትን አገኘች። ይህም በመጨረሻው ለሰማዕትነት አበቃት።"

"በፍቅረ ሀገር በሰማዕትነት ዐረፈች። እኛስ ከዚህ ታሪክ ምን ትምህርት እንማራለን? ይህ ታሪክ ራስ መሸሻ ቴዎድሮስ "ገድለ ቴዎድሮስ"በሚል ርእስ በዘመኑ ከጻፉት መጽሐፍ ጎንደር እንፍራዝ ገነተ ማርያም ዕቃ ቤት ውስጥ ነው የተገኘው፤ ይህን አስደናቂ ታሪክ በመጽሐፍ ጽፈው ለትውልድ በማቆየታቸው ነፍሳቸውን ይማርልን በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል" ሲሉ ቀሲስ ከፍያለው ጽፈዋል።

<u>የኢትዮጵያ መንግሥት በወርኃ የካቲት</u> በተባለው መጽሐፍ" የእንግሊዝ ወታደሮች እየገሰገሱ ወደ እሳቸው ሲቀርቡ አጤ ቴዎድሮስ በርከክ አሉና ሽጉጣቸውን በአፋቸው ላይ ደቅነው እንደ ውሃ ጠጥተው ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር ሰጥተው ዐረፉ።"

"የእንግሊዝ ወታደሮች ከንግሥታቸው እንደታዘዙት አጤ ቴዎድሮስን በሕይወታቸው እጃቸውን ይዘው ለመውሰድ እንጂ ለመግደል ስላልነበረ ጀግናው ቀድመው በመሞታቸው የእንግሊዝ ወታደሮች የኀፍረት ኃዘን አዘኑ ተጸጸቱ።"



"ወዲያው ቀረብ አሉና የጀግናውን ዘውድ ከራሳቸው ላይ ሲያነሡ ምንትዋብ የማነን ዘውድ ማን ያነሣዋል ከባለቤቱ ጋር በኢትዮጵያ ይቀራል እንጂ ብላ ተራምዳ ዘውዱን ካነሣው ወታደር ጋራ ትንቅንቅ ጀመረች። ጉሮሮውን አንቃ የማትለቀው ስለሆነ የእንግሊዝ ወታደር ሲተኩስ ጓደኛውንም ምንትዋብንም አንድ አድርጎ ጣላቸው። አወዳደቃቸውም ከጀግናው አጤ ቴዎድሮስ ሬሣ ሥር ዝቅ ብሎ ነበር። በዚህ ጊዜ ለእንግሊዝ ታላቅ ኀፍረት ሆነ "ሲሉ ጽፈዋል።

"አባቴን ቢገድሉ ነበር መናደዴ፤
ወንድሜን ቢገድሉ ነበር መናደዴ፤
በራስሁ ቆረጡ ይቅር አለ ሆዴ"
ብለው መግጠማቸው አይዘነጋም።

እውነትም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ነበሩ። የጀግነዋ ወይዘሮ ምንትዋብን ታሪክ ለመጻፍ ስጀምር እስኪ ይህን ታሪክ ያገኙትን ቀሲስ ከፍ ያለው መራሒን ሳናግራቸው ብዬ ስልክ አዲስ አበባ፤ ደውዬ ሳናግራቸው ቀሲስ ከፍ ያለው መራሂ፤ "ለወደፊቱ የሚቀጥለው ትውልድ አስተካክሎ ታሪኩን እንደሚጽፍላቸው እርግጠኛ ነኝ። ሴትዮይቱ የወንዶች ወንድ ናቸው። በእንግሊዞች በኩል ይህን ታሪክ አልጻፉትም።

አጤ ቴዎድሮስን ጀግናውን ቢያጡ፤
ሴት ገድለው መጡ
ላለመባል ሲሉ ታሪክ ደፈጠጡ
የሚገርመኝ ነገር ቢኖር ጋዜጠኛ የተባለው እንኳን ሳይጠቅሰው ማለፉ ነው" ሲሉ በአድናቆት ገልጸውልኛል።

# ምዕራፍ 5

## እንግሊዞች የኢትዮጵያን ቅርሳቅርስ ዘረፉ

<u>አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 306 "በወቅቱ በሥፍራው የነበረው አሜሪካዊ ጋዜጠኛ ራቅ ብዬ ስመለከት ብዙ ኦፊሰሮች እንግሊዛውያን ሲቪሎች በደም የተበከለውን የቴዎድሮስን ሸሚዝ ለኔ ይገባል በማለት ሲጓተቱትና ሲጣሉበት አየሁ ይላል:: ይህ በደም የተለወሰው የቴዎድሮስ ሸሚዝ ዛሬ በእንግሊዝ አገር ባንክ ፊልድ ሙዚየም ውስጥ ይገኛል:: ያው ጋዜጠኛ ሬሳቸው ተዘርሮ ጠጉራቸው ተሸልቶ ልብሳቸው ተገፎ በከፊል እርቃነ ሥጋቸውን አየኋቸው ሲል ጽፏል"በማለት አቶ ጳውሎስ ኞኞ ጽፈዋል::

የእንግሊዝ ጦር የኢትዮጵያን ቅርሳቅርስ ብቻ ሳይሆን ደም የተነከረውን የፊታውራሪ ገብርዬን ልብስ እስከ ደሙ ለበሰው:: የአጤ ቴዎድሮስንም ልብስ ሆነ የአንገት ሀብል ሌላም ሌላ ቅርስ ይቅርና የራሳቸውን ጠጉር ነጭቶ ወሰደው::

መጻሕፍትን በተመለከተ አጤ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን ልጆች ሊያስተምሩበት ከተለያዩ አድባራት የሰበሰቡትን ልቅምቅም አድርገው ወሰዱ:: በአሁኑ ሰዓት በእንግሊዝ አገር ከ1000 በላይ መጻሕፍት እንዳሉ አንዳንድ ሰነዶች ሲጠቁሙ በዚህ ወቅት ወደ 600 መጻሕፍት ወስደዋል::

በዚህ ቀን በአጤ ቴዎድሮስ ግምጃ ቤት ብዙ የጦር መሣሪያ ተገኝቷል:: በእንግሊዞች እጅ ያልገቡ ጋፋት በኢትዮጵያውያን እጅ የተሠሩ ቀላል የጦር መሳሪያዎች ከጎጃም የመጡ ወታደሮች አጤ ቴዎድሮስ ድል ሲሆኑ ራሳቸውን እየተከላከሉ ወደ ትውልድ አገራቸው መግባታቸውን አቶ ጳውሎስ ይጠቁማሉ:: መቅደላ እንግሊዞች የማረኩት የጦር መሣሪያ ይህ ነበር::

1ኛ 83.563 የቀላል መሳሪያ ጥይቶች
2ኛ 11.063 ልዩ ልዩ ጠበንጃዎች



3ኛ 878 ሽጉጦች
4ኛ 555 የመድፍ ጥይት
5ኛ 481 ሳንጃዎች
6ኛ 15 መድፎች
7ኛ 7 መንጀኒቆች ሞርታሮች ተመዝግበዋል
8ኛ ከ1000 በላይ የተለያዩ መጻሕፍት::

ሀብቴ ለንደን <u>ጦቢያ መጽሔት</u> ቅጽ 7 ቁ 12-1992 ዓም ገጽ 17 "ታሪኩ በመቅደላ መወረር ይጀምራል:: በጄኔራል ናፒዬር የሚመራው የእንግሊዝ ጦር መቅደላን ከወረረ በኋላ የመቅደላን ምሽግ መዝረፍ ጀመረ:: አጤ ቴዎድሮስ ለብዙ ወራት እንዲያዋጋቸው ለሠራዊቱ ያዘጋጁትን ስንቅ የእንግሊዝ ጦር ተረባረበበት:: በሴቶች ላይ ከፍተኛ ድፍረት ተፈጸመ" ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስ የሚጠቀሙበት መጽሐፋቸው የማቴዎስና የማርቆስን ወንጌል በአንድነት የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ በለንደን ብሪትሽ ቤተ መጻሕፍት እንደሚገኝ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ነግረውኛል:: ሌላው የሚገርመው ነገር ደግሞ ታቦት ሳይቀር ዘርፈዋል:: ሚያዝያ 7 ቀን 1860 ዓም ከዘረፉት መካከል አንድ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ የካቲት 2 ቀን 1994 ዓም ተመልሷል::

ሊ.ማ. አበባው ይግዛው <u>የቁም ጽሕፈት ሙያ በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 62 " የመቅደላውን ወረራ ከማቀዳቸው በፊት አንድ የምርምር ሊቅ አብሮ እንዲሄድ አዘጋጅተው ነበር:: ለዚህም ሥራ Mr.r.r holms የሚባሉ ምርጥ ዕቃ አሳሽ ከወታደሩ ጋር አብረው ተልከው ቅርሳቅርሶች ይገኛሉ በሚባሉበት ቦታ ሁሉ እንዲያስሱ በተለይም የብራና መጻሕፍትን እንዲያሰባስቡ መመሪያ ተሰጥቷቸው ነበር::"

"ግን የጦርነቱ ሁኔታ ጊዜ ስላልሰጣቸው በሌሎች ቦታዎች ያሉትን ቅርሶች ማሰባሰብ ባይችሉም በመቅደላ የተገኙትን ምርጥና ድንቅ መጻሕፍት መርጠውና ዘርፈው ለማምጣት በቅተዋል:: ስለመጻሕፍቱና ቅርሶቹ በእሥር ላይ ከነበሩ እንግሊዞች ቀደም ብለው መረጃ ማግኘታቸው አይጠረጠርም:: የቀረውንም ወታደሩ ዘርፎ ስለነበር ከጊዜ በኋላ ከግለሰቦች እየተገዙ የተጨመሩ አሉ::"

"የተዘረፈውና የተቃጠለው ቅርሳቅርስ እቃዎች ቀደም ብሎ ቆጠራ እንደሚያስረዳው መጻሕፍቱ ብቻ ከሸህ በላይ ነበሩ:: ጸሐፊው እንደሚሉት ቢያንስ ከ500 ያላነሰው ወደ እንግሊዝ ሀገር ተወስዷል: (ሙሉ ዘገባ ያለበት የአጤ ቴዎድሮስ የማቴዎስና የማርቆስ ወንጌል በአማርኛ፣ የተጻፈ ከተዘረፉት ጋር አብሮ በብርቲሽ ቤተ መጻሕፍት ይገኛል)" ይሉና::

"አጤ ቴዎድሮስ ማዕከላዊ ቤተ መጻሕፍት በመቅደላ አቋቁመው ከየአድባራቱና ገዳማቱ በተለይ ከጥንት ቤተ መንግሥት የሰበሰቧቸው የብራና መጻሕፍት ተዘረፉ:: በደረሰው ጥቃት እርሳቸው ብቻ ሳይሆኑ መጻሕፍቱም ተቃጠለ:: ከዚያም በኋላ ያለው ዘመን ቅርስ የሚጠበቅበት አልሆነም" ሲሉ ጽፈዋል:: የሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛውን ዘገባ የሚያጠናክር የአቶ ማሞ ውድነህ መጽሐፍ ተጠቃሽ ነው::

ማሞ ውድነህ የደረስኩበት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 257 "አጤ ቴዎድሮስ በየቤተ ክርስቲያኑ መጻሕፍትን አሰባስበው ባንድ እንዲቀመጡና ሕዝቡ የጸሎት መጻሕፍትን ብቻ ሳይሆን የዕውቀት መጻሕፍትንም እያነበበ እንዲመራመር ጥረት ያደርጉ እንደነበር ይታወቃል::"

"ቴዎድሮስ በዘመነ መንግሥታቸው አንድ ሺህ ያህል መጻሕፍትን በቤተ መንግሥታቸው አሰባስበው እንደነበርና በኋላም እንግሊዞች ዘርፈው የወሰዱት መጻሕፍት በጨረታ የብርቲሽ ሙዚዬም አራት መቶ የሚሆኑትን ገዝቷል:: እስከዛሬም ድረስ በዚያው እንደሚገኙ ጥናቶች ያረጋግጣሉ" ሲሉ ጽፈዋል::

1860 ዓም እንግሊዞች ከወሰዱት ንብረት መካከል የአጤ ቴዎድሮስ ዘውድ አንዱ ነበር:: ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ አገራቸውን ወዳድ ታሪካቸውን አፍቃሪ ነበሩ:: በዚህ ምክንያት በ1916 ዓም ራስ ተፈሪ መኮንን አልጋወራሹን ወደ ሎንዶን በላኩ ጊዜ ካስጠየቁት እቃዎች መካከል የአጤ ቴዎድሮስ ዘውድ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ነበር::



ሆኖም በዚህ ወቅት ተልከዋልና አልጋ ወራሹ መጠየቃቸው አልቀረም:: እንግሊዞች ራሳቸው እንደወሰዱት ራሳቸው ማምጣቱን መረጡ:: በዚህ ምክንያት ዘውዱን ለንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ አስረከቡ::

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 284 "የአጤ ቴዎድሮስ ዘውድ ስለ መመለሱ! ከእንግሊዝ አገር የመጣው የአጤ ቴዎድሮስ ዘውድ ሐምሌ 4 ቀን 1917 ዓም ቅዳሜ ለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ተመለሰ::"

"ከጧቱ በ4 ሰዓት የግቢ ምኒስትር ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል በሻህ በጦር ልብስ ያጌጡ ጭፍሮችን አስከትለውና በአራት ፈረሶች የሚሳብ ሠረገላ አሲዘው ከአቶ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ፀዳሉ ጋራ ወደ እንግሊዝ ሌጋሲዮን ሄዱ:: የእንግሊዝ መንግሥት ሚኒስትር ሚስተር ቻርልስ ቤንቲንክም ዘውዱን በሠረገላው ላይ አስቀመጡትና ሁሉም ዘውዱን አጅበው ወደ ቤተ መንግሥቱ መጡ::"

"ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ በቤተ መንግሥታቸው ውስጥ በተለይ በተሰናዳው በቀኝና በግራ ተሰልፈው ነበርና ሠረገላው በሰልፍ መካከል አልፎ ከንግሥት ፊት ደረሰ:: እዚያም አንድ ጠረጴዛ ተዘጋጅቶ ነበርና ሚስተር ቤንቲንግ ዘውዱን ከሠረገላው አውርደው ከጠረቤዛው ላይ አስቀመጡትና ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ"::

"ግርማዊት ሆይ በንግሥት ቪክቶሪያ መንግሥት በ1868 ዓም ከመቅደላ የተወሰደው የአጤ ቴዎድሮስን ዘውድ የታላቂቱ ብሪታንያና የአየርላንድ፤ከባሕር ማዶ ያሉት ግዛቶች ንጉሥና የሕንድ ንጉሠ ነገሥት በሆኑት በግርማዊ ጌታዬ በንጉሡ ትእዛዝ ለግርማዊት ንግሥት በማክበር መለስሁ:: ብለው ተናግረው ሲጨርሱ ተጨበጨበ:: ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ራስ ተፈሪ መኮንን የሚከተለውን ቃል ተናገሩ::"

"ክቡር ሚኒስትር ሆይ! ካውሮፓ መንገዴ በተመለስኩ ጊዜ ግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ ያጤ ቴዎድሮስን ዘውድ እመልሳለሁ ብለው ስለናበታቸው የነገሩኝን ቃል ለግርማዊት ንግሥት ባመለከታቸው ታላቅ ደስታ አድርገው ነበር:: አሁንም የግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ

ቃላቸው ስለ ተፈጸመ ግርማዊት ንግሥትና የኢትዮጵያ ሕዝብ በመላው እግዚአብሔርን በቸርነቱ እናመሰግናለን። ይህ ዘውድ ከ57 ዓመት በኋላ እኔ ወደ አውሮፓ በመሄዴ ምክንያት በግርማዊት ንግሥት በመንግሥታቸው ዘመን ተመልሶ ስለ መጣልን በጣም ደስ አለን።"

"ክቡር ሚኒስትር ሆይ! እዚህ ላይ የማስታውስዎ ይህ ያጤ ቴዎድሮስ ዘውድ ተመልሶ ስለ መጣልን ከትልቅ መታሰቢያ እንቆጥረዋለን፤ነገር ግን የኢትዮጵያ ዘውድ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ከብሮ የኖረና አሁንም ወደፊት እስከ ፍጻሜ ዘመን ባለተስፋ መሆኑ ከዕውቀትዎ እንዳይሰወርዎ በፍጹም አምናለሁና ለዚህ ታሪኩን አስረዝሜ ልነግርዎ የሚያስፈልግ መስሎ አልታየኝም።"

"ክቡር ሚኒስትር ሆይ! ይህ የግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ ስጦታ የሚደነቅ የወዳጅነት ምልክት ስለ ሆነ ግርማዊት ንግሥት በፍጹም ልቦናቸው ምስጋናቸውን ለግርማዊ ንጉሥ ያቀርባሉና እንዲያስታውቁላቸው በብዙ ይለምኑዎታል። እኔም ራሴ ንጉሥ ጆርጅን ለማየት ሄጄ በታላቁ ከተማቸው ሳለሁ ይኸንን ቸርነታቸውን ስላሳዩኝ ይህ ሥራ ለዘለዓለም ከልቤ ተጽፎ መታሰቢያ ሆኖኝ ይኖራል።"

"በዚህም ምክንያት ከፍ ያለ ምስጋናዬን ለግርማዊ ንጉሥ አቀርብላቸዋለሁ። ቸርነቱ የማያልቅበት እግዚአብሔር ለግርማዊ ንጉሥ ጆርጅና ለግርማዊት ሜሪ እንዲሁም ለቤተ ዘመዶቻቸው ሁሉ ሰላምና ጤና ክብርና ደስታ ለዘወትር እንዲሰጣቸው በታላቅ ተስፋ እንለምናለን። ልዑል አልጋ ወራሽ ይህን ተናግረው ሲጨርሱ ተጨበጨበና በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የሻምፓኝ ግብዣ ሆኖ ሥነ ሥርዓቱ ተፈጸመ" ሲሉ ጽፈዋል።

እንግሊዞች የኢትዮጵያን ቅርሳቅርስ በብዛትም መጻሕፍት ዘርፈው ወስደዋል። የኢትዮጵያን ቅርሳቅርስ ሽጠውታል። ከሚገርመው ነገር ታቦት ሳይቀር መውሰዳቸው የሚያስገርም ነው። አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያውያንን ለማስተማር ያመቻቸው ዘንድ ጎንደር ከተማ የ44 ቤተ ክርስቲያንን መጻሕፍት ወደ መቅደላ መውሰዳቸው አይዘነጋም።

እነዚህን መጻሕፍት እንግሊዞች ወደ ሀገራቸው ወስደውታል። እንኳን መጻሕፍቱንና ሌላውን ርቅሳቅር ቀርቶ በደም የተጨማለቀውን



የአጤ ቴዎድሮስን ልብ አውልቀው ወስደውታል። የፊታራራሪ ገብርዬን ልብስም እንዲሁ ከሬሳቸው ላይ አውልቀው ለብሰውታል።

መቅደላ የተዘረፈውን ንብረት አስመልክቶ ከሌሎች የታሪክ መጽሐፍት በይበልጥ ጥናት አድርገው ያቀረቡት ግርማ ኪዳኔ ናቸው። ይህም ታሪክ የሚገኘው የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ባሳተመው ካሳ እና ካሳ በተባለው መጽሐፍ ነው።

ግርማ ኪዳኔ ካሳ እና ካሳ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 205-215 ባለው ይገኛል። ታዲያ ከዚህ መጽሐፍ ጥቅስ ልወስድ ማቅለም ጀመርኩና ስመለከተው ግርማ ኪዳኔ በጣም በጥልቅ በጥናት ያመጡት በመሆኑ ሳሳሁለት። ጥቅስ ከምወስድ እኔ እንዳነበብኩት ሌሎች ወገኖቼ ኢትዮጵያውያን ካሳ እና ካሳ የተባለውን መጽሐፉን ያላገኙ ከዚህ መጽሐፍ ላይ እንዲያነቡት ስለፈለኩኝ በአባሪ አውጥቸዋለሁ። ታዲያ ታዝናላችሁ፤ታለቅሱማላችሁ፤ ልትቆጡም ትችላላችሁ። አባሪ ቁጥር 4 ይመልከቱ።